“የተፈጥሮ ፈውስ” ከተባለ በጠበብት የጸደቀ መሆን ይኖርበታል

አሸናፊ ዘደቡብ

ኩረጃና የትምህርት ጥራታችን ማሽቆልቆል ወዴት ይወስደናል?

መምሕር አሸብር ውርጌሳ

አዲስ አበባ የትናንሽ መንግስታት ከተማ ልትሆን?

መላክ ቢ.


# ግዮን

በየሳምንቱ ቅዳሜ

ግዮን ቅጽ 2 ቁጥር 56 ግንቦት 2011 ዓ.ም

ዋጋ 14.99

በተለይ ለግዮን መፅሔት



## የጽንፈኝነት አመጣጥ በኢትዮጵያ

መሳይ ከበደ (ፕሮፌሰር)



## የእነ ታማኝ ግሎባል አልያንስ

እነ ታማኝ ገንዘቡን ከየት አመጡ?

ግዮን ቅጽ 1 ቁጥር 56 ቅዳሜ ግንቦት 10 2011 ዓ.ም



# የእነ ታማኝ ግሎባል አሊያንስ


14

2 ግሎባል አሊያንስ ለተፈናቃዮች ከ31 ሚሊዮን ብር በላይ አሰረከበ

3 ድሬድዋ በሰርግ ላይ የተነሳው አለመግባባት ወደ ብሔርና ሐይማኖት ግጭት ተሻገረ

4 ወንጀለኞችን ከመያዝ ባሻገር፤ የሕግ ክፍተቶችንም መሙላት ያስፈልጋል!!!

7 **አዲስ አበባ** የትናንሽ መንግስታት ከተማ ልትሆን? — መላክ ቢ.

10 **የአግ7 ጉባኤ ኢሳትን በተመለከተ ጉባኤው ያስተላለፈው ሙሉ ውሳኔ**

12 ኩረጃና የትምህርት ጥራታችን ማሽቆልቆል ወዴት ይወስደናል? — መምሕር አሸብር ውርጌሳ

13 “የተፈጥሮ ፈውስ” ከተባለ በጠበብት የጸደቀ መሆን ይኖርበታል — አሸናፊ ዘደቡብ

11 **ለዛ**

18 “ቢከፍቱት ተል”ባ የሆኑ ተቋማትን እንዴት እናጠንክራቸው? — ኢዮብ ሳለሞት

19 ምክንያታዊነት ለኑሮአችንና ለፖለቲካችን — ተስፉ (ኢትዮጵያ) አሊታሰብ

21 **የሴትነት ተግዳሮቶች ጀግና**

23 በሀገራችን የመጣው ለውጥ ግቡን ይመታ ዘንድ መደራጀት ግድ ይላል — ጥላሁን መሸሻ

27 “ትፈልጉ እንደኾነ፤ አስከሬኑን ውሰዱና ቅበሩት”

**የማትጨርሰውን ነገር አትጀምር “ዋ”!** — መታሰቢያ መልአከ ሕይወት 16

**የታጠፉ ጥያቄዎች** — ፍቅርተ ተሾመ 17

5




# የጽንፈኝነት አመጣጥ በኢትዮጵያ

መሳይ ከበደ (ፕሮፌሰር)


**ግንቦት 8 የዛሬ 30 ዓመት** 28


**ቀጣይ ዕትም ቅዳሜ ግንቦት 17 ይጠብቁን!**




ቁጥር 55 ዕትም

# ሰላም ፌስቲቫል በወላይታ ሶዶ

በሰናይት ማርዮ የተቋቋመው ‘one peace fashon’ የተሰኘው ድርጅት “ሠላም ፌስቲቫል”ን ግንቦት 25 ቀን 2011 ዓ/ም በወላይታ ሶዶ ጉተራ አዳራሽ ሊያቀርብ መሆኑን አስታወቀ፡፡

ለወጣቱ ሠላምን ለመስበክና እየተዝናና ባህሉን የሚያውቅበት መድረክ ለመፍጠር ሲባል ተዘጋጅቷል የተባለው ሠላም ፌስቲቫል በርካታ ዝግጅቶችን ያካተተ መሆኑንም ለመረዳት ተችሏል፡፡ በተለይም የአገር ባህል አልባሳትን፣ በእጅ የሚሰሩ የጥጥ አልባሳትንና ዲዛይኖቻቸውን (ውቅሮቻቸውን) በማስተዋወቅ ለአገር ውስጥና ለውጭ አለም ሰዎች የባህል ልውውጥ አጋጣሚዎችን መፍጠር ዋንኛ አላማው እንደሆነም የደረሰን መረጃ ያመለክታል፡፡

‹‹ኢትዮጵያዊ የሆኑት የባህል አልባሳቶቻችን እጅግ ውብና የተለዩ ሆነው ሳለ አገራችን ከአልባሳቶቹ ማግኘት የሚገባትን ኢኮኖሚያዊ ጥቅምን እስካሁን ማግኘት አልቻችም፤ ይህም ሊሆን የቻለው ለዘርፉ ትኩረት በመነፈጉ ነው፤ በመሆኑም የባህል አልባሳቶቻችን ለአገራችን የገቢ ምንጭ እንዲሆኑ በር ለመክፈትና የአገር ውስጥም ሆኑ የውጭ ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪዎች አይንና ሀሳባቸውን ለመሳብ ታቅዶ የተዘጋጀ ፌስቲቫል ነው›› ሲሉ የፌስቲቫሉ አዘጋጅ ሠናይት ማርዮ ተናግረዋል፡፡በወላይታ ሶዶ በሚካሄደው በዚህ ፌስቲቫል ላይ የተለያዩ ክንውኖች እንዳሉ የተነገረ ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ አስር (10) ታዋቂ ኢትዮጵያዊ ዲዛይነሮች የፋሽን ስራዎቻቸውን ያቀርባሉ፣ የሙዚቃና የኮሚድያን ዝግጅት፣ እንዲሁም የሥዕል ኢግዚብሽንም ተካቷል፤ ከጀርመን፣ ከፓሪስና ከጣሊያን የመጡ ታዋቂ የፎቶግራፍ ባለሙያዎችም የዝግጅቱ ተካፋይ መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በጣሊያን ሮም የሀይቅ ዳርቻ የምትገኘውና የሆሊዉድ ዝነኞች መናሀሪያ ከተማ በሆነችው ብራቻኖ ከተማ እና በወላይታ ሶዶ ከተሞች መካከል የእህትማማችነት ስምምነት እንደሚደረግም ይጠበቃል፡፡ በሌላም በኩል ከፌስቲቫሉ አስቀድሞ ከታወቁትና ከተለመዱት የአገራችን መስህቦች በተጨማሪ በተለይም በደቡብ ክልል የሚገኙትን በርካታ ያልተዳሰሱ መስህቦች ለአገር ውስጥና ለውጭ ቱሪስቶች በስፋት ለማስተዋወቅ የሚያስችልና ለፕሮሞሽን ግብአት የሚውል ቀረፃ እንደሚደረግም ታውቋል፡፡

የባህል አልባሳቶቻችንን ለውጭው አለም ማስተዋወቅን ጨምሮ ለአገራችን የዲዛይን ባለሙያዎችና ለምርቶቻቸው አለም አቀፍ የገበያ ትስስርን ለመፍጠር አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል የተባለለት ይህ ፌስቲቫል በወላይታ ዞን አስተዳደርና በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ በከፍተኛ ደረጃ ትብበር የተደረገለት ከመሆኑም ባሻገር በቀጣይም በጋራ ተቀናጅተው እንደሚሰሩም ከደረሰን መግለጫ መረዳት ተችሏል፡፡

## 4 የምርጫ ቦርድ አመራሮች በቅርቡ ይሾማሉ

በጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ አቅራቢነት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የምርጫ ቦርድ ኃላፊ ሆነው ከተሾሙ በኋላ፤ ተቋሙ ቀጣዩ ሀገራዊ ምርጫን በተመለከተ ከወዲሁ በርካታ ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡ “ፓርቲው አልከሰመም” ከሚል ወቀሳና ውንጀላ አንስቶ የተለያዩ አዳዲስ የፓርቲ ምዝገባዎችን በመመልከት ሂደት ውስጥ ያለው ምርጫ ቦርድ፤ አራት የአመራር አባላት እንደሚሾሙለትም ተሰምቷል፡፡

እነዚህን አራት የቦርድ አመራሮችን የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የሚያፀድቅ ሲሆን አራቱን የቦርድ አዲስ ተሿሚዎችን የሚመርጥ አንድ ቡድን ደግሞ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካይነት ተዋቅሯል፡፡

በቅርቡ በፀደቀው አዲሱ የምርጫ ቦርድ አዋጅ መሰረት የቦርዱ ቀዳሚ ስራ ሕጋዊ መስመሮችን ላሟሉ ፖለቲካ ድርጅቶች የዕውቅና ምስክር ወረቀት መስጠትና ህጋዊነታቸውን ማረጋገጥ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ የምርጫ ቦርድ 9 ወራት የስራ አፈፃፀም ሪፖርትን በያዝነው ሳምንት አጋማሽ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባላት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ያቀረቡ ሲሆን፤ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የሕግ፣ ፍትህና ዲሞክራሲ ቋሚ ኮሚቴ ምርጫ ቦርድ ለ2012 ምርጫ እንዲዘጋጅ ማሳሰቢያ ሰጥቷል፡፡ የምርጫ ቦርድ ኃላፊ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በበኩላቸው የቦርድ አባላት አለመሟላት እንቅፋት እየፈጠረባቸው እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

# ግሎባል አልያንስ ለተፈናቃዮች ከ31 ሚሊዮን ብር በላይ አሰረከበ

## ‹‹ሁሉም ተመላሽ የዕርዳታው ተቋዳሽ ይደረግ››

### የጌዶኦ ተፈናቃዮች

ላለፉት አራት ወራት ያህል ከመኖሪያ ቀዬአቸው ተፈናቅለው የነበሩት የጌዶኦ ነዋሪዎች በተወሰነ መልኩም ቢሆን መንግስት ሁኔታዎችን በማመቻቸቱ ወደቀድሞ መኖሪያቸው መመለስ መጀመራቸውን ከስፍራው የደረሰን መረጃ ያመለክታል፡፡

በዚህና ባሳለፍነው ሳምንት በየቀኑ 10 መኪና ተፈናቃዮች ወደቀዬአቸው እየተመለሱ መሆኑን የጠቀሱት ምንጮቻችን ተጨማሪ የትራንስፖርት አቅርቦት አማራጭ ካልተፈለገ በቀር ሂደቱ ወራትን ሊፈጅ እንደሚችል ግምታቸውን ያስቀምጣሉ፡፡

መንግስት ለተመላሾች ጊዜያዊ ማረፊያዎችንና ዕለታዊ ዕርዳታዎችን ማመቻቸቱን አስቀድሞ የተናገረ ቢሆንም፤ ተመላሾቹ ግን በዕርዳታ አሰጣጡ ላይ አሁንም ቅሬታ እንዳላቸው እየገለፁ ነው፡፡ ዕርዳታው እየተሰጠ ያለው ለሁሉም ተወላጆች ሳይሆን ከዚያ ቀደም በቦታው ላይ ስለመኖራቸው የሚያረጋግጥ የይዞታ ማረጋገጫ ለሚያቀርቡና የመታወቂያ ወረቀት ላላቸው ብቻ በመሆኑ አሰራሩን እንቃወማለን፣ እየተደረገ ያለው መከፋፈልም ተገቢ አይደለም፣ ሁሉንም ተመላሽ በእኩል ደረጃ የዕርዳታው ተቋዳሽ ማድረግ ይገባቸዋል፣ የሚመለከታቸው አካላትም በቅርበት ጉዳዩን መከታተል አለባቸው ብለዋል፡፡

ተፈናቃዮቹ ወደቀዬአቸው መመለስ ቢጀምሩም አሁንም በዞኑ ያሉት ባለስልጣናት ከቀደመው ህገ - ወጥ ድርጊቶቻቸው እንዳልተቆጠቡና በቀርሳ ቢረዳ ቡሪሳ ቀበሌም ሊቀመንበሩ 2 ሰዎችን ያለምክንያት ማሰራቸውንም ምንጮቻችን ተናግረዋል፡፡ ሁሉም ተፈናቃይ ወደ ቀድሞ ቀዬው ተመልሶ ባልገባበት በዚህ ወቅት ሠዎችን ያለ ጥያቄና በገዛ ፈቃድ ማሰሩ እንደገና ችግሩን ለመቆስቆስ የሚደረግ ጥረት ይመስላል ያሉት ተፈናቃዮች የክልሉ መንግስት ችግር ፈጣሪ የተባሉትን ባለስልጣናት በተመለከተ ጥብቅ ክትትል በማድረግ ለህግ ሊያቀርባቸው ይገባል ሲሉ ሀሳባቸውን ሰንዝረዋል፡፡

በተለይም በመንግስት፣ በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ግለሰቦች የተለገሱ ዕርዳታዎች በተገቢው መንገድ ለተፈናቃዮቹ እየደረሱ እንዳልሆነና በአንድ አባወራ ቤተሰብ ውስጥ ለሚገኙ ከ10 እስከ 15 ለሚደርሱ የቤተሰብ አባላት እየተሰጠ ያለው ዕርዳታ ከአንድ ጣሳ ያልተፈጨ በቆሎ የማይበልጥ መሆኑና እሱንም ለማግኘት የሚችሉት ከ20 ዓመት በፊት በስፍራው የነበሩና የመታወቂያ ወረቀት ያላቸው ናቸው በሚል እየተሰራ ያለውን የዕርዳታ አሰጣጥ መንግስት ጣልቃ ገብቶ ሊያስቆመውና ሁሉም ተፈናቃይ ያለውን ዕኩል የመካፈል መብቱ እንዲጠበቅለት መደረግ አለበት በማለት የተፈናቃዮቹ ተወካይ የኮሚቴ አባላት ይገልፃሉ፡፡ ‹‹ከእርዳታ ስርጭት ጉድለቱ የተነሳም ወደቀዬአቸው ተመልሰው የነበሩ ተፈናቃዮች በድጋሚ ወደነበሩበት ስደት እየተመለሱ ስለሆነ በጉዳዩ ላይ የፌደራል መንግስት እጁን አስገብቶ ዘላቂ የሆነ መፍትሄን ሊያበጅ ይገባል›› በማለትም ሀሳባቸውን ሠንዝረዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ለጌድዮና ጉጂ ተፈናቃዮች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት የሚውል ከ31 ሚሊዮን ብር በላይ በግሎባል አልያንስ አማካይነት መሰብሰቡ ይፋ ተደርጓል፡፡ ግሎባል አልያንስ ለጌድዮና ለጉጂ ተፈናቃዮች ካደረገው ዕርዳታ ባሻገር ባለፉት ስድስት ዓመታት ድርጅቱ በሀገር ውስጥና በባህር ማዶ የነበረው እንቅስቃሴ የሚያስቃኘውን ሰፊ ዘገባችንን በገፅ 14 እና 15 ላይ ይመልከቱ፡፡

# ድሬድዋ በሰርግ ላይ የተነሳው አለመግባባት ወደ ብሔርና ሐይማኖት ግጭት ተሻገረ

እሁድ ግንቦት 4ቀን 2011 ዓ.ም በድሬድዋ ከተማ አንድ የክርስቲያን ሰርግ ስነ ስርዓትን ተከትሎ በጥቂት ሰዎች መሀል የተፈጠረው ግጭትና አለመግባባት ወደ ብሔርና ሐይማኖት ግጭት ከፍ ባለ ሁኔታ በፍጥነት ቢዛመትም፣ መከላከያ ሰራዊት በቦታው ገብቶ በወሰደው የማረጋጋት ዕርምጃ ችግሩ ሳይባባስ በፍጥነት ሊቀጭ መቻሉን ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰን ዜና አስታውቋል፡፡

በስፍራው የሚገኘው የግዮን መጽሔት ሪፖርተር እንዳደረሰን ከሆነ በተጠቀሰው ቀን በተለምዶ ሳቢያን ተብሎ በሚጠራው አካባቢ "ገንደ ተስፋ" በሚባለው የታችኛው ሰፈር ክፍል፣ ተወልደው ያደጉና ነዋሪ የሆኑ የሁለት ሙሽሮች የጋብቻ ስነ ስርዓት ይካሄድ ነበር፡፡ ሙሽሮቹ ሠርጉን ለማከናወን ወደ አካባቢው በሚሄዱበት ወቅት በአከባበቢ የሚሰሩ ባጃጆች መንገድ ዘግተው በመቆማቸው፣ "አሳልፉን፣ ቆዩ" በሚል በተፈጠረ ግብግብ፤ የተወሰኑ ወጣቶች ከሁለቱም በኩል ግጭት ውስጥ ቢገቡም፤ ነገሩ ዕልባት ካገኘ በኋላ ሰርገኞቹ ወደ ፕሮግራማቸው በመሄድ የጋብቻ ስነ ስርዓታቸውን ለመፈፀም ችለዋል፡፡

ይህ ይሁን እንጂ አስቀድሞ ለተፈጠረው ውዝግብ መንስኤ የሆኑ ናቸው የተባሉ ወጣቶች 12 ሰዓት ላይ ወደ ሰርጉ ቤት በመሄድ የረመዳን ፆምን አፍጥረው፣ በስነ ስርዓቱ ተመግበው ከወጡ በኋላ፤ ዕድምተኛው ባለበት ሰርግ ቤቱን በድንጋይ በመደብደባቸው ከፍተኛ የሆነ ግጭት ሊፈጠር ችሏል፡፡ በዕለቱ በእዚህ ሰርግ ላይ ግጭቱ በግልፅ ይስተዋል እንጂ፤ በአካባቢው ከዚህ ቀደም የክርስቲያን ሰርጎች፣ የክርስትናና የሐውልት ምርቃትን የመሰሉ ፕሮግራሞች በነፃነት ማካሄዱ አዳጋች ስለሚሆን፤ አራትና አምስት ፖሊሶች አስጠብቆና አበል ከፍሎ ግብዣዎችን ማስፈጸም የተለመደ አሰራር መሆኑን የአከባቢው ነዋሪዎች ይናገራሉ፡፡

ሳቢያን ውስጥ ከሚገኙት ሁለት መንደሮች "መስቀለኛ" በሚባለው አካባቢ (አስፋልት ዳር ያለ ቦታ ነው) ክርስቲያኖች ሲበዙ፤ "ገንደ ተስፋ" በተሰኘው ወደ ውስጥ ገባ ብሎ በሚገኘው ሌላ መንደር ደግሞ የኦሮሞ ሙስሊሞች በስፋት እንደሚኖሩ የጠቆመው ሪፖርተራችን፤ በዕለተ ዕሁድ ከታችኛው የሰርግ ሰፈር የተነሳው ግጭት ሰኞ ዕለት ወደ ሁለቱም ቦታዎች በመዛመት፣ ወደለየለት የብሔር ግጭት በመዛመቱ ት/ቤቶች ተዘግተው ውለዋል፡፡

የተፈጠረውን ግጭት ተከትሎ በክልሉ የመከላከያ ኃይል ከፖሊስና ከከንቲባው ቢሮ በተውጣጡ ኃላፊዎች አማካይነት፤ የሁለቱን አካባቢ ነዋሪዎች በተናጠል የማወያየትና ሕብረተሰቡን የማነጋገር ስራ የተካሄደ ሲሆን፤ ሕብረተሰቡም በችግሮቹ ዙሪያ መፍትሄ ናቸው ያለችውን ሀሳቦች አቅርቧል፡፡

የድሬድዋ ፖሊስ አደረጃጀት ብሔርን ተዋፅኦ ባደረገ መልኩ 40/20 በሚለው ሲስተም መሆኑ፣ በዕለቱ ግጭቶች ሲነሱ ፖሊሶች ፀቡን ከማስቆም ይልቅ ወደ ብሔርተኝነት ስሜት በማጋደል ያልተገቡ እንቅስቃሴዎችን ማድረጋቸው፤ መከላከያ በፍጥነት ባይደርስ ኖሮ ችግሩ የከፋ ሊሆን እንደሚችል የገለፁት ነዋሪዎች፣ በተወለዱበትና ባደጉበት አከባቢ ወንድሞቻችን ከሚሏቸው ወገኖቻቸው ደስታ ቸውን የሚያደፈርስ ድርጊት መፈፀሙ በእጅጉ እንዳሳዘናቸው መግለፃቸው ተሰምቷል፡፡

## የአስተዳደር ወሰን እና ማንነት ጉዳዮች ኮሚሽነሮች ሹመት በም/ቤት ፀደቀ

ግንቦት 8 ቀን 2011 ዓ.ም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የአስተዳደር ወሰን እና የማንነት ጉዳዮች ኮሚሽን ኮሚሽነር እና ምክትል ኮሚሽነር ሹመትን አፅድቋል፡፡

ም/ቤቱ በዕለቱ ባካሄደው 4ኛ ዓመት የስራ ዘመን 39ኛ መደበኛ ስብሰባ በጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ የቀረበለት የአስተዳደር ወሰን እና የማንነት ጉዳዮች ኮሚሽን ኮሚሽነር እና ምክትል ኮሚሽነር ሹመትን በ25 ተቃውሞና በአብላጫ ድምፅ ማፅደቁ ታውቋል፡፡

በተጨማሪም ምክር ቤቱ የዕርቀ ሰላም ኮሚሽን ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ሹመቶችን ያፀደቀ ሲሆን፤ በዚህም መሰረት ካርዲናል ብርሃነ ኢየሱስ ሱራፌል ሊቀ ጳጳሳት ዘካቶሊካውያን የኮሚሽኑ ሰብሳቢ፣ ወ/ሮ የትነበርሽ ንጉሴ ምክትል የኮሚሽኑ ሰብሳቢ በመሆን ተመርጠዋል፡፡ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የእርቀ ሰላም ኮሚሽኖቹን ሹመት በአስር ድምፀ ተአቅቦና አራት ተቃውሞ በአብላጫ ድምፅ አፅድቆታል፡፡

## አንቀጽ 39 ፊልም ዛሬና ነገ ይመረቃል

በማክቤል ፊልም ፕሮዳክሽን ተሰርቶ በሠላም ፊልም ፕሮዳክሽን የቀረበው "አንቀፅ" 39 ፊልም በሁሉም ሲኒማ ቤቶች ግንቦት 10 እና 11 ቀን 2011 ዓ/ም ይመረቃል፡፡

ተወዳጆቹ ወጣት ተዋንያን ካሳሁን ፍስሃ (ማንዴላ) እና ቃልኪዳን ጥበቡ የተጣመሩበት አንቀፅ 39 ፊልም ደራሲና አዘጋጅ ሐብታሙ ዳኘው የዝና ሲሆን፣ ስመኝ ሚደቅሳ በረ/አዘጋጅነት ተሳትፋበታለች፡፡

"ህጉን መሻር ባንችል እንኳን ለአብሮነታችን ዋጋ ተከፍሏል" የሚል ዕሳቤን ያነገበው አንቀፅ 39 ፊልም በኢትዮጵያ ወቅታዊና ነባራዊ ሁኔታዎች ላይ የሚያጠነጥን እንደሆነም ተነግሯል፡፡

## የታሪክ መማሪያ መፅሐፍ፣ ክለሳ ጥናት ተቋረጠ

የትርክት ችግር አለበት የሚባለው የኢትዮጵያ ታሪክ ትምህርት መጽሐፍ እንዲከለስ በትምህርት ሚኒስቴር ትዕዛዝ ተሰጥቶበት የነበረ ቢሆንም፤ በልሂቃን አለመግባባት ሳቢያ የክለሳው ጥናት ሊቆም መቻሉ ተሰምቷል፡፡

ባለፉት ሰባት ዓመታት "የተመረጡ የፖለቲካ ትርክቶች ጎልተውበታል" በማለት፣ የኢትዮጵያ የታሪክ መፃኅፍትን ለመከለስ ጥረት ሲደረግ ቢቆይም፤ በጉዳዩ ላይ የብሔር ልሂቃን ባለመስማማታቸው ክለሳው ሊቋረጥ እንደቻለ ነው የተነገረው፡፡ የትምህርት ሚኒስቴር የስርዓተ ትምህርትና ትግበራ ዳይሬክተር፤ አቶ አሸቱ አስፋውን ጠቅሶ፣ ረቡዕ ግንቦት 7 ቀን 2011 ዓ.ም በዜና ዕወጃው መረጃውን ፋና ይፋ ቢያደርግም፤ በዚሁ ቀን ስማቸው የተጠቀሰው ኃላፊ፤ ምሽት ላይ ለቢቢሲ በጉዳዩ ላይ ሌላ ማብራሪያ ሲሰጡ እርስ በርሱ በሚጋጭ መልኩ የፋና ዘገባ ትክክል እንዳልሆነና በታሪክ ትምህርት ላይ የተለየ ክለሳ እየተደረገ እንዳልሆነም ጭምር ገልፀዋል፡፡

ሌሎች ትምህርቶች ሁልጊዜ ማስተካከያና እርምት እየተደረገባቸው ለተማሪው እንደሚቀርቡት ሁሉ የታሪክ ትምህርትም የተወሰነ ማስተካከያ ሊደረግበት አንዳንድ እንቅስቃሴዎች ተጀምረው የነበረ ቢሆንም፤ ጥናቱ ለረዥም ጊዜ ተቋርጦ እንደቆየና በቅርቡ ግን የስርዓተ ትምህርት ክለሳ ፕሮግራም ላይ በመድረሱ፤ የታሪክን ትምህርት በተለየ ሁኔታ ከማየት እንደሌሎቹ ትምህርቶች አንድ ላይ በተገቢው መንገድ እንየው በሚል ሀሳብ ለጊዜው እንደቆመ እንጂ ተሰረዘ ወይም ተቋረጠ እንደ ማይባል ኃላፊው ቢናገሩም፣ አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ፕ/ር ተሰማ ተአ ግን በተቃራኒው የታሪክን መጽሐፉን የማስተካከል ስራ እየተሰራ እንደነበር ለቢቢሲ ገልፀዋል፡፡

# ወንጀለኞችን ከመያዝ ባሻገር፤ የሕግ ክፍተቶችንም መሙላት ያስፈልጋል!

በተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች ለውጡን ለማጠልሸት በማድረጉ እንቅስቃሴዎችና ሁከቶች ታጅበው ጥቂት የማይባሉ ዜጎች ሕይወታቸውን ከማጣታቸው ባሻገር፤ ለስደትና ለመፈናቀል በተዳረጉበት አስራ ሁለት ወራት ውስጥ ዋና መዲናይቱ አዲስ አበባ አንፃራዊ በሆነ መልኩ በተረጋጋ ሰላምና ፀጥታ ውስጥ ሰነባብታለች፡፡

ይሁን እንጂ አዲስ አበባ በሀገሪቱ ውስጥ ብልጭ ያለውን ፖለቲካዊ ለውጥ ተከትሎ ከወራት በፊት አድማሳቸውን ያሰፉ፣ ሂደትና ስልታቸውን በየግዜው የሚቀያይሩ፣ የተጠናከሩ ዝርፊያዎች የተከናወኑባትና አሁንም እየተፈፀመባት ያለች ከተማ ሆናለች፡፡ ከአስር ወር በፊት ከተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች የተገኘውን ፖለቲካዊ ድልና አዲስ የአመራር አቅጣጫ ተከትሎ፤ ብዛት ያላቸው ዕስረኞች (ከፖለቲከኛ እስረኞች ውጪ ማለታችን ነው) መፈታታቸውና በዚህ ይቅርታና ምህረት ውስጥም በርካታ በወንጀል ተግባር ላይ የተሰማሩ ግለሰቦች መኖራቸውን ተከትሎ ከተለያየ አቅጣጫ ፍቺው ጊዜውን ጠብቆ ችግር ሊፈጥር እንደሚቻል ሲነገር ቆይቷል፡፡

በከተማዋ የተጠናከረ የሌብነትና የተደራጀ ዝርፊያ ተግባር መጠናከሩን ተከትሎ ጉዳዩ አሳሳቢ ደረጃ መድረሱን የተገነዘበው የአዲስ አበባ ፖሊስ፤ ከወራት በፊት ከየማረሚያ ቤቶች በምህረት የተለቀቁ ግለሰቦች ዝርዝር በቂ መረጃ እንዲደርሰው ጥያቄ አቅርቦ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ፖሊስ በከተማዋ ውስጥ በቡድን እየተደራጁ ዝርፊያ የሚያደርጉት ኃይሎች ቀደምት ሙያዊ ልምድ ያላቸውና በዘርፉ ብዙ ወንጀሎችን የፈፀሙ ግለሰቦች እንዳሉ መጠርጠሩን ተከትሎ ረዘም ላለ ጊዜ ሲያደርግ በቆየው ክትትል መሰረት፤ ባሳለፍነው ሳምንት መገባደጃ በዋና ከተማዋ ነዋሪዎች ላይ ዝርፊያ ሲያካሄዱ፣ ወንጀል ሲፈፅሙ ነበር ያላቸውን ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ስር አውሏል፡፡

የተለያዩ የቤት መኪኖችን በመጠቀም በተጠና ስልት፣ ከሞባይል ስርቆሽ እስከ ሙሉ ዘረፋ፣ በሚኒባስ፣ ታክሲዎች አማካይነት ከሚካሄደው ‹‹ሿሿ›› ከተሰኘው የስርቆት አይነት፤ በዚህ ወቅት መዲናዋን በስርቆትም፣ በትራፊክ አደጋም ጭምር እስከሚያሰቃይዋት የሞተር ሳይክል ዝርፊያዎች ድረስ፤ አዲስ አበባ ላይ በተለይም ላለፉት አስራ አንድ ወራት በርካታ የቡድን ዝርፊያዎች ተፈፅመዋል፡፡

አምባገነኑ ስርዓት ሕብረተሰቡን እርስ በርስ ለመነጣጠልና በሀሳብ የሚቃረኑትን ለማስወገድ ጭምር "ኮሚኒቲንግ ፖሊሲ" (የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አገልግሎት) ብሎ ቢያቋቁምም፤ ሕዝብና የፖሊስ አካላቱ በእጅጉ የተራራቁ በመሆናቸው፣ በየመንደሩ እንደ ባስ ስቴሽን የተቋቋሙት ኮሚኒቲንግ ፖሊሲዎች ወንጀለኛን አድነው ከመያዝና ለይተው ከማውጣት ይልቅ "እከሌ ኢህአዴግን ይቃወማል" በሚል የካድሬ አገልግሎት ሲፈፅሙ በመክረማቸው፣ በመዲናይቱ የተለጠጠ የወንጀል ተግባር እንዲፈፀም በር ከፍቷል፡፡

ፖሊስ ከሕግ አስከባሪነቱ በተቃራኒ መልኩ፣ የሥርዓቱ አፍቃሪና ቀጥተኛ አገልጋይ ሆኖ ለአመታት መስራቱ፤ ቀደም ባሉት ዓመታት ወንጀለኞችን ለማጋለጥ ሕብረተሱ ከፀጥታ አካላት ጋር እጅና ጓንት ሆኖ የመስራቱን ጉዳይ አሻክሮት በመቆየቱ፣ ሕግ አስፈፃሚዎችን ከመረጃም ከህዝብም የተነጠሉ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ በጣቢያዎች ውስጥ ያለውና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የመጣው ወንጀለኛን የመያዝና ምስክር የማቅረብ ሂደትን ተከትሎ የተተገበረው አሰራር፣ ፖሊስና መርማሪ፣እንዲሁም ዓቃቤ ህግ እርስ በርስ ሳይግባቡ ክሱ ውድቅ የሚደረግበት አሰራር፤ ህብረተሰቡ በሕግ ላይ ዕምነት እንዲያጣ ከማስቻሉም በላይ፣ ከተጠቀሱት ተቋማት ጋር ወንጀለኛን አሳልፎ በመስጠት፣ በመጠቆምና በመመስከር ተግባር ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዳይሆን ያስገድደዋል፡፡

በመጨረሻም ሰሞኑን የአዲስ አበባ ፖሊስ በተጠርጣሪዎቹ ላይ የወሰደው ዕርምጃ የሚደገፍ ከመሆኑ ባሻገር፤ አሁንም በተለያዩ የከተማይቱ ወረዳዎች ውስጥ በመሰል ተግባር ላይ የተሰማሩ ወንጀለኞችን አድኖ መያዝና ለፍርድ ማቅረብ የሚገባው መሆኑን እየገለፅን ችግሩን ከምንጩ ለማድረቅና ዘለቄታዊ መፍትሄ ለማበጀት ከታሰበ፤ የሚታዩትን አንዳንድ የህግ ክፍተቶች እንዲሁም ፖሊስ ከሕብረተሰቡ ጋር እንዲህ ባለ ሰፊ የሆነ የመረጃ ዕጦትና ልዩነት የተራራቀበትን ስፋት ማጥበብና ለአስተማማኝ ሰላም በጋራ መስራት እንደሚገባ ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡


**ግዮን መጽሔት**
**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**
**በየሳምንቱ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት**

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

**ዋና አዘጋጅ**
ሮቤል ምትኩ
አድራሻ፡- የካ ክ/ከተማ
ወረዳ 2 የቤት ቁጥር 475

**ከፍተኛ አዘጋጅ**
ብሩክ መኮንን
መለስ ሽኔ
ፍቅርተ ተሾመ

**ተባባሪ ዘጋቢያችን**
ቶማስ አያሌው(ከአሜሪካ)

**አምደኞች**
ወንድሙ ነጋሽ(ኢ/ር ከለንደን)
ተረፈ ወርቁ
ሁሴን ከድር

**ክርኤቲቭ ዲዛይን**
ፍፁም ንጉሴ

**ጸሐፊ**
ሠላም ግርማ


**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09
የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 2ተኛ
ፎቅ ቢሮ ቁ. 207
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 22 76 61
+251 912 165606
+251 118 12 2333
ኢ-ሜይል፡
enqu2013@ gmail.com
Ghion2011meg@gmail.com
**Facebook**
Gihon-meg Fekadu
www. facebook.com/enqu2013



በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ ማተሚያ ቤቱን አይመለከትም



**አታሚ**
ቴዎድሮስ ገብሩ ማተሚያ ቤት ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ
ወረዳ 10 የቤ.ቁ. 066/ሀ
0911223335/ 0911420506



መሳይ ከበደ (ፕሮፌሰር)

# የጽንፈኝነት አመጣጥ በኢትዮጵያ

በተለይ ለግዮን

ይህ ጽሁፍ በ60ዎችና በ70ዎች (እ.ኤ.አ)የገነነውን የኢትዮጵያ የተማሪዎችና ምሁራን ንቅናቄ ያጠናውን፣ በእንግሊዘኛ ተጽፎ በአሜሪካን አገር የታተመው መጽሓፌን (Radicalism and Cultural Dislocation in Ethiopia, 1960-1974)፣ ፍሬ ነገር በጣም ባጭሩ ያቀርባል፡፡ የተማሪዎችና ምሁራን ንቅናቄ በኢትዮጵያ ለተከሰተው ማህበራዊ አመጽና የንጉሣዊ አገዛዝ መደምሰስ ዋና ምክንያት እንደሆነ በሰፊው ይታመናል፡፡ ይህ ጽሁፍ አንድ አነስተኛ የሕብረተሰብ ክፍል ይህን የሚያክል እጅግ ከፍተኛ ተጽኖ ያለው ሚና እንዴት መጫወት ቻለ? የሚለውን ጥያቄ አያነሳም፡፡ ይልቁንም የሚመረምረው የትኞቹ ምክንያቶች የኢትዮጵያ ተማሪዎችንና ምሁራንን ቀስ በቀስ አክራሪ ጎዳና እንዲይዙ አደረጋቸው? የሚለውን ጥያቄ ነው፡፡ ከሁሉ ጎላ ብሎ የወጣው ንድፈሐሳብ የጽንፈኝነት ዋናው ምክንያት በኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩት በጣም አስከፊ ማህበራዊ ችግሮች ናቸው ይላል፡፡ የቀረበው ጽሁፍ የማህበራዊ ችግሮችን ተጽዕኖም ይቀበላል፡፡ ሆኖም የአክራሪነት ዋናው ምንጭ በቅድሚያ የተከሰተው የአስተሳሰብ መናጋት ነው በማለት ይከራከራል፡፡

## የተማሪው ክፍል የመሪነት ቦታ

ምንም እንኳን በአብዛኛው ተመራማሪ ዘንድ የተማሪዎችና የምሁራን ንቅናቄ በ1974 (እ.ኤ.አ) በፈነዳው አብዮት ውስጥ መሪ ሚና እንደነበራቸው ቢቀበልም፤ ንቅናቄው ለምን አክራሪ ሆነ የሚለው ጥያቄ ሲነሳ ግን ብዙ ስምምነት አይታይበትም፡፡ ጽንፈኝነት የመጣው ከኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ነው የሚሉ ተመራማሪዎች ንቅናቄውን የሚያዩት እንደ አቀጣጣይ ኃይል ነው፡፡ ለተነሳው ሕዝባዊ አመጽ የተማሪው ንቅናቄ አቀጣጣይ ነበር ማለት የለውጥ ፍላጎት በሕዝቡ ውስጥ አስቀድሞ ነበር፣ የሚጠበቀው የሚለኩሰው ክብሪት ነበር ማለት ነው፡፡ በሌላ አባባል፣ የኃይለ ሥላሴ መንግሥትን የጣለው ዋናው ምክንያት ተንሰራፍተው የነበሩት ከባድ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ናቸው፡፡ ንጉሡ በጊዜው እጅግ አስፈላጊ የነበሩ ለውጦችን ባለመቀበላቸው ነው አብዮት የመጣው፡፡ ከችግሮቹ ውስጥ ዋናዎቹ የሚከተሉት ነበሩ፤ 1) የገበሬው አስከፊ ኑሮ፣ በተለይም የጭሰኛ ሥርዓት ያስከተለው ገደብ የለሽ ብዝበዛ፤ 2) የአማራ ልሂቃን የበላይነት የቀሰቀሳቸው ዘውጋዊ ተቃውሞዎች፣ በተለይም የተነሱት ክልላዊና ተገንጣይ እንቅስቃሴዎች፣ ለምሳሌ በኤርትራ የተነሳው የመሳሪያ ትግል፤ 3) በየከተማው ሰፍኖ የነበረው ሰፊ ድህነትና ሥራ አጥነት፤ 4) የመቃወምና የመደራጀት መብቶች መከልከል፡፡

እዚህ ላይ የሚነሳ አንድ ወሳኝ ጥያቄ አለ፡፡ ማህበራዊ ችግሮች ለሕዝብ መነሳሳትና ለውጥ መፈለግ ምክንያት እንደነበሩ የማይካድ ሃቅ ነው፡፡ ነገር ግን ለውጥ መፈለግና ለፍላጎቱ አክራሪ አቅጣጫ መቀየስ የተለያዩ ነገሮች ናቸው፡፡ ጥያቄው ለምን ለውጥ መጣ? ሳይሆን ለምን ለውጡ ወደ ሥርነቀል አብዮት ሄደ? ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ መልስ ሲፈለግ ነው የተማሪው ክፍል ንቅናቄ ልዩ ሚና ጎልቶ ብቅ የሚለው፡፡

## የጽንፈኝነት መንስኤዎች

የጽንፈኝነትን አመጣጥ ለማወቅ፣ ብዙ ተመራማሪዎች የኃይለ ሥላሴ መንግሥት አሠራር ላይ ያተኩራሉ፡፡ ብዙዎቹም የሚስማሙት በሚቀጥሉት ነጥቦች ላይ ነው፡፡

### 1) የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ክስረት

በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ያገኘው መላምት፣ አስፈላጊ ለውጦች አለመደረግ ከኃይለ ሥላሴ መንግሥት ኢ-ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ ጋር ሲዳመር የተማሪው ክፍል ወደ አክራሪነት ለምን እንዳዘነበለ ያብራራል ይላል፡፡ የዴሞክራሲ አለመኖር ብቻ ሳይሆን ተቃዋሚ ፓርቲ ጨርሶ በተከለከለበት ሁኔታ ውስጥ የተማሪው ክፍል ያለው ብቸኛ መንገድ ወደ አክራሪነት መጓዝ ብቻ ነበር፡፡ እርግጥ ነው፣ በንጉሡ ጊዜ ተማሪው ማህበር የመመሥረትና የመናገር ነጻነት ነበረው፡፡ ነገር ግን ነጻነቱ በዩኒቨርሲቲ ደረጃና ግቢ ብቻ የተወሰነ ስለነበር ወደ ሕዝብ አልዘመተም፡፡ ቅሬታን ለሕዝብ ማሰማትና በፓርቲ የመደራጀት መብት ሲከለከል በድብቅ መሰባሰብና መደራጀትን ያስከትላል፡፡ ይህ ደግሞ የሴራ መንፈስ ከመፍጠሩ በላይ ላለው ሥርአት ተጻራሪ ወደ ሆነ አመለካከት ይገፋፋል፡፡ በድብቅ መደራጀት ካለው የፖለቲካ ሥርአት የሚለይ ብቻ ሳይሆን ከሥርአቱ ጋር ምንም ድልድይ ወይም ውይይት እንዳይኖር ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም የፖለቲካ አፈና እጅግ ሲጠነክር መካከለኛ አመለካከት ያላቸው ተማሪዎችና ምሁራን ከትግሉ ይወጣሉ ወይም ተደማጭነት ያጣሉ፡፡ በአንጻሩ ደግሞ አክራሪ የሆነው ቡድን ተደማጭ ከመሆኑ ባሻገር የመሪነት ቦታ ይይዛል፡፡ ምክንያቱ የሚታየው በተጨባጭ ሁኔታ ጽንፈኛውን ቡድን እውነት ተናጋሪ፣ ሌላውን ግን ለዘብተኛ ከዚያም አልፎ የመንግሥቱ ተባባሪ ያስመስላል፡፡ ያለው መንግሥት ለማንኛውም የለውጥ ጥያቄ የሚሰጠው መልስ ሁሌም እስራትና ግድያ ከሆነ ከተማሪው ክፍል ጋር ምንም ዐይነት ድልድይ አይኖርም፤ ይህ ደግሞ በሁለቱ መካከል ፍጹም ተቃርኖአዊ ግንኙነት ብቻ እንዲዳብር ያደርጋል፡፡

> ይህ አገር የማቅናት ተልዕኮ ከምዕራባዊ ቅኝ አገዛዝ የሚለየው በቅርጽ እንጂ በይዘት አይደለም፤ ምክንያቱም የሁለቱም ዐላማ አገር ማሰልጠንና ከኋላቀርነት ወደ ሥልጣኔ መውሰድ ነው፡፡

### 2) የችግሮች መጠንና ዐይነት

አንድ መንግሥት ለማህበራዊ ችግሮች በጊዜው አስፈላጊ መፍትሄዎችን ካላበጀ የችግሮቹ መጠን መጨመር ብቻ ሳይሆን በዓይነትም ይለወጣል፡፡ ችግሮች የተወሰነ ደረጃ ላይ ሲደርሱ ያለው መንግሥት እራሱን ለማዳን የሚያስችለውን ተመጣጣኝ መፍትሄ ማምጣት ያቅተዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለውጥን የሚፈልገው ክፍል ወደ ሥርነቀል ለውጥ ያዘነብላል፡፡ ምክንያቱም የችግሩ መጠን በቀላሉ ወይም በጥገና የሚፈታ አይመስልምና፡፡ የችግሩ መጠንና ዐይነት የመንግሥትን መወገድና ሥርነቀል ለውጥን የሚጠይቅ ስለሚመስል የተማሪው ክፍል ጽንፈኝነትን እንደ ብቸኛ መፍትሄ ለመቀበል ይገደዳል፡፡

## የርዮተዓለም ተቀዳሚ ቦታ

በእኔ አስተሳሰብ፣ የንጉሣዊው መንግሥት ፖለቲካዊ ጭቆናና ያስከተላቸው የችግሮች መከማቸት የተማሪውን ክፍል ወደ ጽንፈኝነት ወሰደው የሚለው አመለካከት የሚዘነጋው፤ ▶

የተጠቀሱት ምክንያቶች በራሳቸው ብቻ በቂ እንዳልሆኑ ነው፡፡ በሌላ አባባል፣ ተማሪዎችና ምሁራን በቅድሚያ የአክራሪነትን አቋም በመያዛቸው ነው ለችግሮቹ ከሥርነቀል አብዮት በስተቀር ሌላ መልስ የለም ብለው የተነሱት፡፡ ይህ ቀደም ያለ እምነት የነበረውን ሥርአት በማጥላላትና የብዙሐኑንና የወታደራዊ ክፍሉን ፖለቲካዊ ንቃት በመቅረጽ ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ ከሁሉም በላይ ለችግሮቹ ብቸኛ መፍትሔ ሶሺያሊዝም ነው የሚለውን እምነት እንዲስፋፋ አድርጓል፡፡ በመሆኑም የተማሪው ክፍል ንቅናቄ አቀጣጣይ ብቻ ሳይሆን የለውጡን አቅጣጫ የቀየሰ የአብዮቱ መሪ ነበር፡፡ የተዋቀረ ፖለቲካ ፓርቲ በሌለበት ሁኔታ ውስጥ ፖለቲካ ፓርቲን በመወከል የመሪ ሚና ተጫውቷል፡፡

በተለይ የደርግ አመሰራረትና አብዮታዊ አመለካከትን መላበስ የተማሪውን ክፍል መሪነት ሚና አጉልተው ያሳያሉ፡፡ ደርግ የመሪነቱን ቦታ በመጨረሻ ቢወስድም ሃቁ ግን አመለካከቱን ያገኘው የተማሪው ክፍል ካሰራጨው የማርክሳዊ ሌኒናዊ ንድፈ ሐሳብ ነው፡፡ ደርግ ለማርክሳዊና ሌኒናዊ አመለካከት የነበረው ታማኝነት አጠራጣሪ ነበር ብንልም፤ የማይካደው ሐቅ ግን በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነትና ሕጋዊነትን ለማግኘት እንደተጠቀመበት ነው፡፡ ቅድሚያ መሰጠት ያለበት ለርዮተዓለማዊ ለውጥ ነው የሚለው አቋሜ የሚከተሉትን የመከራከሪያ ነጥቦች ያቀርባል፡፡

1) በተማሪው ክፍል ንቅናቄ ውስጥ ጎላ ያለ ድርሻ የነበራቸው፤ ከመኳንንት፣ ከከፍተኛ ወታደራዊ ማዕረግና ከከበርቴ የሕብረተሰብ ክፍሎች የመጡ ተማሪዎችና ምሁራን መሆናቸው የታወቀ ነው፡፡ ታዲያ እነዚህ በተጠቀሱት ማህበራዊ ችግሮች ከተጠቀሙ ክፍሎች የተወለዱ ተማሪዎችና ምሁራን ለምን አብዮት ፈለጉ፣ ለምን ሥርነቀል ለውጥ ውስጥ በመሪነት ተሳተፉ? ከማሻሻል ፍላጎት አልፈው ለምን የራሳቸውን መደብና ጥቅም በመክዳት ለሥርነቀል አብዮት ተሰለፉ? መልሱ የማህበራዊ ችግሮች መብዛትና መክረር ሊሆን አይችልም፡፡

2) የአማራ ገዢ መደብ የበላይነት ያስከተለው የዘውግ ጭቆና የአገሪቱ ዐቢይ ችግር ስለሆነ ለአብዮታዊ ሂደት መንስኤ ሆነ የሚለው አስተያየት የማያብራራው፤ ለምን የአማራ ተማሪዎችና ምሁራን በብዛትና በመሪነት ደረጃ ለአብዮቱ ተሰለፉ የሚለውን ጥያቄ ነው፡፡ የራሳችውን የዘውግ የበላይነት ለምንና እንዴት ከዱ? እዚህ ላይ ማስተዋል የሚያስፈልገው ያለ አማራ ተማሪዎችና ምሁራን የኢትዮጵያ የተማሪው ክፍል ንቅናቄ ተሰሚነትም ኃይልም ሊኖረው አይችልም ነበር፡፡ እንደሚታየው፣ በመደባዊም ሆነ በዘውጋዊ ትንታኔ፣ የተማሪውን ክፍል አክራሪ መሆን ለማብራራት አስቸጋሪ ነው፡፡

3) ከዚህም አልፎ መመልከት ያለብን፤ ካለሥርነቀል አብዮት የማይፈቱ የመሰሉት ችግሮች በቅድሚያ የተማሪው ክፈል የተቀበለው የርዮተዓለማዊ ለውጥ የሰጣቸው መልክ እንደሆነ ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የሥርነቀል አብዮት አስፈላጊነት በቅድሚያ ስለታመነበት የማሻሻል ወይም ተሃድሶ (reform) ፖለቲካዊ አቋም ተንቋሸሸ፣ እንደ አማራጭም እንዳይወሰድ ተደረገ፡፡ ከሌሊናዊ ሶሺያሊዝም ውጪ ያለ አመለካክት ሁሉ አድሓሪ፣ ወይ ወግ አጥባቂ፣ ወይ ጠጋኝ ተብሎ ተጥላላ፡፡ ከሁሉም በላይ የአገሪቱ ችግሮች በማርክሳዊ ሌኒናዊ መነጽርና ትንታኔ ስለታዩ በተሃድሶ ሳይሆን በሥርነቀል አብዮት ብቻ የመፈታት ገጽታ ተሰጣቸው፡፡ አንድን ሰው በሽታ ካጋባንበት በኋላ ብንጠይቀው አሞኛል እንደሚል ሁሉ፣ የተማሪው ጽንፈኛ ቡድንም የአክራሪነት በሽታን ከረጨ በኋላ ካለሥርነቀል አብዮት ሌላ መፍትሄ የለም የሚሉ ብዙ ተከታዮችን አፈራ፡፡ ለዚህ ውጤት ዋናው ምንጭ ከማርክሳዊ ሌኒናዊነት የተወሰደው የተቃርኖ ንድፈ ሐሳብ ነው፡፡ የነገሮች ባህሪያትና የማህበራዊ ክፍሎች ግንኙነቶች በሙሉ የተመሰረቱት ቅራኔ ላይ ነው ካልን ሊስማሙ የማይችሉ ጠላቶች እናደርጋቸዋለን፡፡ ይህ አመለካከት አክራሪነትን ከመውለድ ውጪ ሌላ መንገድ የለውም፡፡ ከመደብ ትግል ወደ ዘውግ ትግልና የመገንጠል መብት የወሰደን ይኸው ከማርክሳዊ ሌኒናዊ ፍልስፍና የተወረሰው የተቃርኖ አመለካከት ነው፡፡

4) ለርዕዮተአለም ቅድሚያ እንድንሰጥ የሚያደርገን ሌላው ማስረጃ ለኢትዮጵያ ችግሮች እንደ መፍትሄ የቀረበው፣ ማለትም ሶሺያሊዝም፣ ችግሮችን ከማቃለል ይልቅ ማባባሱ ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው በጥናት በተደገፈ ምርምር ሶሺያሊዝም በእርግጥም ለአገሪቱ ይበጃል ተብሎ ሳይሆን በቅድሚያ የተማሪው ክፍል የተቀበለው ጭፍን እምነት መሆኑን ነው፡፡ ከሶሺያሊዝም ውጪ ሌላ መፍትሄ የለም የተባለው በጥናትና ከሌሎች አማራጮች ጋር በማወዳደር የተገኘ እምነት ባለመሆኑ የሚያረጋግጠው እንደ ቀኖና መወሰዱን ነው፡፡

ቅሬታን ለሕዝብ ማሰማትና በፓርቲ የመደራጀት መብት ሲከለከል በድብቅ መሰባሰብና መደራጀትን ያስከትላል። ይህ ደግሞ የሴራ መንፈስ ከመፍጠሩ በላይ ላለው ሥርአት ተጻራሪ ወደ ሆነ አመለካከት ይገፋፋል። በድብቅ መደራጀት ካለው የፖለቲካ ሥርአት የሚለይ ብቻ ሳይሆን ከሥርአቱ ጋር ምንም ድልድይ ወይም ውይይት እንዳይኖር ያደርጋል።

## የጽንፈኝነት ተቀዳሚ ምንጭ

በትክክልም በኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው ነባራዊ ሁኔታ በራሱ ብቻ ሥርነቀል አብዮት አላስከተለም ካልን፤ ከአገሩ ሁኔታ ውጪ የሆኑ ምክንያቶች ማስቀመጥ ይኖርብናል፡፡ አብዮቱ ከአገሩ ሁኔታ ካልመነጨ፣ አመጣጡ ከላይ ወደ ታች፣ ማለትም ከምሁራን አመለካከት ወደ ሕዝብ ወረደ ማለት ነው፡፡ ይህ አመጣጥ ለርዕዮተአለማዊ ልወጣ ቅድሚያ ይሰጣል፡፡ በቅድሚያ ተቀባይነት ያገኘ እምነት የነባራዊ ሁኔታ ችግሮችን ግንዛቤና መፍቴዎች በቅድሚያ ይወስናል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው፣ የተሄደው ከችግሮች ወደ ግንዛቤ ሳይሆን በቅድሚያ ከተያዘ እምነት ወደ ችግሮች ነው፡፡

### 1) ትምህርትና ዘመናዊነት

በኢትዮጵያ የምዕራባዊ ትምህርትና የዘመናዊነትን አመጣጥ ስንመረምር ነው የአክራሪነት የውጭ ምንጮችን የምናገኛቸው፡፡ በጥቅል አነጋገር፣ ከምዕራባዊ አገሮች የመጣው ትምህርት ዘመናዊነት ማለት ከኋላ ቀርነት ለመላቀቅ ምዕራባዊ እሴቶችን፣ ተቋማትንና አሠራሮችን መቀበልና መቅዳት ነው ይላል፡፡ ለዚህ ግብ ወሳኝ ማስፈጸሚያ የሚሆኑ ዘመናዊ ትምህርት ቤቶችን በመክፈት የአገሩን ተወላጆች ማሠልጠን ነው፡፡ በመሆኑም ኋላቀር በሆኑ አገሮች ውስጥ ተማሪዎችና ምሁራን በተወሰኑ ሙያዎች ብቻ የሚያገለግሉ ሳይሆን አገርን የማሠልጠን ተልዕኮም አላቸው፡፡ ይህ አገር የማቅናት ተልዕኮ ከምዕራባዊ ቅኝ አገዛዝ የሚለየው በቅርጽ እንጂ በይዘት አይደለም፤ ምክንያቱም የሁለቱም ዐላማ አገር ማሰልጠንና ከኋላቀርነት ወደ ሥልጣኔ መውሰድ ነው፡፡ በሌላ አባባል፣ እንዲህ አይነት ተልዕኮ የሚያስፈጽመው የአገሩ ተወላጅ የሆነ፣ ነገር ግን በቅኝ አገዛዝ አመለካከትና አሠራር የታነጸው የተማሪው ክፍል ነው፡፡ ልክ እንደ ቅኝ አገዛዝም የአገሩን የተወረሱ እምነቶችና እሴቶች ኋላቀር አድርጎ ይመለከታል፤ መሠልጠንም እነሱን አጥፍቶ በምዕራባዊ ተቋማትና እሴቶች መተካት ነው ይላል፡፡

2) የሶሺያሊዝም እምነት እንደ ቀኖና ለምን ተወሰደ? ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው ሌላው መልስ የማርክሳዊ ሌኒናዊ ንደፈሐሳብ ዓለምአቀፋዊ የበላይነት ደረጃን በጊዜው መያዙን እንድንመለከት ያደርገናል፡፡ በ60ዎቹና በ70ዎቹ (እ.ኤ.አ)የነበረው ሥዕል የሚያሳየው ካፒታሊዝምና ሊበራሊዝም እያፈገፈጉ፤ ሶሺያሊዝም ድል እየተጎናጸፈና እየተስፋፋ እንደሚሄድ ነበር፤ በተለይ በቪየትናም ጦርነት የተነሳ፡፡ ይህ ሥዕል አታላይ እንደነበር አሁን ታውቋል፡፡ ነገር ግን በጊዜው ብዙ ተቀባይነት ስለነበረው የማርክሳዊ ሌኒናዊ

*ቀሪውን በገፅ 22 ይመልከቱ*

# አዲስ አበባ

# የትናንሽ መንግስታት ከተማ ልትሆን?

መላክ ቢ.

ይህቿን ከተማ ሲያንቆለጳጳሷት "የአፍሪካ መዲና፣ ከብራስልስ ቀጥሎ በአለም ሁለተኛዋ የዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ መናኸሪያ፣ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች መንደር፣ የህብረብሄር እና ህብረባህል መገለጫ ወዘተ" ይሏታል። አዲስ አበባ እንደስሟ ያላበበች ከተማ ናት የሚሏትም ብዙዎች ናቸው። አሁን አሁን ደግሞ ይህች የፈረደባት ከተማ የዘመኑ ዋና የፖለቲካ መጫወቻ ካርታ እየሆነች ነው።

ኬኛ እና የኛ የሚሉት ቃላት በፖለቲካው ውጥረት መዝገብ ውስጥ የሰፈሩት በዚህችው ከተማ መነሻነት ነው። የኦሮሚያ ክልል የአዲስ አበባ ከተማን የልዩ ጥቅም ጥያቄ አልፎ የከተማዋን የይገባኛል ጥያቄ ካርድ ከመዘዘ ሰነባብቷል። ቄሮ ከሚያነሳቸው ጥያቄዎች ዋነኛው ጥያቄም እስካሁን ይኸው ነው። የዴሞግራፊ፣ የቀበሌ መታወቂያ፣ የአዳዲስ ሰፋሪዎች ጉዳይ፣ የኮንደሚኒየም ግንባታ፣የህገወጥ ቤቶች ማፍረስ ዘመቻ ወዘተ አዲስ አበባን ተግነው እና ዓላማቸው አድርገው የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች ውጤቶች ናቸው። "ፊንፊኔ ኬኛ" እና "አዲስ አበባ የህዝቦቿ ናት" የሁለት ወገን ክርክር አሁንም ገና ከመድረኩ አልወደረም።

ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ "ጦርነት እንከፍታለን" ያሉበት የነእስክንድር ነጋ ባለአደራ ምክር ቤት የተቋቋመው፣ አዲስ አበባ ለአዲስ አበባውያን ንቅናቄ (አለን) እንቅስቃሴ የተጀመረው ወዘተ ይህችኑ ከተማ የመታገያ ሜዳ አደርጎ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገበታ ሸገር ያሉት የሸገርን እናስውብ ፕሮጀክትም የዚሁ የአዲስ አበባ ጉዳይ ነው።

ይህ ሁሉ ዓይን ላይዋ አርፎ፣ የፖለቲካ ትግል ፊሽካ ተነፍቶባት ከወዲህ ወዲያ ስሟ የሚላጋው ይህች ከተማ አሁን ደግሞ ለነዋሪዋ ስጋት የሆነ ስርዓት አልበኝነት እና ወንጀል እየተስፋፋባት ያለች መስላለች። የከተማዋ ፖሊስ የወንጀል መከላከል ብቃት ጥያቄ ውስጥ የገባበት፣ የጥበቃ ሽፋኑ የት ድረስ እንደሆነ ግራ ያጋባበት፣ ወንጀለኞች በጠራራ ጸሃይ ሰዎችን መዝረፍ የጀመሩበት፣ አዳዲስ የወንጀል አይነቶች እንደጉድ ፈልተው ለነዋሪው ስጋት የሆኑበት ጊዜ መጥቷል። በተለይም ከተሃድሶ ፖለቲካ ሽግግሩ በኋላ ባለፈው አንድ አመት አዲስ አበባ የማን አለብኝ ባዮች እና የወሮበሎች መንፈላሰሻ እየሆነች መጥታለች ይላሉ ብዙዎች። ከአነስተኛ ጀምሮ እስከከባድ ወንጀል ድረስ በረቀቀ እና ከወትሮው በተለየ መንገድ የሚፈጸምባት ከተማ ሆናለች። አንዳንዶች እንደሚናገሩት አዲስ አበባ ህግ በማይፈሩ እና ማንአለብኝ በሚሉ ትናንሽ መንግስታት ቁጥጥር ስር የዋለች እስክትመስል ድረስ



በየቦታው ህብረተሰቡን የሚያስበረግጉ እና በሰላም ወጥቶ መግባቱ ላይ ጥያቄ የሚያጭሩ ወንጀሎች እየተፈጸሙባት ነው። በየክፍለ ከተሞቹ የሚፈጸሙት ወንጀሎች ከመከላከል አቅም በላይ የሆኑ እስኪመስሉ ድረስ ወንጀል ፈጻሚዎች ያለስጋት መንቀሳቀስ ጀምረዋል።

ፖሊስ ወንጀል ፈጻሚዎቹን በመያዝም ሆነ ምርመራ አጣርቶ ለፍትህ አካላት በማቅረብ የማስቀጣት ሂደቱ ላይ ያለው ብቃት ጥያቄ ውስጥ ገብቷል። ከሁሉም በባሰ የፖሊስ አባላት ራሳቸው በከባድ ወንጀሎች ውስጥ ሲሳተፉ መገኘታቸው ህብረተሰቡ በፖሊስ ላይ ያለውን አምነት እንዲያጣ እና በስጋት እንዲንቀሳቀስ ምክንያት ሆነዋል። የወንጀል ምርመራ ስራ ላይ የፖሊስ የመወሰን አቅም ተዳክሞ በአንጻሩ የወንጀል ፈጻሚዎች መብት በርትቶ አብዛኛው ጉዳይ የፍትህ ደጅ ሳይጠና እየተዘጋ ዜጎች ጥያቄ እንዲያነሱ እየገፋፋ ነው።የፖሊስ የመያዝ፣ የማሰር፣ የመመርመር እና የማስቀጣት አቅም ተዳክሟል።

በተለያዩ የማህበራዊ ሚዲያ ገጾች ከተማዋ የወንጀለኞች መናኸሪያ እየሆነች መምጣቷ እና ነዋሪው በሰላም ወጥቶ በሰላም ለመግባት አለመቻሉ፣ ከምንም በላይ ለወንጀል ስጋት መጋለጡ እየተጻፈ እና እየተሰራጨ ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ለዲፕሎማቲክ ማህበረሰቡ የመረጃ ምንጭ ሆነው የሚያገለግሉ የአለም አቀፍ ተቋማት ገጾችም በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በተለይ አመሻሽ ላይ እና በቀንም ጭምር ወንጀሎች እየተበራከቱ በመምጣታቸው ጥንቃቄ እንዲወሰድ ሲመክሩ ተስተውለዋል።

## "ሰላማዊዋ አዲስ አበባ"

የሩቁን ሃገር ደቡብ አፍሪካ ጆሃንስበርግ ወይም ፕሪቶሪያ ከተማ ትተን ጎረቤት አገር ኬንያ ናይሮቢ ውስጥ ያለውን የወንጀል ስፋት መጠን ስናስተውል አዲስ አበባ ፍጹም ሰላማዊ እና ከስጋት ነጻ ቀጠና ናት ብለን ለመመስከር የሚቀድመን አልነበረም። በተለይ በከተማዋ የሚገኙ የብዙ ሃገራት ዜጎች አዲስ አበባ ውስጥ ቀን ቀርቶ ሌሊት ለብቻ መንቀሳቀስ ጭምር ስጋት የሚደቅን ተግባር አለመሆኑን ሲናገሩ ይህች ከተማ በአፍሪካ ካሉ ፍጹም ከወንጀል ስጋት የተላቀቁ ሰላማዊ ከተሞች የላቀችው መሆኗን እየገለጹ ነው። ከአራት አመታት በፊት ፕሪስት ሞሰስ ሚልስ የተባለ

▶የጃማይካ ቄስ አዲስ አበባ ውስጥ በነበረው የ1 ዓመት ቆይታ ስለከተማዋ በግል የጡመራ መድረኩ ይህንን አስፍሮ ነበር።

“አዲስ አበባ ለማንም ቀላል የሆነ እና ኒው ፍላወር የሚል ትርጉም ያለው ስም የያዘች አፍሪካዊ የኩራት ከተማ ናት። የአዲስ አበባ ጓዳ ጎድጓዳዎች የነጻነት አየር ሲተነፈስባቸው እና የአልበገር ባይነት ወኔ ሲናኝባቸው የኖሩ ቦታዎች ናቸው። እንደኔ ላለ ጥቁር የአፍሪካ መጤ ካሪቢያን ሰው አዲስ አበባ ከትውልድ ስፍራ እኩል ሁሉን የምታስተናግድ ከተማ ናት። ይህች ከተማ ምናልባት ለአይን የሚያማምሩ መናፈሻዎች እና ውብ የእግር ሽርሽር ማድረጊያ መንገዶች አይኖሯት ይሆናል። ወይም መንገድ ዳር ቁጭ ብሎ ወጪ ወራጁን እየቃኙ ንጹህ አየር ሊተነፍሱበት የሚችሉበት ምቹ ስፍራ የላትም ይሆናል። አዲስ አበባ በየመንገዱ ዳር ዳር በተተከሉ ዛፎች ስር ሃሩር ማሳለፊያ መቀመጫዎች ወይም ሰዎች ተቀምጠው ጋዜጣ የሚያነቡበት አደባባዮች የሏትም ይሆናል። በዚህች ከተማ ምናልባትም ከመዲና የጸዳ እፍኝ ቦታ ማግኘት ችግር ይሆን ይሆናል። በየመንገዱ ሙዚቃ እየተጫወቱ የሚያዝናኑ ሰዎች አልሞሉባትም ይሆናል። አዲስ አበባ ስሟ እንጂ መልኳ አበባ ላይሆን ይችል ይሆናል። ነገር ግን ከዚህ ሁሉ በላይ ውድ የሆነ አንድ ነገር እዚህች ከተማ ውስጥ አለ። ይህ ነገር በሌሎች የአፍሪካ ሃገራት ከተሞችም ይሁን በሌላው የአለም ሃገር በፍለጋም የማይገኝ ውድ ነገር ነው። ይህ ነገር ሰላም ነው። አዲስ አበባ ቀንም ሌሊትም ሰላም ናት። ማንም የውጭ ሃገር ዜጋ ምሽት ላይ ጭር ባለ መንገድ ሲሄድ ቢያድር የሚተናኮለው ሰው የለም። ማንም በፈለገው ስፍራ ብር ቢዘረዝር ተከትሎ የሚዘርፈው የለም። ማንም በየመንገዱ እየቆመ ፎቶ ቢያነሳ ካሜራውን ለመቀማት ጩቤ ይዞ የሚመጣ የለም። ማንም ለመዝናናት ወጣ ቢል ሽጉጥ የዞ የሚተኩስበት የለም። አዲስ አበባ በየመንገዱ ምናልባት ለማኝ ያስቸግር ይሆናል እንጂ ሌባ ስጋት አይደለም። እገድልሃለሁ ብሎ የሚያስፈራራ ቀርቶ ለስድብ ምላሱን የሚያወጣ ሰው እንኳን የለም። ሰው አክባሪነት ብቻ ሳይሆን ወንጀል ነውር መሆኑ በራሱ ከተማዋን ሰላማዊ አድርጓታል። ለኔ ትልቁ የከተማ ውበት ጸጥታና ሰላሙ መረጋገጡ እንጂ ፎቅ በርክቶ ገዳይ መብዛቱ አይደለም። ስራና ገንዘብ ሞልቶ ሌባና ዘራፊ መፍላቱም አይደለም። ዘመን ይለውጣት እንደሁ እንጃ እንጂ አሁን አዲስ አበባ ሰላማዊ ከተማ መሆኗን ኖሬባታለሁና እመሰክራለሁ”

ዛሬ ፐሪስት ሞሰስ የሚጠቅሷት አዲስ አበባ በህይወት ያለች አትመስልም። ዛሬ አዲስ አበባ የውጭ ዜጋ ቀርቶ የሃገሬው ነዋሪም ካሜራ ይዞ የፈለገውን ነገር ያለስጋት ፎቶ የሚያነሳባት አልሆነችም። ዛሬ አንድ አካባቢ ላይ ድንገት በቡድን የተባሰቡ ልጆች የፈለጉትን ወግረው እና ያሻቸውን አድርገው ወደየቤታቸው ሲገቡ ምነው የሚላቸው እየጠፋ ነው። ፖሊስ ወንጀል የፈጸሙ ሰዎችን በቁጥጥር ስር ለማዋል የሚወስድበት ረጅም የቢሮክራሲ እና የሂደት መንቀራፈፎች በብዙዎች ዘንድ ተዓማኒነቱን እንዲያጣ እያደረገው መሆኑም ይነገራል። በዚያው መጠን የምርመራ ስራው በመዳከሙ የማስቀጣት መጠኑ በዚያው ደረጃ ላልቷል። እናም አዲስ አበባ “የቄስ ሞሰስ አይን የበላት ከተማ” ሆናለች።

## የተገለበጠው ስም

ወትሮም የአዲስ አበባ ከተማ ወንጀል ከሌሎች ማናቸውም የኢትዮጵያ ከተሞች የወንጀል አፈጻጸም ደረጃ አንጻር ሲታይ ብዙ ነው። ብዛቱ ግን በቀላል ወንጀል እንጂ በከባድ እና ሰላምን እና ጸጥታን በሚያናጉ የወንጀል አይነቶች አልነበረም። ይህች ከተማ በብዛት የለመደችው ቀላል ወንጀል ቅሚያ/ንጥቂያ ሲሆን፤ ከባድ የሚባለው ደግሞ ወቅት ጠብቆ የሚመጣው የሰብሮ ስርቆት ወንጀል ነው።እንዲያም ሆኖ ቀላል የሚባለው የወንጀል አይነትም ቢሆን ቀን በቀን እና በማን አለብኝነት የሚፈጸም ሳይሆን አሳቻ ጊዜና ቦታ ጠብቆ የሚካሄድ የወንጀል ተግባር ነበር። ዛሬ ግን በመሃል አስፓልት ላይ ሰው እያየ ሰው የያዘውን ንብረት ይነጠቃል። ፖሊስ በአካባቢው እያለ በመኪና ሰዎች ይዘረፋሉ። ተው ተው እየተባለ ነጥቆ የሚሮጥ ብዙ ነው። ቤት ተሰብሮ ንብረት ይወሰዳል። ቢሮዎች ተፈልቅቀው ዝርፊያ ይፈጸማል። በተለይ የሞባይል ስልክ ንጥቂያ አይን በአይን የሚካሄድባት እና አንዳንዴም ቀላል ሌብነቶችና ዘረፋዎች በቀን የሚደረግባት ከተማ እየሆነች ነው አዲስ አበባ።

## የወንጀል መብዛት ለምን?

ብዙዎች እንደሚናገሩት ከለውጡ በኋላ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ከማረሚያ ቤት መለቀቃቸው አንደኛው የወንጀል መብዛት ምክንያት ነው። የአዲስ አበባ ፖሊስ በአንድ ወቅት ባደረገው አሰሳ በቁጥጥር ስር ካዋላቸው ወንጀል ፈጻሚዎች መካከል 49 ያህሉ ከማረሚያ ቤት የወጡ መሆናቸውን አረጋግጧል። እነዚህ በቅርቡ የተፈቱ ሰዎች ዳግም ወደማረሚያ ቤት እንዲገቡ ያደረጋቸው ነገር ከቀደመ ወንጀላቸው አለመማራቸው ብቻ ሳይሆን የቅጣት ጊዜያቸውን አለመጨረሳቸው የእርምት ሂደቱን ስላስተጓጎለው መሆኑን የፖሊስ አባላት ይናገራሉ።

ሁለተኛው ምክንያት ከለውጡ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሃገራችን ክፍሎች የተፈጠረው “የጎበዝ አለቃ” አካሄድ ህግ መኖሩን ወደመርሳት እና ወደማንአለብኝ መንገድ ማምራቱ ነው። በዚህም ሳቢያ ከዚህ ቀደም የፖሊስ አባላት ባሉበት ስፍራ ቀርቶ በባዶ ሜዳ እንኳን የማይፈጸም ወንጀል በየስፍራው እየተፈጸመ ሰው ንብረቱ እና አካሉ ለጉዳት ሲዳረግ እየተስተዋለ ነው።

የአዲስ አበባ ፖሊስ ያወጣው ከሃምሌ 2011 እስከ መጋቢት 2011 ዓ.ም ያለው የ9 ወራት የወንጀል ሪፖርት እንደሚያሳየው በከተማዋ ለህብረተሰቡ ስጋት ናቸው ተብለው የተለዩ ከባድ ወንጀሎች ብዛት 10 ነው። በ9 ወራት ብቻ ታዲያ 12ሺህ 326 ከባድ ወንጀሎች ተፈጽመዋል። ይህ አሃዝ ሲታይ በአዲስ አበባ ውስጥ በቀን ብቻ ከ20 አስከ 25 ድረስ ከባድ ወንጀሎች እንደሚፈጸሙ ማወቅ ይቻላል። ይህ አሃዝ ወንጀል ተፈጽሞባቸው ያመለከቱትን እንጂ ጥቃታቸውን ውጠው ዝም ያሉትን አይጨምርም። ፖሊስ እነዚህን ከባድ ወንጀሎች ሲፈጽሙ የያዛቸው ተጠርጣሪዎች ብዛት 1ሺህ 680 ነው። እነዚህ ወንጀል ፈጻሚዎች የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪን የእለት ከእለት ኑሮ አደጋ እና ስጋት ውስጥ ሲጥሉ ከነበሩ ብዛት ያላቸው ወንጀለኞች ፖሊስ ለጊዜው በቁጥጥር ሰር ያዋላቸው ናቸው።

## አደገኛው አደጋ

አዲስ አበባ ከተማ በአሁኑ ወቅት የተደቀነባት ከባድ የወንጀል ስጋት በከተማዋ የተስፋፋው የጦር መሳሪያ ንግድ እና ዝውውር ወንጀል ነው። ይህ ወንጀል በራሱ ከተማዋን የጦር መሳሪያ የሽያጭ እና ዝውውር እንዲሁም መሸጋገሪያ ቀጠና ከማድረግ ባሻገር በመሳሪያ የተደረገ ከባድ ዘረፋ እንዲፈጸም ሊያደርግ ይችላል። መሳሪያዎቹ አንድም በባለቤትነት፣ አለያም በኪራይ በወንጀል ፈጻሚዎች አጅ እየገቡ የህዝቡን ሰላም ለማወክ እና ለዘረፋ ብሎም አካል ለማጉደል እና ግድያ ወንጀሎች ያደርሳሉ።

በዚህች ከሃምሌ ጀምሮ አሁን እስካለንበት ጊዜ ድረስ በፖሊስ የተያዙት ህገወጥ ጦር መሳሪያዎች ብዛት 10ሺህ 732 ሽጉጦች፣ 30 ክላሽንኮቭ ጠመንጃ፣4 መትረየሶች፣ እንዲሁም ወደ 1 መቶ ሺህ የሚጠጋ የተለያዩ መሳሪያዎች ጥይት ነው። ይህ የጦር መሳሪያ ዝውውር እና ህገወጥ አጠቃቀም መበራከት ለከተማዋ አለመረጋጋት እና የስጋት ቀጠና መሆን አንድ ትልቅ ምክንያት ነው። ለአንድ ከተማ በዚህ መጠን መሳሪያ በግለሰቦች እጅ ተይዞ መገኘት የአመጽ መበራከት እና▶

*ከተማዋ የፖሊስ ሃይል ጥበቃ ላይ መላላት እና መሰላቸው የታየባት ጊዜ ተበራክቶ ስለነበር በዚያው መጠን በበርካታ ቡድን ተደራጅተው ከፍ ያለ ወንጀል የሚፈጽሙ ወንጀለኞች ቁጥር ጨምሯል። እነዚህ አሁን ፖሊስ በቁጥጥር ስር ያዋላቸው 21 ወንጀለኞች በጦር መሳሪያ ታግዘው የቤትሰብሮ ስርቆት ፣ የመኪና ስርቆት፣ውንብድና እና ከባድ ሌብነት ወንጀሎችን ሲፈጽሙ ከርመዋል።*

ግጭት ቢነሳ ከፍ ያለ ውድመት ለማድረስ ትልቅ እድል ይከፍታል። ለዚህም ራሱ ፖሊስ ባካሄደው ኦፕሬሽን አስሶ የያዛቸው በቡድን የተደራጁ ወንጀለኞች አንድ መገለጫ ናቸው።

ከተማዋ የፖሊስ ሃይል ጥበቃ ላይ መላላት እና መሰላቸት የታየባት ጊዜ ተበራክቶ ስለነበር በዚያው መጠን በበርካታ ቡድን ተደራጅተው ከፍ ያለ ወንጀል የሚፈጽሙ ወንጀለኞች ቁጥር ጨምሯል። እነዚህ አሁን ፖሊስ በቁጥጥር ስር ያዋላቸው 21 ወንጀለኞች በጦር መሳሪያ ታግዘው የቤት ሰብሮ ስርቆት፣ የመኪና ስርቆት፣ውንብድና እና ከባድ ሌብነት ወንጀሎችን ሲፈጽሙ ከርመዋል። ፖሊስ በቁጥጥር ስር ባዋላቸው ጊዜ ታዲያ ከእጃቸው ላይ 9 መኪኖች፣ 112ሺ.ህ 800 የአሜሪካ ዶላር፣ ከ218ሺ.ህ ብር በላይ የኢትዮጵያ ገንዘብ፣ ከዜጎች ላይ የተነጠቁ ከ132 በላይ ሞባይል ስልኮች፣ 17 ሽጉጦች ከነጥይቶቻቸው፣ እንዲሁም ላፕቶፕ ኮምፒውተሮች፣ ወርቆች እና ሌሎችም ንብረቶች ተይዘውባቸዋል።

በወትሮ ልምድ ደረጃ አዲስ አበባ እንዲህ የበዛ የከባድ ወንጀሎች ጎተራ ሆና የምታውቅበት ጊዜ ብዙ አይደለም። ብዙዎች ለከተማዋ የወንጀል መበራከት ምክንያቱ ፖሊስ ራሱ ነው ሲሉ ይከስሳሉ።

## የፖሊስ ሌቦች

ከዚህ ቀደም ቢኖርም ካለፈው አንድ አመት ወዲህ እጅግ የተበራከተው ወንጀል የሃገር መከላከያ ሰራዊት እና የፖሊስ ዩኒፎርም እየለበሱ አሳቻ ሰአትና ስፍራ መርጠው ወንጀል የሚፈጽሙ ሰዎች መበራከት ነው። እነዚህ ወንጀል ፈጻሚዎች ያንን ልብስ ለብሰው መኪና እያስቆሙ በጦር መሳሪያ አስገድደው ወንጀል ከፈጸሙ በኋላ ይሰወራሉ።

ልክ በዚሁ መጠን የአዲስ አበባ ፖሊስ አባላት ሆነው ሳሉ ለጥበቃ በተመደቡበት ስፍራ በመጥፋት ወደሌላ ቦታ በመሄድ በያዙት መሳሪያ ዘረፋ ሲፈጽሙ አድረው የሚመለሱ ከባድ ወንጀል ፈጻሚ የአዲስ አበባ ፖሊስ የጥበቃ አባላት መበርከታቸው ተነግሯል። እነዚህ በፖሊስ ዩኒፎርም ሆነው፣ ለወንጀል መከላከል ስራ የተሰጣቸውን ትጥቅ ታጥቀው ወንጀል እንዲከላከሉ የተመደቡ የፖሊስ አባላት ሰዎችን ያለታዛቢ ዘርፈው እና ሌላም ጉዳት አድርሰው ተመልሰው ሰራተኛ መስለው ሲገቡ ብዙም የሚጠረጥራቸው አልነበረም። በመጨረሻ ላይ ግን ኮሚሽኑ ባደረገው ማጣራት በወንጀል ተግባር ላይ ተሰማርተዋል ያላቸውን ሁሉ በቁጥጥር ስር አውለዋቸዋል።

እንዲህ አይነት ተግባር የፖሊስን ስም የሚያጠፋ ብቻ ሳይሆን ህብረተሰቡ በፖሊስ ላይ አምነት እንዳይኖረው እና በማናቸውም ጊዜ ፖሊስ ለሚያቀርበው ትዕዛዝ ተፈጻሚነት እምቢተኛ እንዲሆን ያደርገዋል። በህግ አስከባሪ አካላቱ ያልተማመነ ዜጋ ደግሞ ሰላሙን ራሱ ለመጠበቅ ሲል መታጠቅ እና መደራጀት ይጀምራል። በዚህ ወቅት ነው ያልታሰቡ ወንጀሎች መፈልፈል እና የሰላም ስጋት ወደመሆን አደጋ መሸጋገር የሚጀምሩት።

## አዳዲሶቹ የከተማ ወንጀሎች

የሞባይል ንጥቂያ ወንጀል ሁሌም ያለ የወንጀል አይነት ቢሆንም፣ አሁን ሰዎች ሞባይል ስልክ እያነጋገሩ መሄድ ስጋት እስኪሆንባቸው ደርሰዋል። በተለይ በመኪና ሆነው ሞባይል ሲያነጋግሩ ድንገት ከየት መጡ የማይባሉ ሰዎች ስልኩን ቀምተው መሮጥ በመጀመራቸው ብዙዎች በገዛ ከተማቸው የመኪና መስተዋት ዘግተውና ታፍነው ለማሽከርከር ተገድደዋል። በተለይም በትራፊክ መብራቶች አካባቢ ቆመው የአሽከርካሪዎችን ትዕግስት የሚፈታተኑና ሲመቻቸውም ወንጀል የሚፈጽሙ ወጣቶች መበራከት ከባድ እየሆነ መጥቷል።

በሌላ በኩል በሞተርሳይክሎች የሚፈጸሙ ወንጀሎች የከተማዋ ነዋሪ ራስ ምታት ሆነዋል። የከተማዋ ትራፊክ ፖሊስ እንደሚናገረው እዚህ ከተማ ውስጥ እስካሁን ድረስ ከ15ሺ.ህ በላይ ወደከተማዋ በህገወጥ መንገድ የገቡ የሞተር ሳይክሎች ተገኝተዋል። እነዚህ የሞተርሳይክሎች ለቦርሳና ሞባይል ስልክ ንጥቂያ፣ ለህገወጥ ትራንስፖርት አገልግሎት፣ ለሌባ ተቀባይነት እና ሽሻጊነት እንዲሁም ሌሎች ወንጀሎችን ፈጽሞ ለመሰወር አገልግሎት ላይ ውለዋል። በዚህ ረገድ ህብረተሰቡ በተለይ በሴቶች ላይ የደረሱ አደጋዎችን እና ነጥቂያዎችን በማየት ፖሊስ ለምን ይህንን መግታት እንዳልቻለ ደጋግሞ ሲጠይቅ ተስተውሏል። አሁንም ወንጀሉ እንደቀጠለ ቢሆንም ከቀድሞው ግን የመቀነስ አዝማሚያ ማሳየቱን ነው ፖሊስ የሚናገረው።

ከነዚህ ወንጀሎች በተጨማሪ በቪትዝ መኪኖች የሚደረገው ዝርፊያ ሌላው አዲስ የከተማው ወንጀል ነው። በተለይ ዜጎች ከፍ ያለ ብር ከባንክ ይዘው ሲወጡ ተከታትሎ መንገድ በመዝጋት እና በማምታታት ወይም በጦር መሳሪያ በማስፈራራት ገንዘብ ነጥቀው መሰወር ጀምረዋል። ከመኪና ወርደው ሌሎች መኪኖችን በመስበር ውስጥ ያለ እቃ ሰርቀው መሰወርም ጀምረዋል። ንጥቂያ እና ያፈጠጠ ዘረፋም ይፈጽማሉ። ከወንጀሉ ስፍራ ቶሎ ስለሚሰወሩም የሚደርስባቸው ብዙም የለም።

ኮልጌት አፋቸው ውስጥ ይዘው በሚያልፍ ሰው ላይ በመትፋት ከዚያም ይቅርታ የሚጠይቁ መስለው ልብሱን በመጠራረግ ኪሱን የሚያወልቁ ሌቦችም በከተማዋ በርክተዋል። ብዙው ሰው ይቅርታ ጠይቀው ልብሱን መጥረግ ሲጀምሩ ለመከላከል ሲሞክር ኪሱን ስለሚረሳ ሞባይል ስልክ የመሰረቅ እና ሌሎች ንብረቶችን የማጣት አደጋው በዚያው መጠን የጎላ ነው።

## የተፋዘዘው የፖሊስ ወንጀል ምርመራ

በመከላከል ስራ ፖሊስ ሃይል መጠቀም መተዉን ተከትሎ ወንጀል ፈጻሚዎች በፍጥነት ፖሊስን ወደመገዳደር እና በተለይም እጅ ከፍንጅ ተይዘው ወደጣቢያ ሲወሰዱ ሲሉ ለመሄድ አለመፈለግ እና መታገል እየተለመደ የመጣ ተግባር ሆኗል። ፖሊስ በዚህ ሳቢያ ወንጀልን በብቃት የመከላከል አቅሙ ቀንሷል ይላሉ ብዙዎች። ይህ ብቻ ሳይሆን ተጠርጣሪዎች ከተያዙ በኋላ በተገቢው ማስረጃ ለፍርድ የማቅረብ እና የማስቀጣት ብቃቱ ላይም ጥያቄ እየተነሳ ነው።

ለዚህ አንዱ ምክንያት የሚሆነው አሁን ባለው የፖሊስ ምርመራ አደረጃጀት ዐቃቢ ህግ እና ፖሊስ በአንድ ጽህፈት ቤት ውስጥ መሆናቸው እና ዐቃቢ ህግ ያላመነበትን ነገር ፖሊስ መስራት አለመቻሉ ነው። ዐቃቢ.ህግ ከፖሊስ ይልቅ ለተጠርጣሪዎች የሚያደላ አካሄድ በመከተል ፖሊስ ቢያንስ በጥርጣሬ ብቻ ይዞ ሰዎችን ማቆየት የሚችልበትን እድል እያሳጣው እና የወንጀል ምርመራ ስራውን በአግባቡ እንዳይከውን እንቅፋት እየፈጠረበት ይገኛል ይላሉ ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉ የቂርቆስ ክፍለከተማ ፖሊስ መምሪያ አባል። ዐቃቢ ህግ ክስ መመስረት አይቻልም ካለ ሌላ ማስረጃ ለመፈለግ እና ለማጠናቀር እንኳን የሚሆን ጊዜ ስለማይሰጠው ወንጀል ፈጻሚዎች እንዲፈቱ እና ህብረተሰቡ በወንጀል መከላከል እና በፖሊስ የጥበቃ ሃይል ላይ ያለው እምነት እንዲሸረሸር ምክንያት ፈጥሯል።ለአሰራር ማሳለጥ ተብሎ እና ፖሊስና ዐቃቢ.ህግ ቢሯቸውን አንድ ማድረጋቸው የፖሊስ ምርመራ መዝግብ ሊያስቀጣ በሚችል መረጃ ተደራጅቶ ለፍርድ ቤት እንዲላክ ለማድረግ የሚካሄድ ስራ ቢሆንም በዚያው መጠን የፖሊስን ምርመራ የማድረግ እና የተለያዩ ቴክኒኮችን ተጠቅሞ እውነቱ ላይ ለመድረስ የሚሰራው ስራ ላይ አሉታዊ ጫና አለው ብለዋል አስተያየት ሰጪው።

## ትናንሾቹ መንግስታት

አዲስ አበባ መስፋቷ ብቻ ሳይሆን በየዕለቱ ከሁሉም የሃገራችን ክልሎች የሚፈልሱ ዜጎች እያጣበቧት መሆኑ በራሱ ለወንጀል መበራከት መንስዔ ነው። ይህ ብቻም ሳይሆን በቡድንም ይሁን በተናጥል በወንጀል ተግባር ላይ ተሰማርተው የፖሊስ ዳና ያልደረሰባቸው ሰዎች ከተማዋን የሚያስተዳድሩ ትናንሽ መንግስታት ሆነው እየመጡ ነው ይላል በጉዳዩ ላይ አስተያየቱን ለግዮን የሰጠ የቀድሞ ፖሊስ አባልና አሁን በአንድ የግል ጥበቃ ስራ ድርጅት ውስጥ ሱፐርቫይዘር የሆነው ኢንስፔክተር ወሰን መሳይ። እነዚህ ወንጀል ፈጻሚዎች በእለት ከእለት ህይወት ውስጥ ጣልቃ እየገቡ የነዋሪውን ሰላም የሚያውኩ ከሆኑና ፖሊስም ይህን ለመከላከል አቅም ካነሰው ትናንሾቹ መንግስታት ከተማዋን እንዳይገዟት ስጋት አለ። ከወዲሁ ግን የአዲስ አበባ ፖሊስ በ10 ክፍለ ከተሞቹ፣ በ800 ወረዳዎች እና በ57 ፖሊስ ጣቢያዎች የሚያስማሰራውን 19ሺ.ህ የሰው ሃይል በመጠቀም ይህንን እያደገ የመጣ ኀበዝ አለቅነት እና የወንጀል መስፋፋት ሊያግድ ይጠበቅበታል። አዲስ አበባ የቀደመ ሰላሟን መልሳ ከማግኘት የሚያግዳት አንድ ነገር ቢኖር ወንጀል ከደረቅ ወንጀልነቱ ተሻግሮ የፖለቲካ መልክ ከያዘ እና ለዚህ መልክም የሚሰሩ ዜጎች ከተበራከቱ ብቻ ነው። ይህ እንዳይሆን ደግሞ የፖሊስ ኮሚሽኑም ይሁን የደህንነት ሃይሉ በጥምረት መስራት ይጠበቅባቸዋል።

# የአግ7 ጉባኤ ኢሳትን በተመለከተ ጉባኤው ያስተላለፈው ሙሉ ውሳኔ



የኢትዮጵያ ህዝብ በወያኔ አፋኝ ስርአት የሚደርስበትን የመረጃ አፈና ለመበጣጠስና በኢትዮጵያ ውስጥ ለዴሞክራሲ የሚደረገውን ትግል ለማገዝ ግንቦት 7 ለፍትህ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ በሚያዝያ 2010 ኢሳት ሳተላይት ቴሌቪዥንን አቋቋመው። ኢሳት ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ "የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ኢሳትን ያቋቋምኩት እኔ ነኝ" የሚል መረጃ ሳይሰጥ እስከዛሬ ድረስ ቆይቷል። በዛን ወቅት ይህ ውሳኔ ተወስኖ በተግባር የዋለበት ምክንያት ኢሳትን ከወያኔ ጥቃት ለመከላከል ታስቦ ነበር። ሁለገብ ትግል ለማድረግ ከወሰነ ድርጅት ጋር ኢሳት የተቆራኘ መሆኑ ከተረጋገጠ፤ ተቋሙ ምንም ያህል በነጻ ሚዲያ መርህ የሚሰራና ለዴሞክራሲ የቆመ መሆኑ ቢታወቅም፤ በአሸባሪዎች መሳሪያነት በወያኔ መንግስት ተከሶ በተለያዩ ሃገሮች መንግስታት ይታገድ ነበር።

የኢሳት እንቅስቃሴ እንዳይስተጓጎል ወይም እንዳይቋረጥ ለማድረግ የሚያስችል ተጨባጭ መረጃ ላለመስጠት እስከ ዛሬ ድርጅታችን "ኢሳትን የመሰረትኩት እኔ ነኝ" ሳይል ቆይቷል። ንቅናቄው ኢሳት የተመሰረተበትንና ለበርካታ ወራት የሚያስፈልገውን ወጪ በቀጥታ በመሸፈን፣ ከዛም አልፎ አባላቱን በአለም ዙሪያ በማስተባበር፣ በመላው አለም የሚገኙ ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በስፋት ኢሳትን እንዲደግፉ በማድረግ የድርጀቱ አባላት ታሪክ የሚያስታውሰው ተግባር እንዲያከናውኑ አድርጓል። ከዚህ በተጨማሪ ንቅናቄው መልካም ግንኙነት ከነበራቸው ሌሎች አካላት ጋር በመነጋገር ኢሳት በየጊዜው ሲያጋጥመው የነበረውን የፋይናንስ ችግር እንዲወጣ ተጨማሪ እገዛ አድርጓል። ከዚህ በተጨማሪ ከፍተኛ የግልና የቡድን የመተማመን ሰብአዊ እሴት የነበራቸውን አባላቱን በኢሳት ባለቤትነት፣ የቦርድ አባልነት የሃላፊነት ድርሻ እንዲሸከሙ፣ በአስተዳደርና በቴክኒክ ስራዎች ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዲያደርጉ በማድረግ ንቅናቄው ከገንዘብም በላይ ኢሳት አስተማማኝ በሆነ ውስጠ ድርጅት ሁኔታ መንቀሳቀስ የሚችልበትን ሁኔታ ፈጥሮለታል።

ንቅናቄው እንዲህ አይነቱን የሚዲያ ተቋም ባቋቋመበት ወቅት ከላይ ከተቀመጠው የወያኔ የመረጃ አፈና ከመበጣጠስ ምክንያት ውጭ፣ "አንድ የፖለቲካ ድርጅት የራሱ ሚድያ ሊኖረው ይገባል" የሚል እምነት ስላልነበረው፣ በጣቢያው የኤዲቶሪያል ፖሊሲ ጣልቃ ላለመግባት ወስኖ ተንቀሳቅሷል። በመሆኑም በሃገራችን ታሪክ የፖለቲካ ድርጅቶች እጅ ተቋቁመው ከታዩ ሚዲያዎች ሁሉ ኢሳት የአንድ ድርጅት ተራ የፕሮፓጋንዳ መሳሪያ ሳይሆን የመላው የሃገሪቱ ህዝብ አይንና ጆሮ ሆኖ፣ በየትኛውም ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚደርስን ጥቃት፣ በደል፣ የመብት አፈና፣ እምነትንና ዘርን ሳይለይ ለተበዳዮቹ አለኝታና እንዲሁም ለሁሉም በዳዮች ደግሞ በተመሳሳይ ማንነታቸውን ሳይለይ የእግር እሳት ለመሆን ችሏል።

በዚህ አርማ የላቀ የሃገርና የመላው ኢትዮጵያ ህዝብ ወገንተኝነቱ የተነሳ ኢሳት በሃገሪቱ ዜጎች በሙሉ፣ ግፍ በመፈጸምና በዘረፋ ወንጀል ተጠምደው ከነበሩት ውጭ፣ የተወደደና የታመነ ለመሆን በቅቷል። በዚህ ተቋም ውስጥም አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ የጋዜጠኝነት ሃላፊነታቸውን ሲወጡ ለነበሩ ጋዜጠኞች ህዝቡ ያሳየው ከፍተኛ ፍቅርና ክብር እነዚህ ጋዜጠኞች በተቋሙ ውስጥ ባገኙት የኤዲቶሪያል ነጻነት ግዴታቸውን በብቃት፣ በነጻነትና በቁርጠኝነት የተወጡ በመሆናቸው ነው።

ባለንበት ወቅት አርበኞች ግንቦት ሰባት ከኢሳት ጋር የነበረውንና ያለውን ግንኙነት ይፋ ማድረግና ይህን ተቋም በተለመከተ ንቅናቄው ያለውን አቋም ከአዲሱ ፓርቲ ምስረታ በፊት ማሳወቅ ስላለበት ከላይ ያቀረብነውን ማብራሪያ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል። በመቀጠል ባለንበት የተለወጠ ሃገራዊ ሁኔታ ሚዲያን በሚመለከት ንቅናቄያችን ከያዘው አቋም ጋር ከኢሳት ጋር ያለውን ዝምድና ሸፋፍኖ ማለፉ አብሮ የማይሄድ፣ ወደፊትም በአደባባይ ለምናቀርበው በመርህ ላይ ለተመሰረተ ሃገራዊ የሚዲያ ራእይ በግብዝነት ሊያስፈርጅ ስለሚችል ግልጽነት ወቅቱ የሚጠይቀው ጉዳይ ሆኖ አግኝተነዋል።

በንቅናቄው እምነት "በአንድ ሃገር ላይ እውነተኛ ዴሞክራሲ ተግባራዊ እንዲሆን ከተፈለገ በመንግስት ስልጣን ላይ ያለ የፖለቲካ ድርጅት/ወይም ድርጅቶች እንዲሁም በአንድ ሃገር ውስጥ የሚገኙ ተፎካካሪ ድርጅቶች የሚዲያ ባለቤቶች መሆን የለባቸውም" ብሎ ያምናል። የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ፣ "ከየትኛውም የፖለቲካ ድርጅቶች ያልወገኑ፣ ነጻና ገለልተኛ የሚዲያ፣ የፖለቲካ ድርጅቶቹን በህዝብ ስም መጠየቅና መሞገት የሚችሉበት ሁኔታ ሳይኖር ሊከናወን አይችልም" ብሎ ንቅናቄያችን ያምናል። ዴሞክራሲያዊ ስርአት በተገነባባቸው ሃገሮች ውስጥ ሚዲያ 4ኛ መንግስት ተብሎ የሚጠራበት ምክንያት፣ በዋንኛነት የፖለቲካ አካላትን ዴሞክራሲያዊ ያልሆኑ አመለካከቶችና ድርጊቶችን ለህዝብ በማጋለጥ የዴሞክራሲያዊ ስርአቱን ጤነኛነት ለማረጋገጥ በሚጫወተው ወሳኝ ሚና ነው። የስልጣን ብልግና እንዳይኖር፣ እርስ በርሳቸው እንዲጠባበቁ ሆነው ከተቀረጹ መንግስታዊ ተቋማት ላይ 4ኛው የስልጣን ብልግናን ተከላካይ ተብሎ የሚታሰበው የሚዲያ ተቋም በፖለቲካ ድርጅት እጅ እንዲወድቅ ማድረግ፤ የአንድ ሃገርን ዴሞክራሲ በአንድ አራተኛ ጤና ከመንሳት ልዩነት የለውም። በዚህ የተነሳ በሃገራችን የሚገኙ ማናቸውም የሚዲያ ተቋማት ከፖለቲካ ድርጅቶች ቁጥጥር ነጻ እንዲሆኑ የምናደርገውን ትግል አጠናክረን ለመቀጠል ንቅናቄያችን ኢሳትን በተመለከተ የሚከተለውን ውሳኔ አስተላልፏል።

✓ የኢትዮጵያ ህዝብ በወያኔ አፋኝ ስርአት የሚደርስበትን የመረጃ አፈና ለመበጣጠስና በኢትዮጵያ ውስጥ ለዴሞክራሲ የሚደረገውን ትግል ለማገዝ የግንቦት7 ንቅናቄ ኢሳትን ማቋቋሙን ለመጀመሪያ ጊዜ በጉባኤና በአደባባይ ግልጽ በማድረግ፣ የኢሳት ባለቤትነት ጉዳይ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እልባት እንዲያገኝ በማሰብ፣ ኢሳት ከተመሰረተ ጀምሮ አብዛኛውን የገንዘብ፣ የመረጃና የቴክኒክ ድጋፍ ሲያገኝ የነበረው ከህዝብ መሆንን በመገንዘብ፣ ሲያገለግልም የነበረው የኢትዮጵያ ህዝብ አይናና ጆሮ ሆኖ ስለነበር፣ የወደፊቱ የሚሻሻለው የሃገሪቱ የሚዲያ ህግ በሚፈቅደው አዲስ አሰራር መሰረት የኢሳት ባላቤት የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲሆን፣ ተቋሙም አትራፊ ያልሆነ ማህበራዊ ድርጅት ሆኖ እንዲመዘገብ፤

✓ ኢሳት ሲያገለግላቸው የኖሩትን የሃገሪቱን ዜጎች በሙሉ የሚወክል ስፋትና ስብጥር ያለው ቦርድና የማህበር አባላት ያሉት ሃገራዊ ተቋም ሆኖ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲደራጅ፣

✓ ይህን የሽግግር ስራ በወቅቱ ኢሳትን የሚያስተዳድሩ የቦርድ አባላት ከግቡ እንዲያደርሱት፣

✓ ይህን ተቋም አዲሱ ፓርቲ በባለቤትነት የሚወርሰው ተቋም ስለማይሆን፣ ንቅናቄው ሲፈርስ የጉቤውን ውሳኔ በባለቤትነትና በበላይነት የሚያስፈጽም አካል ክፍተት እንዳይኖረው በማሰብ፣ አሁን ያለው የኢሳት ቦርድ የጀመረውን የማሸጋገር ስራ ተከታትሎ የሚያስፈጽም ኮሚቴ መኖር አስፈላጊነቱን በማመን፣ አዲሱ ፓርቲም በማያውቀው ጉዳይ ሃላፊነት ውስጥ ገብቶ ችግር ላይ እንዳይወድቅ በመስጋት፣ የሚቋቋመው ኮሚቴ አባላት ኢሳትን ከምስረታው ጀምሮ የሚያውቁት፣ ኢሳትን ነጻና ገለልተኛ ተቋም ለማድረግ የሚያስችል አቅም፣ ብቃትና የመርህ ጥብቅነት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል በሚል እሳቤ፣ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን፣ አቶ መአዛህ ታፈሰን፣ አቶ ሲሳይ አጌናንና አቶ ፋሲል የኔአለምን የኮሚቴው አባላት ሆነው እንዲሰሩ ጉባኤው በሙሉ ድምጽ ወስኗል።

## አንደበት



“ግምማ የሚባለው አሰራር በዚህ ሂደት አልተካሄደም፡፡ እስካሁን አመራር ከሆነ ተገመገመ እየተባለ ነበር የሚነሳው፤ አሁን ግን አሰራሩ ቀርቶ፣ ሰራተኛውንም የማወዳደሩ ሂደት ተለውጧል፡፡ በፊት፣ ቢያንስ ሰውን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት በህግ የተሰራ ለማስመሰል ይጣር ነበር፣ የአሁኑ ግን ጫፍ የወጣ ነው፡፡ ከተነሱት አመራሮች፣ 23 ከአንድ ብሄር (ትግራይ ያልሆኑ) የወረዱ ሲሆን፣ በአንፃሩ የኦሮሞ አንድ ልጅ ብቻ ነው ከኃላፊነት የወረደው፡፡ ይህን ተግባር፣ ተራ ሰው እንኳ ቢያየው፣ ብቃት በብሄር እየተመነዘረ መሆኑን ያሳያል”

***አቶ ማስተዋል አረጋ /የገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን ኦዲተር የነበሩ ኢትዮጲስ ጋዜጣ ግንቦት 4 ቀን 2011 ዓ.ም***



“የኛ ዋናው መሠረታዊ ዓላማ አንደኛ፤ አደረጃጀቱ ህዝባዊ መሆን አለበት፣ ሁለተኛ፣ ማህበራዊ ፍትህን ማስፈን አለበት የሚል ነው፡፡ ይህን አላማ ይዘን አሁን በየወረዳዎቹ ጽ/ቤቶች ከፍተናል፡፡ 312 ተብሎ የተጠቀሰው የወረዳ ቁጥር በቀጣይ እየጨመረ ይሄዳል፡፡ በእነዚህ ወረዳዎች ላይ ሙሉ ጉባኤ አለ፡፡ ሁሉም ወረዳዎች የራሳቸው 15 የስራ አስፈፃሚ፣ 5 ወይም 3 የጠቅላላ ጉባኤ ተወካይ ምክር ቤት ያላቸው ናቸው፡፡ ጠንካራ ስራ የሠራንባቸውን ነው አሁን 312 ብለን በመግለጫ የጠቀስነው እንጂ ሌሎች ወረዳዎች ላይም ይሄው አደረጃጀት ነው የተፈጠረው”

***አቶ የሺዋስ አሰፋ /የቀድሞው የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር/ አዲስ አድማስ ጋዜጣ ግንቦት 3 ቀን 2011 ዓ.ም***



“ምን ያህል ሰዎች ስለሪፎርሙ ግንዛቤው እንዳላቸው አመላካች መረጃ የለኝም፡፡ አማርኛ ወይም የትኛውንም የአገሪቱን ቋንቋም መናገር አልችልም፡፡ በመሆኑም እየተካሄደ ስላለው ነገር ዝርዝር ጉዳዮችን ለመከታተል ከባድ ያደርገዋል፡፡ ሆኖም ግን በተመድ ሥርዓት ውስጥ ከመንግስት፣ ከሲቪል ማኅበረሰቡና ከሌሎችም ብሔራዊ ተቋማት ጋር በቅርበት እንሠራለን፡፡ በመሆኑም ምን እየተካሄደ እንዳለና በአገር አቀፉ ጉዳይ ላይ ጥሩ ጆሮ ያለን ይመስለኛል፡፡ እኛ የምንሠራው አገር አቀፍ ባለድርሻነትና አመራር እንዲስፋፋ ነው፡፡ ቀድመን አንፈርጅም”

***ሚስ ሉዊ ቻምበርሊን / በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የልማት ፕሮግራም (ዩኤንዲፒ) የኢትዮጵያ ቋሚ ወኪል/ ሪፖርተር ግንቦት 4 ቀን 2011 ዓ.ም***



“እኔ ለህሜት ብዙም ጆሮ የለኝም… ለበቀል ቢሆንማ ኖሮ በሩን ከርችሞ ለዘጋብኝ ፌደሬሽን ከውጭ የመጡ የህክምና ባለሙያን አሳምኜ፣ አግባብቼ ስልጠና እንዲሰጡ ሁኔታውን አላመቻችም ነበር፡፡ የገፉኝና ውለታዬን የረሱት ግለሰቦች እንጂ ፌደሬሽኑ አይደለም፡፡ እኔ ሙያው ለሀገሬ የሚሰጠውን ጥቅምና ትርፍ እንጂ የግለሰቦችን ተንኮል አይደለም የማየው፤ በቀጣይም የሀገራችን ሙያተኞች ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየሰራሁ ነው፤ ይሄ ጊዜው ሲደርስ የሚታይ ነው፡፡ ሚዲያ ደግሞ ማስተማሪያ እንጂ መበቂያ አይደለም፤ እኔም የበቀል ሰው ስላልሆንኩ ሚዲያን ለዚህ ሰይጣናዊ አላማም እንደማላውለው ሀሜተኞቹ እንዲያውቁ እፈልጋለሁ”

***አስራት ሀይሌ /አሰልጣኝ/ ሀትሪክ ጋዜጣ ግንቦት 7 ቀን 2011 ዓ.ም***

## ግጥም

### ስሜት

ስሜትህ ሲነሣ ፍጠን ፍጠን ሲልህ፣
ስሜትህ ሲነሳ አድርግ አድርግ ሲልህ፣
ከባድ ማርሽ አስገባ እንዳይገለብጥህ፡፡
በህይወት መንገድ ላይ ኑሮን ስትመራ፣
በስሜትህ ሣይሆን በማስተዋል ሥራ፡፡
ስሜት ቁልቁለት ነው ቁልቁል የሚያሮጥ፣
አይንን ያሳውራል እንዳይገለጥ፡፡
በስሜት የሚያስብ በስሜት የሚኖር፣
ቁምነገር የለውም ይቀራል በአጭር፡፡
የዘንድሮ ምርጫ ሁለት ብቻ ሆኖአል፣
ማለፍና መውደቅ ውድድር ቀርበዋል፡፡
አንዳንዶች ሣያውቁ በስሜት መርጠው፣
ተሰናክለው ቀሩ እስከ ወድያኛው፡፡
ሁሉም በተሰጠው መኖር እየቻለ፣
ሁሉም ቦታ ልግባ ጆከር ልሁን አለ፡፡
ጆከር ለካርድ እንጂ ለሠው ልጅ አይደለም፣
ሁሉም ቦታ አትግባ ተወሰን ግድየለም፡፡

***(ጆሬጆ ዘውዴ)***

## አባባል

↖ በአምላክህ ላይ ተስፋ አትቁረጥ፣ እሱ በአንተ ላይ ተስፋ አልቆረጠምና፡፡

↖ ጥርሳችን የፈለገውን ያክል ጊዜ ምላሳችንን ቢነክሰውም፤ ዛሬም ድረስ ሳይለያዩ በአንድነት ይኖራሉ፡፡ ይሄ ነው የመቻቻል መንፈስ፡፡

↖ ጨለማውን አትፍራ፤ ከዋክብቱን የምታየው ሲጨልም ነውና!

↖ አይሆንም ወይም አይደለም ለማለት ድፍረት ይኑርህ፤

↖ ሁልጊዜም እውነታውን ለመጋፈጥ ወኔው ይንርህ፤ ትክክል ስለሆነ ብቻ ትክክለኛውን ነገር አድርግ፡፡ እነዚህ ህይወትህን በመልካም ስነምግባር ለመኖር ቁልፍ ነገሮች ናቸው፡፡


## ይሕን ያውቁ ኖረል

■ 4 የሻይ ማንኪያ ካችአፕ ከአንድ ከበሰለ ድንች ጋር እኩል የሆነ የምግብ ንጥረ ነገር እንዳለው ያውቃሉ?

■ ሰውነታችን በየቀኑ ወደ 10 ቢሊየን የሚጠጉ የቆዳ ቅርፋፊዎችን እንደሚያስወግድ ያውቃሉ?

■ ታላቁ መሪ ዊንስተን ቸርችል በዳንስ ቤት በሴቶች ክፍል ውስጥ የተወለደ መሆኑንስ ሰምተዋል?

# ኩረጃና የትምህርት ጥራታችን ማሽቆልቆል ወዴት ይወስደናል?



መምሕር አሽብር ውርጌሳ

28ኛው የትምህርት ጉባኤ መቀሌ ከተማ እየተካሄደ ጎን ለጎን የሰማናቸው ትምህርታዊ ዜናዎች፤ "ያገባኛል፣ይመለከታኛል" ለሚል ሀገር ወዳድ ዜጋ ከማሳፈርም ባለፈ፣ አስቸኳይ መፍትሄ ካላበጀንለት የጀመርነው የቁልቁለት ጉዞ ጠርዝ እንደሌለው አመላካች ነው። ለአዌው መውደቀ ምክንያት ከሆኑ ነገሮች መሀል አንዱ ይኸው በትምህርት የታቀደው ዝግጅት ነበር፤ ከ1970 ዓ.ም ጀምሮ መምህሩም፣ ተማሪውም፤ አሳዳጅ፣ ገራፊም፣ ተሣዳጅም አንድ ክፍል ውስጥ መገናኘታቸው ቁልቁለቱን በጥልቀት የተያያዝንበት ጅማሮ ነበር ማለት ይቻላል። በዚህ መልክ ግማሽ ምዕተ ዓመት ስለተጓዝን የዘራነውን እያጨድን ነው። 28 ጊዜ የትምህርት አመራሮች ከባለ ድርሻ አካላቶች ጋር እየተወያዩ፣ በውጤታቸው ግን "ማንበብ የማይችሉ ተማሪዎች ቁጥር በዛ" ይሉናል። ተማሪዎችም በምዘና ማለፍ አልቻሉም፣ መውደቀ በዛ፤ ለምን? ከተባለ ይዘነው የመጣነው የመኮረጅ ባህልም ትንሽ እውቀት ይፈልጋልና ነው። ካላነበበ እንዴት ይኮርጅ? ከትምህርት ማስፋፋት ጋር ችግር የለብንም፣ 40 ዩኒቨርስቲዎች ላይ ደርሰናል። ግን እነሱም ቢሆኑ ኢትዮጵያን እንደምንመኛት ሊያበለፅጉ አልቻሉም። በህግም፣ በኪነ ህንፃ፣ በኮንስትራክሽን፣ በአመራርም ስናየው በሌብነት "እንደ ሜቴክ" እና ጓደኞቹ ስኳር ፋብሪካዎች ውስጥ ያሉ ግዙፍ ሙስናዎች እንዲበራከቱና የቢልዮን ብሮች እዳ በላያችን መቆለል የትምህርት ጥራታችን መጓደል ማሳያዎች ሆነው እንዲቀሩ አድርገዋል።

ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ አዲስ የሚባለው ሥርዓተ ትምህርት መመዘን ያለበት ከተግባሩ፣ ከምርቱ፣ ከፍሬው ነው። የአዌው ጊዜ እንከን የለውም አይባልም፤ ሞልቶታል። የአሁኑም መልካም ፍሬዎች በጥቂቱ ይኖሩታል፤ ግን ገዢ አስተሳሰቡንና ያልተፃፈው ሥርዓተ ትምህርት (ማለት ታች መሬት ላይ ያለው) ትግበራ እያጓደልን መሆኑን አውቀን፤ ሰሞኑን ዶ/ር ዐቢይ ከበፊቱ በተለየ ፊታቸውን ክስክስ አድርገው "ተባብረን ወደ መፍትሄ ፍለጋ እንሂድ" እንዳሉት፤ የትምህርት ባለሙያዎችም የሚከፈለውን ዋጋ እየከፈሉ፣ ህዝቡን አሳትፈው ወደ መፍትሄ ያድርሱን። እኛም በወግ ሣይሆን በተግባር እናግዛቸው፤ መደመር ይሄኔ ነው። ጉባኤዎችን በባለ አራትና ባለ 5 ኮከብ ሆቴል ውስጥ እያሰናዱና ብዙ ሚልዮን ብሮችን እያወጡ፣ ከአመት አመት "ለመለወጥ እየሰራን ነው" እያሉ መግለጫና አቋም ማውጣት ውሃ ቢወቅጡት እምቦጭ ነው የሚሆነው።

የሀገሬ ኢትዮጵያ ችግርና መከራ መነሻው የትምህርት ጥራታችን መውደቅ ነው። አመራሮቻችን በአብዛኛው በተጭበረበረ የትምህርት መረጃ ባለቤትነታቸው ነው የሚታወቁት። በሁሉም ክልል ከ400 በላይ የሀሰት ዲግሪ ያላቸው አመራሮች ተገኝተዋል። እነዚህ ሰዎች ለልጆቻቸው ምን ያስተምራሉ? አሁን የ10ኛ የ12ኛ ክፍል የመልቀቂያ ፈተና እየቀረበ ነው፤ ለኩረጃም ቅድመ ዝጅግት እየተደረገ ነው። ነገር ግን በሚተገበረው የት/ሚኒስቴር ህግ፣ በመጨረሻው ክፍል እርከን አመራሮች በሚሰጠው ትዕዛዝ ይፈፀማል፡ ፡ ይሄ ግነት የለበትም፤ ወላጆች ልጆቻቸው ሲወድቁባቸው ከወረዳቸው፣ ከዞናቸው ሩቅ ወደሆኑና ብዙ ተማሪዎች ወደሚያልፉባቸው ት/ቤቶች ይሸኛሉ። የመካከለኛ አመራር ልጆችም ይላካሉ (የከፍተኞቹ ግን ቻይና እና አሜሪካ አሉላቸውና እነሱ አልተቸገሩም)። ነገር ግን በሀገሪቱ ውስጥ ጥቂት ት/ቤቶችም (የመንግሥት ይሁኑ የግል) አቅሙ ያላቸው ተግተው እየሰሩ፣ ውጤታቸውንም እያየነው ነው። ግና ይሄ በኢትዮጵያዊ የጋራ አሠራር ይቀየር ነው የምንለው። ለማሳያ የሚሆኑ እንደ ድሮው የአ.አ የጄነራል ዊንጌት ት/ቤትን የሚመስሉ አዳዲስ ተቋሞች እያየን ነው፤ በትግራይ የቀላሚኖ ት/ቤት ከየወረዳው ጥሩ ውጤት ያላቸው፣ በአብዛኛው ድሃ የሆኑ፣ በውጤታቸው ተወዳድረው ወደ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እንዲገቡ እየተደረገ ነው፤ይሄ የሚበረታታና የሚደገፍ ነው።


የቀድሞው ጀነራል ዊንጌት ያኔ በእንግሊዝ መንግስት ነበር የሚመራውና የሚደገፈው፡ ፡ ኢትዮጵያ በጠላታችን ጣልያን ለደረሰባት መከራ እንደ ካሣ ሆኖ፣ ነገር ግን እንግሊዞች አዌውን በብልጠታቸው "አይዞህ ከጎንህ ነን" ለማለት የከፈቱት ተቋም ነበር። ዛሬ ላይ ድንቅዬ የሆኑና እድሜአቸው ከ55 ዓመት እስከ 75 የሚደርሱ፣ (ውጭ ሀገር በብዛት የሚገኙትን ጨምሮ) ከፍተኛ ምሁሮችና ዶክተሮች የዚህ ት/ቤት ፍሬዎች ናቸው። በጥሩም ይሁን በመጥፎ መንገድ ከሚጓዙት የከፍተኛ የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎች መሀልም አንዳንዶቹ የዊንጌት ተማሪ የነበሩ ናቸው። በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ አሻራ ያኖሩ ሚሊየነሮችም አሉ። የሚያሳዝነው ነገር 27 ዓመት ሙሉ የትምህርት ሥራዎች እንዴት ይሻሻላሉ? የሚለው ርዕሰ ጉዳይ በየጊዜው እየተነሳ ይጣላል። በ1986 በሥርዓተ ትምህርቱ ቀረፃ አባል የነበሩ፣ (ሚኒስትርም የነበሩ) በእድሜ ገፍተው አሁንም ያው በቴሌቪዥን ሲያወሩ እናያቸዋለን፤ ምንም የተለወጠ የለም፤ እነሱም አያፍሩም? በቅርቡ የድሮዋ ሚኒስትርን በቴሌቪዥን በዚህ ጉዳይ ላይ እንደ ማስታወቂያ ሲያሳዩዋቸው አፈርኩ፤ የወጣላቸውን ስም ኢትዮጵያዊ ሁሉ ያውቀዋል። የእሳቸው ሥርዓተ ትምህርት ለ25 ዓመታት ተተግብሮ የት እንደደረሰም ይታወቃል፤የሚገርመው የሚዲያው ባለቤት ለምን እንዳቀረባቸው ነው። ‹‹ባለጌ ባያፍር ዘመዱ ያፍር›› ነው የሚባለው?!

እንደ ማጠቃለያ ግን ስለወደቀው የትምህርት ጥራት ለመወያየትና ለአስቸኳይ መፍትሄ ሰፊ ጥናት ቢያስፈልግም፤ በዋንኛነት ግን ከማንኛውም ድርጊት በስተኋላ ያለውን የህይወት እንቆቅልሽ አይቶ ፍቺ መስጠት ያስፈልጋል። ይሄ ለአመራሩና ለመንግሥት ብቻ የሚተው፣ ባለ ድርሻ አካላት ለይስሙላ የሚናገሩት ሣይሆን ህዝብን ሳንሰለች እያወያየን፣ ራሱ የመፍትሄ ሀሳብ እንዲሰጥ ማድረግም ይጠበቅብናል። በተጀመረው ፍኖተ ካርታ ላይ ተጨማሪ ተግባራትን እንስራ።

ከሁሉም በላይ የአስተሳሰብ፣ የአመለካከት Mindset በተማሪ፣ በወላጅና በመምህራን ላይ በፍጥነት እየሰራን፤ ነገር ግን የህግ የበላይነትን፣ ተጠያቂነትን በትምህርት ባለሙያዎች ላይ መተግበር ለዛሬ፣ ለነገ የሚባል አጀንዳ አይደለም። ለምሳሌ የትምህርት አመራሮችና መሪዎችም ላለፉት 20 ዓመታት ውሽታም ሆነዋል። ለምሳሌ የዛሬ አራት ዓመት ማትሪክ ሲሰረቅ፣ አንድ ከፍተኛ የፖለቲካ ሃላፊ (ከሚኒስትሩ በላይ የነበሩ)እና ራሳቸው ሚኒስትሩም ለጊዜው አፋጦ የያዛቸውን የህዝብ ተቃውሞ ለመሸወድ "በአስቸኳይ እርምጃ እንወስዳለን" አሉና ዋሹ፤ በነጋታው ሌባውን አስረው ለፍርድ የሚያቀርቡ ይመስሉ ነበር። ከ1986 ዓ.ም ጀምረው ሚኒስትርም፣ ዳይሬክተርም፣ የመንግስት ተወካዮችም "እየሠራን ነው" በሚል ፈሊጣቸው እየዋሹ፤ መልሰው "የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎቻችን ማንበብ አይችሉም፣ ፈተና ወደቁብን" ሲሉ ያማርራሉ። ነገር ግን መጀመሪያ ለምን ውጤት ማምጣት አቃተን? በሚል ራሳቸውን መጠየቅ ይገባቸዋል።

አሁን የማትሪክ ፈተና እየደረሰ ስለሆነ በየወረዳው በመላ ኢትዮጵያ ከ200 በላይ የመጀመሪያ አመራር ሆነው በፎርጅድ ዲፕሎማና ዲግሪ የተያዙትን ሰዎች ለፍርድ አቅርቦ ለማስተማሪያነት መጠቀም ያስፈልጋል። ኩረጃን በተመለከተ በተለይ "ያልተፃፈው ሥርዓተ ትምህርት" ላይ ለምሳሌ በአካባቢያቸው ስለወደቁ፤ ወደ ሌላ ክልል ተልከው እየኮረጁና አስተማሪዎች እየሰሩላቸው ፈተናውን አልፈው ለመምጣት የሚሰደዱትን በግልፅ ማስቆምና ማገድ ያስፈልጋል። በእኛ ክልል (ደቡብ ወሎ) የዞኑ አስተዳዳሪ ሚስትና ልጅ ተሰደው፣ ተፈትነው አልፈው፣ አሁን ሙያተኛና ባለስልጣን ሆነዋል። ድሮ በልጅነታችን ለሽቀላ ወደ አሳይታ የአሁኑ አፋር ክልል እንሄድ ነበር፤ አሁን ግን ማትሪክ ማለፍ ያቃተው ይሄድበታል። ይህ አገር ያወቀው ሃቅ ነው፤ ወላጆች እንዲህ ካደረጉ ህፃናት ምን ይማራሉ? እነዚህን ህፃናት በዚህ መንገድ እየቀረፅን "ትልቅ ነበርን፣ ትልቅም እንሆናለን" ማለት እንዴት ይቻላል?

**ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይጠብቅ!**



አሸናፊ ዘደቡብ

# “የተፈጥሮ ፈውስ” ከተባለ በጠበብት የጸደቀ መሆን ይኖርበታል

“ተፈጥሯዊ ፈውስ” ሲባል እንሰማለን፡ ፡ ምን ማለት ይሆን? ዕፅዋትስ በዚህ ረገድ ድርሻ ያበረክታሉን? እነዚህ ዓበይት ጥያቄዎች በአያሌ ሕሙማን ሲቀርቡ፣ ጠቢባን ሲያሰባስቡ ለጊዜ ሽምግልና ምስክርነት የበቁ መሆናቸውን ሳንገነዘብ አልቀረንም፡፡ “ጎመን አንጀቴን አራሰልኝ፣ የደረቀ ሆዴን አለሰለሰልኝ፣ ሎሚ ቁርጠት አስታገሰልኝ…” የሚሉ ሞልተዋል፡፡

“ነጭ ሽንኩርት መብላት ከጀመርኩ ወዲህ ያ መከራ ሲያስቆጥረኝ፣ ሆዴን እየቀበተተ ሲያስጨንቀኝ የኖረው የጨጓራ በሽታ (ጋዝስታራይትስ) ለቆኛል” ብለው ያጫወቱኝ አንድ ሰውም ይጠቀሳሉ፡፡ አሁን ደግሞ ጥቁር አዝሙድ ለብዙ ሕመም ፈውስ እንደሚያስገኝ ሲነገርለት ይደመጣል፡፡ ዝንጅብልም እንዲሁ በሻይ መልክ ሲጠጣ ወይም እንደዚሁ ተቀቅሎ ወይም ጥሬውን ሲወሰድ ማለፊያ እንደሆነ ሲወራ እንሰማለን፡፡ የአትክልትን ውለታ ከጋዝ ትዝታ አጣምረው በረዥሙ ያወጉኝ አንድ አዛውንት ዘወትር ከትዝታዬ ጠፍተው አያውቁም፡፡ ለአብነት ይሆን ዘንድ ወደኋላ እመለስበታለሁ፡፡

በባሕር ማዶ የሕክምና ሊቃውንት የቀለመ አንድ የፍተሻ ሰነድ እንደሚያመለክተው ክረምሪም ባሉት ዓመታት የአንጀት ነቀርሳ (ካንሰር) የሚያሰጋው ብዙውን ጊዜ በሃምሳኛው የዕድሜ ዘመን የሚገኙትን ወንዶች ነበር፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የሰላሣ አምስት ዓመት ወጣቶች በዚሁ አደገኛ ደዌ ተይዘው ሲማቅቁ መታየታቸውን የሙያው ብስሎች ይናገራሉ፡ ፡ ብሎም ቢሆን ሆድ በቆረጠ፣ የበሉት በተገላበጠ፣ ጥቂት በጎረበጠ ቁጥር መደንገጥ እንደማያሻ ጠበብት ይመክራሉ፡፡ በጥቅሉ ሁሉም የካንሰር መርዶ አይደለምና፡፡

የጨጓራ በሽታ ሲባል ዓይነቱ ብዙ ነው፡ ፡ ከማቅለሽለሽ እስከ ማስመለስ፣ ከሆድ ድርቀት እስከ ቁርጠት፣ ከቃር እስከ ጨጓራ ቁስለት ያሉት ሁሉ የተካተቱበት አበሰኛ ደዌ ነው፡፡ ሆድ በነፋስ የሚወጠርበት፣ በአየር የሚነፋበት፣ ሳይበሉ የሚጠግቡበት፣ ረሀብ የሚናፈቅበት አልያም የመባልዕት ሽታ የሚጠላበት ነው፡፡ ሳይጎርሱ ቦርጭ ማውጣት፣ ሳይመገቡ ማግሳት የጨጓራ ሕመም ዕለታዊ ትዝታ ከመሆን አያመልጥም፡ ፡ ማልመዝመዙ፣ ማስጨነቁ፣ ስንቱ ስንቱ!! ተዘርዝሮ አያልቅም፡፡

የሕክምና ባለሙያዎች እንደሚያስረዱት ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ሁኔታዎች ዕውን በሚሆኑበት ወቅት በጥድፊያ ወደ ሐኪም ቤት ሄዶ ምርመራ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

*“ጨጓራው ተቆጥቶ ነው፣ አብጦ ወይም ተልጦ ነው……..” ውጤቱ ከሐኪሞች ይገ ኛል፡፡*

*በጽሑፌ መግቢያ ላይ ስለ ተፈጥሯዊ ፈውስ በተለይም ዕፅዋት በዚህ ረገድ ሊኖራቸው የሚችለውን ድርሻ በማስመልከት በጥያቄ ለተውኩት ነጥብ ምላሽ ለማግኘት ግን የጀርመናዊቷን የዶክተር ኡልሪክ ሆርገር ድርሳነ ሥነ ሕይወት መመልከት አለብን፡፡ እንዲህም ይነበባል፡፡----*

*“ቃርና ቁርጠት እየተከሰተ፣ ሆድ በነፋስ እየተቀበተተ፣ ግሳት እየበረከተ፣ የማቅለሽለሽና የማስመለስ አዝማሚያ እያመለከተ በሚታይበት ወቅት በሻይ መልክ የሚጠጣው ካሞሚላ ፍቱን ነው፡፡ ማለዳ በባዶ ሆድ አንድ ወይም ሁለት ሲኒ ወፈር ያለ ካሞሚላ ጠጥቶ ለአሥር ደቂቃ በጀርባ መንጋለል፣ ለአሥር ደቂቃ ደግሞ በግራ ጎን ማረፍ፣ በመጨረሻም ለአሥር ደቂቃ ደግሞ በደረት መተኛት ከሕመሙ ለመዳን ከሚደረገው ጥረት አንፃር በእጅጉ ይረዳል፡፡”*

የተጠባቢዋ ሰነድ እንደሚያመለክተው ለብ ያለ ውሀ ውስጥ ተነክሮ የተጨመቀ ጨርቅ በሆድና ጀርባ ዙሪያ መጠምጠም ከካሞሚላው ጎን በተፈጥሮ ፈውስ አጋዥነቱ የታወቀ ነው፡፡ ከበድ ወደ ሚለው ወደ ጨጓራ ቁስል (አልሰር) ለመሸጋገር እስከ አሁን በተደረገው ጥናት መሠረት ብዙ ጊዜ የሚፈጅ አይደለም፡፡ አበጠ… ሰነባብቶ ተገሸለጠ ነው… ቆሰለ ነው፡ ፡ በወቅቱ ካልደረሱበት!!

*የዶክተር ሆርገር መልዕክተ ፈውስ የጨ ጓራውን ቁስል ጠቅሶም እንዲህ ይላል፡፡----*

“ለጨጓራ ቁስልም (ለአልሰር) ቢሆን ካሞሚላ የማይረዳበት ምክንያት የለም:: ይበልጡን በፍቱንነት የታወቀው ግን ጥቅል ጎመን ወይም ጥሬ ድንች ጨቅጭቆና ጨምቆ ውሀውን መጠጣት ነው:: እንግዲህ የጎመኑንና የድንቹን፣ የካሚሞላውን ፍቱንነት ተረዳን፡ ፡ በምርምር የታቀፈ፣ በሊቃውንት ማስረጃ የተደገፈ በመሆኑም እንቀበላለን፡፡ የነጭ ሽንኩርቱስ ታሪክ የቱን ያህል ይደገፍ ይሆን? ነጭ ሽንኩርት ተከትፎ የመፋጀት ኃይሉ እንዲቀንስ ከውሀ ውስጥ ተዘፍዝፎ ይጠጣል፡ ፡ ከዚያ በእንጀራ ይበላል፡፡ አንዳንዴም ሽንኩርቱ ተዘፍዝፎ የቆየበት ውሀ ማወራረጃ ይሆናል፡፡ ይጠጣልም፡፡ ከዚያ ወዲህ በሽታው አያውቀኝም፡፡ ስለ በሬ ምላስና ሰምበር፣ ስለ በግ ጨጓራና ጉበት (ዱለት) ካልሆነ ስለራሴ ጨጓራ ማውራት ከተውኩ ሰንብቻለሁ፡፡ ጋዝ የተባለውንማ ለማገዶነት ከምመኘው በቀር ከሆዴ ካስወጣሁት ብዙ ቀን አልፎኛል ሲሉ ያወጉኝ አሉ፡፡ ቀደም ብዬ የጠቀስኳቸው ሰው፡ :”

እኚሁ ሰው እንዳጫወቱኝ ከራሳቸውም አልፈውና ተርፈው ለሌሎች ሕሙማን የተድላ ብስራት አስደምጠዋል፡፡ ሆዱ እየተቀበተተ፣ ሱሪው አልበቃ ብሎት የተቸገረ አንድ ወዳጃቸውም በነጭ ሽንኩርት አብነት ከጋዝ መጋዘንነት ወጥቶ ተንፍሷል፡፡

በጥቅሉ ሲታይ በዕጸዋትና በአትክልት አማካይነት የሚገኘው ተፈጥሯዊ ፈውስ በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡ ከሐኪሞች ረድኤት በመለስ ተፈጥሯዊ ፈውስ ግዙፍ ድርሻ ሊያበረክት እንደሚበቃ ተረጋግጦለታል፡ ፡ ይሁንና ከፍ ሲል ከተገለፀው ሌላ ሥር እየማሱ፣ ቅጠል እየበጠሱና እየደቆሱ “ይህ ለጉበት፣ ያ ለኩላሊት……” የሚሉ የመንደር ሊቃውንት ሥፍራ ያገኛሉ ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ሊሆን ይገባል፡፡ ሳይንሳዊ ምስክርነት ካልተሰጠበት በቀር “ውሃ አፍስሰን፣ በአናቱ ቸልሰን…….” የሚሉም ሞልተዋል፡፡ ዋጋ ሊቸራቸው የሚገባ ነው ተብሎ መታሰብ ያለበት አይመስልም ፡፡ “ከሆድ ውስጥ አውሬ እናወጣለን” ከሚሉ “መድኃኒተኞች” መሐከል የተቆጠሩ አንድ ግለሰብ በአንድ ወቅት በሕልም ያዩትን ውሀ አዳሜን ሲያጠጡ መሰንበታቸው ትዝ ይለኛል፡፡ ብቻ የሆድ ላውንድሪው አልሠራም እንጅ!! ማ የሚሉት አውሬ በሆድ ውስጥ ይቀመጣል? መቼስ ተሰምቶ ይታወቃል? የዋሁ ወገኔ የሌለውን አውሬ ከሆድ አስወጣ ብሎ ያን የቅዥት ውሀ በሴንኬሎ እየቀዳ ሲጎነጭ በተቅማጥ ሊያልቅ ነበር፡፡

በእርግጥ “የሀገር ባህል መድኃኒት በፍጹም አያገለግልም፣ ረብ የለውም” ልንል አንችልም፡፡ የማዕድን ውሀ ንጥረ ነገር አዘልነቱ ከተረጋገጠ ማለፊያ ነው፡፡ ሐኪሞች “ሚነራል” ብለው አጽደቀው ሊፈውስ የሚችለውን ደዌ ካላረጋገጡ ግን ፋይዳ አይኖረውም፡፡ ሥራ ሥሩ ቅጠሉና ሌላውም ሳይንሳዊ ምስክርነት ከተሰጠበት ትድግናው ያስተማምናል፡፡ “የተፈጥሮ ፈውስ” ከተባለ በሕክምና ሊቃውንት የጸደቀ መሆን ይገባዋል፡፡

ዛሬ በባህር ማዶዎቹ ሀገሮች የተፈጥሮ ፈውስ ከፍተኛ ሥነ ሕይወታዊ ትርጓሜ ያለው መሆኑ ታምኖበታል፡፡ ምርምር ይካሄዳል፡ ፡ በጥናት ይደግፋል፡፡ በሀገራችን ተመሳሳይ ፍተሻ ቢደረግና ሣሩ፣ ሥራሥሩ፣ ቅጠሉ፣ ውሀው….. የቱ ለየትኛው ፍቱን ሊሆን እንደሚበቃ ቢታወቅ ግን ደግ ይመስለኛል፡፡ በተፈጥሮ ሀብት የከበረች ኢትዮጵያ ለተፈጥሮ ፈውስ ዓይነተኛ አስተዋጽኦ ልታደርግ የማትችልበት ምክንያት አይኖርምና፡፡

# የእነ ታማኝ ግሎባል አልያንስ

## የ6ዓመት የስውርና ይፋዊ ሀገራዊ በረከቶች!

ዓለም አቀፍ ትብብር ለኢትዮጵያውያን መበት (ግሎባል አልያንስ) አሁንም ለወገን ደራሽነቱን አጠናክሮ ቀጥሎበታል፡፡ ከተቋቋመ ስድስት ዓመት የሞላውና በአርቲስት ታማኝ በየነ የሚመራው ግሎባል አልያንስ፤ ለጌዲዮ ጉጂ ተፈናቃዮች፣ አንድ ነጥብ አንድ የአሜሪካን ዶላር ወይም ሰላሳ አንድ ሚሊዮን፣ አራት መቶ ሺኅ ሰባት መቶ ብር የእርዳታ ድጋፍ አድርጓል፡፡

ረቡዕ ግንቦት ሰባት ቀን 2011 ዓ.ም በአዲስ አበባ ስካይ ላይት ሆቴል በተሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ፣ ግሎባል አልያንስ (ዓለም አቀፍ ትብብር ለኢትዮጵያውያን መብት) በጌድዮ ጉጂ ዞን በተከሰተው ግጭት ምክንያት የተፈናቀሉ ወገኖችን ወደ ቀዬአቸው ለመመለስ፤ ከዚህም ባሻገር ለዘለቄታው ለመቋቋም የሚያስችል የፕሮጀክት የመግባቢያ ሰነድ ከወርልድ ቪዥርን ጋር በይፋ ተፋራርሟል፡፡

ለእነዚህ በጌድዮ ጉጂ ዞን በተከሰተው ግጭት ሳቢያ ለከፋ ችግር የተጋለጡ ነዋሪዎችን የማቋቋም በጎ ተግባርን መሰረት አድርጎ፤ ከኢትዮጵያ ውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውንና ትውልደ ኢትዮጵያውን የዕርዳታ ገንዘብ ሲያሰባስብ የቆየው የአለም አቀፍ ትብብር ለኢትዮጵያውያን መብት ፕሬዝዳንት አርቲስት ታማኝ በየነ፤ የመግባቢያ ሰነዱ 70 ሺኅ 72 ተፈናቃይ ተመላሽ ወገኖችን ማዕከል አድርጎ የሚሰራ እንደሆነና፤ በቅድሚያ ግን በተለይም በመፈናቀል ሂደቱ ለጉዳት ተዳርገው የሚያስፈልገውን ሰብዓዊ እርዳታ በተገቢው ጊዜ ማግኘት ያልቻሉት ላይ ትኩረት እንደሚያደርግ ይፋ አድርጓል፡፡

በባህር ማዶ በሚኖሩ ሀገር ወዳድ ጥቂት ኢትዮጵያውያን ተቋቁሞ በርካታ የበጎ ስራ ተግባራትን እያከናወነ የሚገኘው ከግሎባል አልያንስ ጋር በጌዶኦ ጉጂ ዞን የተፈናቀሉትን ወገኖች መልሶ በማቋቋሙ ተግባር ላይ አብሮ ለመስራት የተስማማው ወርልድ ቪዥርን አሜሪካ በበኩሉ 200 ሺኅ የአሜሪካ ዶላር ወይም አምስት ሚሊዮን 717 ሺኅ 220 ብር ለስራ ማስኬጃ መለገሱን አርቲስት ታማኝ በየነ በዕለቱ በነበረው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ አስታውቋል፡፡

ተፈናቃዮችን ወደ ቀዬአቸው የመመለስና መልሶ የማቋቋም ፕሮጀክቱን በበላይነት የሚመራው የወርልድ ቪዥርን ኢትዮጵያ ዳይሬክተር ኤድዋርድ ብራውን፤ በእቅድ የተያዘውና ወደ ስራ ለመግባት በዝግጅት ላይ ያለው ፕሮጀክት፣ በግጭቱ የተጎዱ ወገኖችን በመርዳት፣ መልሶ በማደራጀናት በተጓዳኝም የግጭቱን መንስኤ በመመርመር አስተማማኝ ሰላም በአካባቢው ለማስፈን ከተለያዩ አካላት ጋር ለሚሰሩ የትብብር ስራዎች መልካም




ጅምር እንደሚሆን አመላክተው፤ ፕሮጀክቱ ለአንድ ዓመት የሚቆይ ሲሆን እንቅስቃሴውም በዚህ ወር እንደሚጀምር ተናግረዋል፡፡

## እነ ታማኝ ገንዘቡን ከየት አመጡ?

የዓለም አቀፍ ትብብር ለኢትዮጵያውያን መብት ከፍተኛ ኃላፊዎችና ወርልድ ቪዥርን በጋራ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ድርጅታቸው ስላደረጋቸው አጠቃላይ እንቅስቃሴዎች፣ ሰሞኑን ወደ ሀገር ቤት ስላመጡበት የጌድዮ ጉጂ ዞን ተፈናቃዮችን ሕይወት የመታደግ ተግባር ሰፋ ያለ ማብራሪያ የሰጠው ተወዳጁና ሀገር ወዳዱ አርቲስት ታማኝ በየነ፤ የዕርዳታ አሰባሳቢው ቡድን ወደ ሕዝብ ወጥቶ አየሩን እንደፈለጉ እንዲዋኙበት ያስቻላቸው፤ እንዲሁም ዕርዳታውን ለመሰብሰብ ሀሳባቸውን በግልፅና በተደጋጋሚ ለህዝብ እንዲያደርሱ ያስቻለቸውን የኢሳት ቴሌቭዥርን ሬዲዮ ጣቢያን ክልብ አመስግኖ፤ እንደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ የመሰሉ ጥቂት የሀገር ውስጥና የውጭ ድርጅቶች አካላት ዕገዛና ዕርዳታ ባይኖር ኖሮ ጥሪያቸው ለህዝብ ደርሶ በቂ ምላሽ ሊያገኙ እንደማይችል አስታውቋል፡፡

“የግሎባል አልያንስ የገቢ ምንጭ ምንድን ነው? ለሚለው ጥሩ የመግለጫ ቃል ስለሌለን “መለመን” በሚለው እሳቤ እንዲያዝልን እንፈልጋለን” የሚለው አርቲስት ታማኝ በየነ፤ “በተደጋጋሚ ለምናቀርባቸው ጥሪዎች በውጭው አለም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ከአጠገባችን ሆነው በጠየቅናቸው ጊዜ ያለምንም ማመንታት የሚሰጡን በተግባር ሰርተን ስላሳየናቸው ነው” ብሏል፡፡ በያዝነው ዓመት መጀመሪያ በአዲስ አበባ ቡራዩ በተፈጠረው ችግር ምክንያት የተፈናቀሉና የተጎዱ ወገኖችን ለመታደግ በኢሳትና በማህበራዊ ሚዲያዎች በቀረበው ጥሪ መሰረት ሕብረተሰቡ በአሰባሳቢው ቡድን ላይ ትልቅ ዕምነት በመጣሉ ለመጀመሪያ ጊዜ በውጭ ሀገር በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ታሪክ ባልታየ መልኩ ከግማሽ ሚሊዮን ዶላር በላይ እንደተሰበሰበ ይታወሳል፡፡

በወቅቱ ይህንን ያህል ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ መጠን በአጭር ቀናት ውስጥ ተሰብስቦው፤ ግሎባል አልያንስ ከአደጋ ዝግጁነትና መከላከል ኮሚሽን ጋር በመተባበር ቤታቸው ለተቃጠለ ቤት በመስራት፣ የሽመና መሳሪያቸው ለወደመ የሽመና ዕቃ በመርዳት፤ በጊዜው የታለመውን ፕሮጀክት ተቋሙ ዕውን ያደረገው ለምኖ ባገኘው ገንዘብ እንደሆነ አስረግጦ የተናገረው ታማኝ በየነ፤ እ.ኤ.አ በ2013 ከስድስት ዓመት በፊት የተቋቋመው የበጎ አድራጎት ድርጅት፣ በተጠቀሱጽ ዓመታት ያከናወናቸውን ሀገራዊ እንቅስቃሴዎችና ድጋፎችን በዝርዝር አስቀምጧል፡፡

## የግሎባል አልያንስ ትሩፋቶች በስውርና በይፋ!

በ2013 (እ.ኤ.አ) በሳዑዲ አረቢያ ኢትዮጵያውያንን በአደባባይ፣ በዓለም መድረክ፤ በኢንተርኔት፣ በፌስ ቡክ ላይ በግልፅ እንደታየው በሰው ሀገር በግፍ ሲሰቃዩ ሲደበዱና ሲሞቱ በአይናችን ተመልክተናል፡፡ ይህ አጋጣሚ ብዙዎችን ያስቆጣ ያስቆጨም ጭምር እንደነበር ሁላችንም እናስታውሰዋለን፡፡ በተለይም እንደ ሳዑዲ አረቢያ ባሉ ሀገራት ለስራ በሚሄዱ ኢትዮጵያውያን ላይ እጅግ አስነዋሪ ድርጊት ሲፈፀም “የእኔ ዜጎች ናቸው፤ አትንኳቸው” ብሎ የሚከራከር መንግስት አለመኖሩ ያንገበገባቸው፤ “ሁልጊዜስ እንዲህ ባለው ሁኔታ እያለቀስን እንኖራለን ወይ?” የሚለው ሀገራዊ ስሜት ቁጭት የተከለባቸው እንደ ታማኝ በየነ ያሉ ኢትዮጵያውያን ተሰባስበው፤ ወገናቸውን በተለያየ መንገድ “ አይዞህ” ሊሉ፣ ችግሩንም ሊጋሩ “ዓለም አቀፍ ትብብር ለኢትዮጵያውያን መብት”ን (ጎሎባል አልያንስ) አሜሪካን ሀገር አቋቋሙ፡፡

ግሎባል አልያንስ እንደተመሰረተ፤ የሳዑዲ አረቢያ መንግስት ዓለም አቀፍ ህግን የጣሰ ዕርምጃውን በፍጥነት እንዲያቆም፣ ከዚሁ ጎን ለጎን የኢትዮጵያ መንግስትም ዜጎቹን እንዲቀበል፤ ብሎም ለመብታቸውም ጭምር የመከራከር ግዴታ እንዳለበት ኢትዮጵያውያንን በማስተባበር በመላው ዓለም በሚገኙ የሳዑዲ አረቢያ ኤምባሲዎች ላይ ሰላማዊ ሰልፍ በማካሄድና በመከራ ውስጥ ለነበሩ በርካታ ኢትዮጵያውያን ድምፅ ከመሆን በተጨማሪ፣ የሚደርስባቸው እንግልት፣ ▶

ድብደባና ግድያ በአስቸኳይ እንዲቆም ዓይነተኛ ሚና ተጫውቷል። እነዚህ በሳዑዲ የነበሩት ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገራቸው እንዲገቡ IOM በሚባለው ኢንተርናሽናል ድርጅት በኩል ገንዘብ በማሰባሰብ ስደተኛ እህትና ወንድሞቻችን ተቆርቋሪ መንግስት ባይኖራቸውም፣ ሀገር እንዳላቸው ሁሉም ዜጎች አብረዋቸው እንደሚቆሙ ጭምር እንዲረዱ አድርጓል።

ቀደም ሲል የነበረው አምባገነን ስርዓት በሚከተለው ፖለቲካዊ አካሄድ የተነሳ በቀደሙትና በድርጅቱ የምስረታ መጀመሪያ ዓመታት ግሎባል አልያንስ ኢትዮጵያ ውስጥ በይፋ እንደ ልብ መንቀሳቀስ ባይችልም፤ በፖለቲካ አመለካከታቸውና ተዛማጅ ጉዳዮች የተነሳ መንግስት የገደላቸውን ቤተሰቦች ተደብቆ በመርዳት. እንደባህላችን ለቅሶ በመድረስ፣ መንግስት ያባረራቸውን ግለሰቦች መጠጊያ በመስጠት፣ ከአደጋ ነፃ እንዲሆኑ በማድረግ፣ እንዲሁም በእስር ላይ ያሉ ጠበቃ በማቆም እንዲከራከሩ በማድረግ በርካታ በጎ ተግባራትን ሲያከናውን እንደቆየ ከተሰጠው መግለጫ መረዳት ተችሏል።

በተለያዩ አጋጣሚዎች ከሀገርና ከወገን የራቁ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያ ውያንን በመለመን እንዲህ አይነቱን በጎ ተግባር ሲፈፀም የቆየው ግሎባል አልያንስ፤ በጎንደር በአማራና ቅማንት መሀል የተነሳውን ግጭት ተከትሎ ለተፈናቀሉ ከዘጠና ሺጎ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች፤ በእነሱ ስም ጎ ፈንድ ሚ በመክፈት በወቅቱ ገንዘብ ለመሰብሰብ ቢሞክርም ዕርዳታው በሚታሰበው መልክ ባለመሄዱ የድርጅቱ መስራች ታማኝ በየነ ከወራት በፊት ወደ ሀገር ቤት በመጣበት ወቅት፤ ከቀድሞ ሠራዊት ጋር በተያያዘ ላደረገው አስተዋፅኦ ከቀድሞ የቀዳማዊ ኃ/ ስላሴ አካዳሚ የጦር መኮንኖች ማህበር እሱ ለሚመራው ድርጅት የአምስት ሺጎ ዶላር ሽልማት ተበርክቶለት ነበር። ይሄንን በዜና ሲነገር ያዩ በአሜሪካ የሚኖሩ የኢትዮጵያውያን የሕክምና ባለሙያዎች ማህበር "ግሎባል አልያንስ" የሚሰራው አስደስቶናል! ሲሉ እርዳታ ያደርጋሉ። በተጨማሪ እነዚህን አኩሪ ተግባራት የተመለከቱ ባንኮክ የሚኖሩ ባልና ሚስት ኢትዮጵያውያን ሌላ ድጋፍ በማድረጋቸው፤ ከተጨማሪ የገቢ ማሰባሰብ ጥረት ጋር በመደመር ረዑዕ ግንቦት ሰባት ቀን 2011 ዓ፣ም በጎንደር ለሚገኙ ተፈናቃዮች ግሎባል አልያንስ የሶስት ሚልየን ብር ድጋፍ ከጌዶኦ ወገኖቻችን በተጨማሪነት አበርክቷል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ካለፉት ጥቂት ወራት አንስቶ እስካሁን ድረስ በየቦታው የብሶት ድምፅ የሚሰማባት፣ ስደት መፈናቀልና ሞት የሚስተዋልበት ሀገር እንደሆነች የሚናገረው አርቲስት ታማኝ በየነ ግሎባል አልያንስ አስራ አንድ የቦርድ አመራር እንዳሉት ገልፆ አባሎቻቸው በየስቴቱ ያሉ ከአምስት ዶላር እስከ ሀያ ዶላር ወርሓዊ መዋጮ የሚፈፅሙ መሆናቸውን፤ ከዚህ በተጨማሪም አልፎ አልፎ በሚዘጋጁ ፈንድ ሪሊዞች ላይ ድጋፍ የሚያደርጉ አንዳንድ ግለሰቦችም እንዳሉ በመግለፅ፤ የቦርድ አባላቱ በአሜሪካን ሀገር የሚኖሩና መደበኛ ስራ ያላቸው ቢሆኑም፣ ይሄንን እንደግዴታቸው ቆጥረው፣ በመደበኛ ስራነት ልክ ጊዜያቸውንና ዕውቀታቸውን በነፃ ለሀገራቸውና ለወገናቸው የሚሰጡ መልካም ኢትዮጵያውያን እንደሆኑ ተናግሯል።

"በአሁኑ ወቅት በተለያዩ ቦታዎች ችግሮች ሲከሰቱ ችግሩ በተከሰተ በሰዓታት ውስጥ ምን አደረጋችሁ? የሚል የሕዝብ ጥያቄ ይመጣል፡፡ ልክ መዋቅር እንዳለው እንደ መንግስ፣ት በጀት እንዳለው ግዙፍ ድርጅት፣ ቁጣውንና ሌላውን ተከታይ ነገር ብዙዎች የምታውቁት ነው። እኛም በምንችለው አቅም ጉዳዩን መርምረን ምን እናድርግ? በሚል መልሰን ሕዝቡን መለመን ብቻ ነው አማራጫችን" ያለው አርቲስት ታማኝ በየነ፤ በዚህ መልክ ግሎባል አልያንስ ከሶማሊያ ክልል ለተፈናቀሉ የኦሮሞ ብሔሬሴብ ተወላጆች በአባገዳዎች በኩል የሚችለውን ድጋፍ እንዳደረገ፣ በጊዜው እርሱን ጨምሮ ሌሎች ግለሰቦች በአሸባሪነት የተወነጀሉ በመሆናቸው በይፋ መንቀሳቀሱና መውጣቱ አስቸጋሪ ቢሆንም ተገቢውን ኃላፊነት እንደተወጡ ግን ይፋ አድርጓል።

በስውርም፣በይፋም ላለፉት ስደስት ዓመታት፣ ከወገኖቹ ያልተለየው ግሎባል አልያንስ፤ ከወልቃይት የማንነት ጥያቄ ጋር ተያይዞ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ የነበሩ የኮሚቴ አባሎች ከመንግስት የፀጥታ ኃይሎች አምልጠው ኬንያ ከገቡ በኋላ፤ የኢትዮጵያ የደህንነት ኃይል ተከታትሎ ሊመልሳቸው ሲል ግለሰቦቹ በፍጥነት ወደ ደቡብ አፍሪካ እንዲገቡ አድርጓል። በ2006 ዓ.ም በአንድ ቀን ሰላሳ ስምንት ጋዜጠኞች ከኢህአዴግ መራሹ መንግስት ዕርምጃ በማምለጥ ናይሮቢ በገቡበት ወቅት፤ የጋዜጠኞቹ ስደትና ጉዞ ድንገተኛ ከመሆኑ አኳያ የት እንደሚያድሩ እንኳን የማያውቁ በመሆናቸው፣ ቢያንስ ለሁሉም አንድ ወር የቤት ኪራይ መክፈል ይኖርብናል በሚል ግሎባል አልያንስ በጊዜው አስፈላጊውን ዕርዳታ አከናውኗል።

በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል ውስጥ በአንድ ወቅት ርሃብ ቢገባም፣ መንግስት ግን "ርሃብ የለም" በማለቱና በእዛ አከባቢ ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ማድረግ ስለማይቻል፤ ለንደን ከሚገኝ የሙስሊም ግብረሰናይ ድርጅት ጋር በመሆን በወቅቱ በድብቅ ለተጎጂዎች ዳቦና ውሃ ያቀረበው ግሎባል አልያንስ፤ ዛሬ ግን በሀገሪቱ ውስጥ በተገኘው የለውጥ ሂደት የኮሚቴው አባላት በሀገራቸው ላይ በነፃነት እየተንቀሳቀሱ እንደሚገኙ የሚናገረው ታማኝ በየነ፤ በተለይም ከሁለትና ሶስት ዓመት በፊት በጎንደር አማራ ክልልና በኦሮሚያ ክልል ውስጥ በተነሱ ህዝባዊ አመፆች የተገደሉ ሰዎች ቤተሰቦችን ለመርዳት የተደረገው ጥረት ፈታኝ እንደነበር አስታውሷል። በወቅቱ ለቅሶ ቤቶች ለመግባት እንኳን አስቸጋሪ ሁኔታዎች ከመኖራቸው ባሻገር፤ የደህንነት ኃይሎችም ጥልቅ ክትትል ስለነበር ጉዳት ከደረሰባቸው ቤተሰቦች መረጃ ለማግኘት የነበረው ትግል ፈታኝ ቢሆንም ሁሉም በፅናት ታልፎ ዛሬ ላይ ለመድረስ መቻሉ በእጅጉ እንደሚያስደስታቸው ገልጿል።

በአሁኑ ወቅት ከ31 ሚሊዮን ብር በላይ በግሎባል አልያንስ በኩል ለመሰብሰብ የተቻለው፤ እነዚህ ያለፉት ስኬቶች ሕዝቡ በስራችን ላይ አመኔታ እንዲጥል በማስገደዱ ነው የሚለው ታማኝ በየነ፤ ገንዘቡን የጌድኦ ጉጂ ዞን ተፈናቃዮችን መልሶ ለማቋቋም ከተሰበሰበ በኋላ ፕሮጀክቱ በወርልድ ቪዥን አማካይነት ተፈፃሚ እንዲሆን የተፈለገው፣ ቀደም ባሉት የችግር ዘመናት ኢንተርናሽናል ድርጅቱ ከግሎባል አልያንስ ጋር አብሮ በመስራት፤ ብዙ ፈተናዎችን ከመጋፈጣቸው ባሻገር፣ "ከፖለቲካ ድርጅት ጋር ነው የምትሰሩት" በሚል ሀሰተኛ ክስ ብዙ ውጣውረዶችን በጋራ ያሳለፉ ከመሆናቸው ባሻገር፤ ከኤንጂዎች ጋር ሲሰራ ትልቅ ችግር የሆነው ኦቨር ሄድ ኮስት በሚል ሰበብ ብዙ ገንዘብ ወደ ድርጅቶች የሚሄድበትን መንገድ እነሱ ሙሉ በሙሉ በማንሳት፣ የተሰበሰበው ገንዘብ በጠቅላላ ለተጎጂዎች ፕሮጀክት እንዲውል በመፍቀዳቸው ጭምር እንደሆነ አመላክቷል።

## የግሎባል አልያንስ ቀጣይ ዕቅዶች!


ድርጅቱ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸውን እንዲታደጉ ባቀረበው ዓለም ዓቀፍ ጥሪ መሰረት በትክክል የሕዝብ ገንዘብ ሊያስብል በሚችል መልኩ የብዙዎች ቀጥተኛ ዕርዳታ ያለበት ነው ማለት ይቻላል። የጌድኦ ጉጂ ተፈናቃዮችን ለመርዳት የተሰበሰበው አንድ ሚሊየን ሶስት መቶ ሺጎ ዶላርን ያዋጡት አስራ ሰባት ሺጎ ዘጠኝ ዘጠኝ መቶ ሰላሳ ስምንት ኢትዮጵያውያን ሲሆኑ፤ ይሄም በተናጠል ሲሰላ አንድ ሰው ሰባ አራት የአሜሪካን ዶላር በእርዳታ መልክ ለግሷል ማለት እንደሚቻል የገለፁት የግሎባል አልያንስ የቦርድ አመራር አባል አቶ በትሩ የተረጂ ዜጎች ቁጥር ከፍተኛ ቢሆንም፤ የድርጅቱ ዋነኛ ዓላማ ቀድሞውኑም ሰዎቹ ከቀዬአቸው መፈናቀል የለባቸውም የሚል መሆኑ በቀጣይነት አስተማማኝ የሆነ የተረጋጋ ሕይወት እንዲመሩ ስደተኞቹን ወደ ነበሩበት መመለስ ተቀዳሚ ተግባራቸው እንደሆነ አስረድተዋል።

ሁላችንም በቀናነት ከተነሳን የነበረውን መቀራረብና ወንድማማችነት መልሶ መገንባት የማይቻልበት ምክንያት ባለመኖሩ ኢትዮጵያ ውስጥ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በእኩልነት በፍቅር በወንድማማችነትና በሰላም አብሮ የሚኖርበትን ሁኔታ ለማምጣት የሚደረገውን ጥረት ማገዝ የግሎባል አልያንስ ቀጣይ ዓላማ እንደሚሆን የተናገሩት የቦርድ አመራር ተቋሙ በቀጣይ ከውጭ ሀገር እንቅስቃሴው ባሻገር በሀገር ውስጥ በህጋዊ መንገድ በሲቪክ ማህበርነት ተመዝግቦ ህግና ደንቡ በሚፈቅደው መልክ ከምርጫ ተፎካካሪነት ውጪ ሆኖ በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ በጥልቀትና በስፋት በመስራት፤ ሕዝብን የማንቃት ስራ እንደሚያከናውን፤ በተለያዩ የሙያ ዘርፎችም ዜጎች በቂ ዕውቀትና ስልጠና እንዲያገኙ በውጭው አለም የሚገኙ ያካበተ ልምድ ባለቤቶችን በማምጣት የተለያዩ ወርክሾፖችን እንደሚያዘጋጁ ጭምር አስታውቀዋል።

ግሎባል አልያንስና ወርልደ ቪዥን የጌድዮ ጉጂ ተፈናቃችን መልሶ ለማቋቋም የቀረፁትን ፕሮጀክት በስካይ ላይት ሆቴል በተፈራረሙበት ወቅት የተገኙት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መ/ቤት ተወካይ አምባሳደረ ነጋ ደጋዮ ዓለም ዓቀፍ ትብብር ለኢትዮጵያውያ መብት ወገኖቻቸውን ከችግር ለመታደግና ዘለቄታዊ መፍትሄ ለማበጀት ዘወትር ለሚያደርጉት ቀና ትብብርና ርብርቦሽ ውስጥ መንግስት ሁሌም አስፈላጊውን ትብብር ከማድረግ ባሻገር አብሮ ለመስራት ዝግጁ መሆኑንም ገልፀዋል።

ነፃ ሃሳብ

# የማትጨርሰውን ነገር አትጀምር “ዋ”!



መታሰቢያ መልአከ ሕይወት

በዚህ አባባል ዙሪያ ለመፃፍ የወሰንኩበት ዋናው ምክንያት፣በአገራችን በሁሉም ሊባል በሚችል መልኩ የሚሰራው ሥራ፣ በፖለቲካውም ሆነ በኢኮኖሚው ያለ በቂ ጥናትና ትክክለኛ ሙያተኛ በሌለበት፤ የሚወሰኑ ውሳኔዎችና ተግባራት አገራችንን ከባድ ዋጋ እያስከፈላትና ወደ አስቸጋሪ አቅጣጫ እየመራት እንደሆነ በግልፅ እየታየ በመሆኑ ነው፡፡

ኢሕአዴግ ሥልጣን ሲይዝ በአገራችን “ዘርን መሰረት ያደረገ የፌደራል ስርዓት እገነባለሁ” ብሎ 85 ብሔረሰብ ባለባት አገር 9 ክልሎች ብቻ ሰርቶ ካቆመ በኋላ፣ ይህ ተግባር ላለፉት ሩብ ክፍለ ዘመን ከባድ ዋጋ ሲያስከፍለን ቆይቷል፡፡ ያ ማለት ኢሕአዴግ የጀመረውን ተግባር የማይጨርሠው ነው ማለት ነው፡፡

አንድ ቡድን የማይጨርሠውን ነገር ያለበቂ እውቀት ጀመረ ማለት፣ በአገርና በትውልድ ላይ ከባድ ወንጀል ፈፀሟል ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ማንኛውም በመንግስት የሚወሰን ውሳኔ በፖለቲካም ይሁን በኢኮኖሚ፣ ዞሮ ዞሮ ሕዝብን ተጠቃሚ ማድረግ አለበት እንጂ የዜጎች ዕዳ መሆን የለበትም፡፡

በብዙ ውጤታማ አገሮች በአንድ ወቅት ተወስነው ተግባራዊ የተደረጉ ውሳኔዎች፤ ማለት በሕገ መንግስት ዙሪያ፣ በፌደራሊዝም፣ በኢኮኖሚ ፖሊሲ የበርካታ ትውልዶችን ሕይወት ከመለወጣቸውም ባሻገር ለሌሎች አገሮች ትምህርት ሠጪ በመሆናቸው ብዙ አገሮች ያንን አስተሳሰብ በመድገም የአለም ሥልጣኔ እንዲፋጠን አስችሏል፡፡

እኛ አገር ስልጣን ላይ የነበሩት የኢህአዴግም ሆነ የደርግም መንግስታት የሰሯቸው ተግባራትን ብንመረምር አብዛኞቹ ተጀምረው የቆሙ ናቸው፡፡ለምሣሌ በደርግ ዘመን ከኤርትራ ጋር የተደረገው ጦርነት ያለ ውጤት የተጠናቀቀ ነበር፤ በወቅቱ በፍጥነት ወደ ፖለቲካዊ መፍትሄ መቀየር ነበረበት፡፡

በኢህአዴግ ዘመንም ሕገ መንግስቱ ላይ ያሉ አንቀፆች አብዛኞቹ ሊተገበሩ የማይችሉ ወይም ውጤት አልባ ሆነው እያለ በግትርነት እስከ አሁን ተሸክመናቸው እንድንኖር ተገደናል፡፡ በፌደራል ስርዓቱም፣ በኢኮኖሚ ፖሊሲውም የምናገኘው እውነታ ይኼንኑ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ቋንቋ ብቻ ተናጋሪ ክልል በሌለበት ሁኔታ ቋንቋን መሰረት ያደረገ ዜጎችን ለሰቆቃ፣ ለድህነት፣ ለሞትና ስደት የዳረገ የፌደራል ሥርዓት ይዘን ይባስ ተብሎ ደግሞ፣ አሁን ስልጣን ላይ ያሉት “በፌደራል ሥርዓጥ አንደራደርም” እያሉ ሌላ የችግር ዘመን እንድናሳልፍ እያወጁብን ነው፡፡ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ከሰማይ በታች ለድርድር የማይቀርብ ምንም ነገር የለም፡፡

አንድ ግለሰብ በገዛ ገንዘቡ ወይም ንብረቱ የማይጨርሰውን ነገር ቢጀምር፣ በዋናነት እራሱን ነው የሚጎዳው፡፡ አገርን፣ሕዝብን የሚያስተዳድር ፓርቲ ወይም መንግስት በምንም መልኩ ያለ በቂ እውቀትና ጥናት፣ ሕዝቦችን ለችግር ብሎም ለድህነት የሚዳርግ ውሳኔ ከመወሰን መጠንቀቅ አለበት፡፡

የሚገርመው የሚጨርሱትን ነገር በመጀመር የሚታወቁት የድሃ አገር መሪዎች ብቻ ሳይሆኑ እንደ አሜሪካ ያሉ ታላላቅ ተቋማትና ምሁራን ያሉዋቸው አገሮችም ጭምር ናቸው፡፡ ለምሳሌ አሜሪካኖች ቬትናም ሂደው ተሸንፈው ተመልሰዋል፡፡ ኢራቅ ለጦርነት ሂደው አገሪቷን አተረማምሰው፣ እራሳቸውም አምስት ሺ የሚሆኑ ዜጎቻቸውንና ወደ 900 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ገንዘብ አውድመው ወደ አገራቸው ተመልሰዋል፡፡

በአሁኑ ዘመን የምንኖር ትውልዶች በዋናነት ከታሪክ በመማር ብቻ አዲስ ነገር ለመፍጠር ምንም ወጪ ሳናወጣ አገራችንን ወደ በለፀገ ደረጃ ማድረስ እንችላለን፡፡

አሁን በአገራችን በስፋት የሚታየው ግን በውሳኔ ሰጪነት ስልጣን የያዙት ኃይሎች እንኳን አገርን የሚጠቅም ተግባር ሊያከናውኑ ይቅርና የሚናገሩትን እንኳን የማያውቁ ሁነው እያየናቸው ነው፡፡ በዕርግጠኝነት መናገር የሚቻለው ከነሱ አመራር ምንም ቁምነገር ጠብ እንደማይል ነው፡፡

ከዚህ በፊት ደጋግሜ ለማስገንዘብ እንደሞከርኩት ኢሕአዴግ በፈጠረው የፌደራል ሥርዓት የብሔሮች ማንነት እየከሰመና እየጠፋ. ድህነት እየተስፋፋ ማየት ተቻለ እንጂ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች የኢህአዴግ አብዮት ምንም ይዞላቸው አልመጣም፡፡

አንድ መንግስት የጀመረውን ነገር መጨረስ ካልቻለ ሌላ ቢቀር “በቃ ተሳስተናል፣ እዚህ ላይ አቁመን እርምት እናድርግ” ማለት በራሱ የትልቅነት ምልክት ነው፡፡

ከላይ እንደጠቀስኩት የጀመሩትን አለመጨረስ እንኳን በድሃ አገር መሪዎች፣ በሐብታም አገር መሪዎችም የተፈፀመ በመሆኑ፡፡ ለምሣሌ ጀርመኖች ሁለት ጊዜ አለምን እንወራለን ብለው እጅግ የሚዘገንን ተግባር ፈፅመው፤ መጨረሻ ሽንፈትን ተከናንበው ወደ አገራቸው ተመለሱ፡፡

በኢኮኖሚ ዘርፍ ደግሞ የጀመሩትን አለመጨረስ ብቻ ሳይሆን የጀመሩትን በተባለው ጊዜ አለመጨረስ በእጅጉ ለከባድ ኪሳራ ይዳርጋል፡፡ በአሁኑ ወቅት አብዛኛው ሊባል በሚችል መልኩ የተጀመሩ ፕሮጀክቶች ወይ ቆመዋል ወይ ደግሞ ከታቀደላቸው ጊዜ በእጅጉ ዘይግይተው ነው የተጠናቀቁት፡፡

ይህ የሚያሳየው የመንግስትን የብቃት ማነስ ነው፡፡ በአሁኑ ዘመን ያለ፣ ከዛሬ 50 ዓመት በፊት ያልነበረ ትልቁ ነገር አንዱ በአለማችን በበርካታ አገሮች የተትረፈረፈ የገንዘብ ክምችት መኖሩ ነው፡፡ ታዲያ ይህንን የተትረፈረፈ የገንዘብ ክምችት እንደ መሰረተ ካፒታል (Upfront Capital) መጠቀም የምንችለው በሕገ መንግስት ስርዓት፣ በፌደራል ስርዓት፣ በኢኮኖሚ ፖሊሲ፣ በፕሮጀክቶች አፈፃፀምና ብድርን በወቅቱ በመክፈል ብቃታችንን ማሳየት ስንችል ብቻ ነው፡፡ ከዛሬ 50 ዓመት በፊት ወደ ሥልጣኔ ያመሩ አገሮች የራሳቸውን ዜጎች ጉልበት በመዝበዝ ብቻ ነበር መሰረተ ካፒታል መፍጠር የቻሉት፡፡


የኢሕአዴግ መንግስት “አንዴ የፃፍኩትን ሕገ መንግስት አላርምም፣ የፌደራል ስርዓቱን አልቀይርም፣ የመሬት ስርዓቱን አልነካም” እያለ እስከ አሁን በድህነት አኑሮናል፡፡ የሚቀጥለው ትውልድም ሕይወት ከኛ የተሻለ ለመሆኑ ምንም ፍንጭ እየታየ አይደለም፡፡

የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ መንግስት በአገሪቱ የተወሰነ ለውጥ ለማድረግ እየሰራ እንደሆነ ሁላችንም እናውቃለን፡፡ ነገር ግን የሚካሄደው ለውጥ ስር ነቀል ካልሆነ፣ ወይም (HALF COOKED) ከሆነ ውጤቱ ከንቱ ነው የሚሆነው፡፡ ወደ አገራችን ሊመጡ የሚችሉት ባለሀብቶች በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር አውጥተው ታላላቅ የመንግስት ንብረቶች የሚገዙት በአገሪቱ በሁሉም ዘርፍ ምንም የሚያሰጋ ነገር አለመኖሩን ሲያረጋግጡ ብቻ ነው፡፡ ነገ ወይም ከነገ ወዲያ ሕዝባዊ አመፅን ልታስተናግድ የምትችል አገር የባለሐብቶችን ቀልብ መሳብ አትችልም፡፡

ኢህአዴግ ባለፉት 28 አመታት ተግቶ የሰራበት ጉዳይ አንዱ በምንም መልክ የተጠናከረ የፖለቲካ ሐይል እንዳይኖር በመሆኑ፤ አሁን ባለው ሁኔታ የኢህአዴግን ችግር እራሱ ኢህአዴግ ቢፈታው የተሻለ ይመስላል፡፡ ይህንን ማድረግ ከቻለ የሁላችንም ባለውለታ ይሆናል፤ አለበለዚያ ሁሉም ነገር የቁልቁለት መንገድ ነው የሚሆነው፡፡

ማንኛውም ሰው ወይም አገር የሚመራ ፓርቲ መጨረስ የሚችለውን ነገር ብቻ በበቂ ጥናት ጀምሮ ሌት ተቀን ሠርቶ በወቅቱ በመጨረስ እራሱንም አገርንም ተጠቃሚ ማድረግ በእጅጉ ብልህነት ነው፡፡

# የታጠፉ ጥያቄዎች


ፍቅርተ ተሾመ

አሜሪካ አመጣሹ የእናቶች ቀን የፈረንጆች 4ኛ ወር በገባ ሁለተኛው እሁድ ይከበራል፡፡ የሀሳቡ አመንጪ የሆነችው አና ጆርቪስ የእናቶች ቀን አሁን በያዘው ቅርፅ ላይ ያላትን እይታ በተደጋጋሚ ገልፃለች፡፡ ይህ አላማው እንዳልነበርና እንደሚፀፅታትም አንዲሁ፡፡

አሜሪካዊቷ አና ጃርቪስ በ20ኛው ክ/ዘመን መባቻ ያነቃቃችው ዘመናዊው የእናቶች ቀን በተለያዩ የአለም ሀገራት ከሺህ አመታት በፊት ተጀምረው ከሚከበሩት ባህላዊ የእናቶችና የእናትነት ምክንያት እና የተለየ የአከባበር ዘዬ አለው፡፡ በ1864 ዓ.ም ዳሊያ ዋርድ የተባለች አሜሪካዊት የጦር መሳሪያ ቅነሳን በመደገፍ ሴቶች በእንቅስቃሴው እንዲሳተፉና ይህን እለት ‹‹የእናቶች ቀን ለሰላም›› ተብሎ እንዲመሰረት ጠየቀች፡፡ አላማዋ በጊዜው እናትነትን መዘከር አልነበረም፤ ሆኖም እናቶች ርህሩህነታቸውን በመጠቀም ጦርነትን እንዲከላከሉ ማስተባበር እንጂ፡፡ መዘከራቸው ባልከፋ፤ በአሁኑ ሰዓት የእናቶች ቀን በአሜሪካ በሰፊው የሚከበር በዓል ሲሆን፣ ከገና ዋዜማ በመቀጠል ቤተ ክርስቲያኖች በርካታ ሰዎችን የሚያስተናግዱበት፤ የአበባ፣ የፖስት ካርድ እና ሌሎች ንግዶች በሰፊው የሚካሄድበት ጊዜ ነው፡፡

አላማው እንዴት ተቀየረ? አጀማመሩ ይዞ የተነሳው የጦርነት ወሬ፣ የሩህሩህነት ጋሻን ነው፡፡ ይህም ፖለቲካዊ ይዘቱን ያጎላዋል፡፡ ታዲያ ከንግድ አላማቸው ፍላጎት የተነሳ ይሁን ጥያቄውን ወይም ዝክሩን በአግባቡ ባለመረዳት ይዘቱን ቀይሮ ማህበራዊ ቅርፅን ብቻ ይዞ ቁጭ ብሏል፡፡ ይሄ አንድ ማህበረሰብ የሴቶችን በፖለቲካው ላይ ለሚያነሱት የተሳትፎ ጥያቄ ጆሮ ዳባ ልበስ ለማለቱ ተግባራዊ ማሳያ ነው፡፡

አና ጃርሲስ እናቷ በእርስ በእርስ ጦርነት ወቅት ከሁለቱም ወገን የተጎዱትን ሰዎች በመንከባከብ ትረዳ የነበረ ሲሆን፣ ከዚያም በኋላ የነበራትን እናቶችን የመዘከር ፍላጎት ሳታሳካ አለፈች፡፡ ልጇም አና ይህን የእናቷን ውጥን ለማሳካት ብዙ ለፍታለች፡፡ ሆኖም በዓሉ እንዳሰበችው አልሆነም፡፡ በነጋዴዎች አይን ገበያ ኖሮ በፍፁም ብስጭት ሁኔታውን በመቃወም መፀፀቷን በመግለፅ ሳትደሰትበት ህይወቷ አልፏል፡፡

## አፍሪካውያን ሴቶች በፖለቲካ

በአፍሪካ የደሃ ደሃ ከሚባሉ ሀገራት አንዷ በሆነችው ሞዛምቢክ አምና የተደረገ ጥናት እንደሚያሳየው በፖለቲካው ዘርፍ የሴቶች ተሳትፎ ከወንዶች ልቆ ይገኛል፡፡ በጥናቱ መሰረት ልዩነቱ በጣም ሰፍቶ የሚታየው የፈረንሳይ ተገዢ በሆኑ አገራት ላይ እንደሆነ ያሳያል፡፡

ሌሎች ጥናቶች ደግሞ የሴቶች ተሳትፎ በተግባር ጎልቶ የሚታይባቸው ፓርላማዎች በጎ የጤና እመርታዎችን አስመዝግበዋል፡፡ በምዕራብ አፍሪካ ሴቶች ጤናን ቅድሚያ የሚሰጡ ዋነኛ የትኩረት ቦታቸው መሆኑን አያይዞም ይጠቁማል፡፡ ጊዜ ጊዜን እየተካ አሁን ላይ ሴቶች በአለም ዙሪያ የፖለቲካ መጫወቻ ስፍራዎችን እያገኙ እንደሆነና ለውጦችም እንዳሉ የበርሚንግሃም ዩኒቨርስቲ ጥናት ማዕከል አባል የሆነችው ሶሃን ታብራራለች፡፡ ባለፈው የአሜሪካ የም/ቤት ምርጫ አዲስ የሴቶች የተሳትፎ ቁጥር አስመዝግቧል፡፡ በአፍሪካም ኢትዮጵያ ያደረገችው የሚኒስትሮች ሹመትና በግብፅ ሴቶች የፓርላማውን ወንበር 25% እንዲቆጣጠሩ በህግ አውጪዎች የቀረበው የህገ መንግስት ማሻሻያን በአብነት በማንሳት እርምጃዎችን ትጠቅሳለች፡፡

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት አፍሪካውያን ሴቶች በፖለቲካ ላይ ያላቸውን ሚና የሚያሳየው ካርታ እንደሚጠቁመው በአህጉሪቷ የአንዱ ሀገር አሳታፊነት ከሌላው ጋር ሰፊ ልዩነቶችን ያስተናግዳል፡፡ እንደ ሩዋንዳ፣ ኡጋንዳና ታንዛኒያ ያሉ ሀገራት ውስጥ ሴቶች በህግ አውጪነት ቦታ ሚዛን የሚደፉ ቁጥር አላቸው፤ በሌሎች ሀገራት ግን ይሄንን ሚዛን ማግኘት አዳጋች ነው፡፡

ሌላው የአፍሪካ ህብረት በ1995 በውሳኔ ሰጪነት ላይ የሴቶችን ተሳትፎ በማሳደግ 5 ሴቶችን 5 ወንዶችን መርጦ ነበር፡፡ አስከትሎም ሴቶችን በአመራር ቦታዎች በመሰየም ለውጦችን አሳይቷል፡፡ ይሄ ታዲያ አብዛኛው አፍሪካውያን ሴቶች የተነፈጉትን የትምህርት፣ ተቀጥሮ የመስራት እድል፣ ዝግ የሆነውን የንግድና የኢንዱስትሪ፣ የአመራር እድል ጉድለቶች መልሶ አግኝቷል ማለት አያስችልም የምትለው ዶ/ር ፋኮንዳ ሃሰን ነች፡፡

ከድህነት ለመላቀቅ አንዳንዴ ብቸኛ ቀዳዳ ሊሆን የሚችለውን ትምህርት ቤቶች መነፈጋቸው ጉዳቱ ከፍተኛ ነው፡፡ ምናልባት የሴቶች ፖለቲካዊ ተሳትፎና ከሚያጋጥሟቸው ተግዳሮቶች ጋር ያላቸው ግንኙነት ጥያቄ ይፈጥር ይሆናል፡፡ በኡጋንዳ ፓርላማ ያሉ ሴቶች ፓርላማው አስገድዶ የመድፈርን አብይ ወንጀል ሆኖ በህግ እንዲካተት ማድረግ ችለዋል፡፡

አሁን የሁሉንም አካላት ተጠያቂነት አፅንዖት መስጠት እንጂ ህልማችንን ዳግም ለድርድር ማስቀመጥ ግባችን አይደለም፡፡ የሚገቡ ቃሎችን ሳይሆን ተግባራዊነቱን እንሻለን ትላለች ወ/ት ፋኮንዳ ሀሰን፡፡

“ለአፍሪካውያን በአሁኑ ወቅት የሴቶችን መብት ጥሠት ለመዋጋት የተቀመጡ የህግ ማዕቀፎች ባለመኖራቸው ሴቶች በሀገራቸውና አህጉራቸው እድገት ላይ ስኬታማ የሆነ ተሳትፎ እንዳይኖራቸው አግዷል፡፡ በማወቅም ይሁን በቸልተኝነት ለሚሰጡት ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ መብቶቻቸው በፕሮቶኮል ጥበቃ ሊደረግለት እንደሚገባ” ወ/ት ኮፋይ ታሳስባለች፡፡

## እኩልነት

ይህ ቃል ለተለያዩ አላማዎች በተለያየ አካላት ይነሳል፡፡ ጥያቄው እየጠቆመ ያለው ከምን ላይ ሆኖ እንደሆነ ማጤን ያሻል፡፡ በሴቶች እና ወንዶች መካከል እኩልነት ይኑር ሲባል? በጠያቂውም ይሁን በተጠያቂው ግንዛቤ ማነስ ምክንያት አለመግባባቶችን ይፈጠራል፡፡ ተፈጥሮ ሰውን ሁሉ ሰው ብላለች፡፡ ሆኖም ሰው የመሆንን ክብር፤ በፆታ፣ በሃይማኖት እና በእድሜ መለያየታችን አያስነፍገንም፡፡ ግን የተነፈገ አካል አለ፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆኑ መሬት ላይ ያሉ የመብት ጥሰቶችን በማንሳት የተለያዩ የመብት ተሟጋቾች ይጠይቃሉ፡፡ ሰው የመሆንን እኩልነት እንጂ የሚመሳሰል ጥያቄ አለመሆኑን ልብ ማለት ይገባል፡፡

እነዚህ ጥያቄዎች አለአግባብ ጠምዞ የሚጠይቅባቸው ሁኔዎች መኖራቸው የማይካድ ነው፡፡ የሴቶች መብት ይከበር ሲባል ሴትን ማክበር አንዱ ንዑስ አካል ነው፤ ታዲያ አንዲትን ሴት ከቤት ውስጥ ግርፊያ እናድን ማለት እናድናት ላይ ይቆማል፡፡ እርሷኑ በአደባባይ በማስታወቂያ ሰበብ በገላዋ መነገድ የሴቶችን ጥያቄ ለግል ፍላጎት ማዋል ነው፡፡ ይሄንን እንደ መብት ጥያቄ መቁጠርም ያለውን ግንዛቤ ማነስ ያሳያል፡፡

አሁንም ቢሆን አማራጮች ሁሉ ወደዚያ እንዳያመሩ ጥያቄዎቹ መጠነ ሰፊ በመሆናቸው እና ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ስነልቦናዊ ተግዳሮቶችን ስለሚዳስሱ ትኩረትን ይሻሉ፡፡ በሁሉም ረገድ ተደራሽ የማይሆኑ እንደሆነ በራሱ የሚፈጥረው ሌላ የሰለጠነ የመብት ጥሰት መኖሩ አይቀሬ ነው፡፡

...አና ጃርሲስ እናቷ በእርስ በእርስ ጦርነት ወቅት ከሁለቱም ወገን የተጎዱትን ሰዎች በመንከባከብ ትረዳ የነበረ ሲሆን፣ ከዚያም በኋላ የነበራትን እናቶችን የመዘከር ፍላጎት ሳታሳካ አለፈች፡፡ ልጇም አና ይህን የእናቷን ውጥን ለማሳካት ብዙ ለፍታለች...

# “ቢከፍቱት ተል”ባ የሆኑ ተቋማትን እንዴት እናጠንክራቸው?



ኢዮብ ሳለሞት

ሀገራችን ኢትዮጵያ በርካታ ትውልዶች በዘመናቸው ያጋጠማቸውን ተግዳሮቶች እየፈቱ በቅብብሎሽ እያሻገሩ እዚህ ደርሳለች፡፡ ትላንትም ዛሬም ሰፊው ህዝብ ለዘመናት አብሮ ክፉ ደጉን በማሳለፍ ሀዘንና ደስታን፤ ድልና ሽንፈትን እየተጋራ አፍንጫው ሲመታ አይኑ እያለቀሰ፤ በአብሮነት እዚህ ደርሷል፡፡ ኢትዮጵያ እንደሀገር የቀጠለችው ብቁ ተቋማት ኖረው ሳይሆን በሰፊው-ሀዝብ አርቆ አሳቢነትና ጨዋነት ብቻ ነው፡፡ እሴቱ ላይ የሚዘባበቱበትን ጥራዝ-ነጠቅ ምሁራንን፤የእብድ ገላጋይ ሆነው ዱላ የሚያቀብሉትን የመገናኛ ብዙሃን ተቋማትን እና ባለሙያዎች፤ የማህበራዊ ሚዲያ አርበኞች፤ የቁጩ አክቲቪስቶችን፤ ቅቡልናቸውን አሽቀንጥረው በጣሉ የሃገር-ሽማግሌዎች ቅሌት ልቡ እየቆሰለ፤ በፈሪሳዊያን የሃይማኖት ተቋማት ቆሽቱ እየደበነ፣ በየአቅጣጫው አንድነቱ፤ አብሮነቱ ላይ የሚወረወሩበትን ፍላፃዎች እየ መከተ አፍራሽ ቅስቀሳዎችን ጆሮ ዳባ ልበስ በማ ለት ሀገር አንደሀገር አንድትቀጥል አደርጓል፡፡

የፍትህ ተቋማት የጥቂት ግለሰቦችና ቡድኖች ፍላጎት ማስፈጸሚያ ሆነው ክስ እንደ ልቦለድ እየተደረሰ ዜጎች መናኸሪያቸው ወህኒ ሲሆን፤ በበሉበት የሚጮሁ ሚዲያዎች የግለሰቦችን ተክለ-ስብእና ሲክቡና ሲንዱ የሚያድሩ፤ እርማቸውን አጀንዳ ቀርጸው አወያይተው፤ ገንዘብ አስጨብጠው፤ ማህበራዊ ንቃተ-ህሊና አዳብረው የማያውቁ፣ ነጋ ጠባ በማህራዊ ሚዲያ በሚሯሯጡ፣ በሬ ወለደ የባልቴት

> ...ከህዝብ ግብር ተለቅሞ ያለንን ተፈጥሮአዊ ሀብቶች በመንከባከብ የገቢ ምንጭ ያደርጋሉ የተባሉት የባህልና ቱሪዝም ቢሮ የዱርና ደን ባለስልጣን መ/ቤት፤ የአደጋ መከላከልና ቅነሳ ዝግጁነት ቢሮ፣ በአካባቢ ጥበቃ ላይ የሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች..ወ.ዘ.ተ የማንን ጎፈሬ ሲያበጥሩ እንደሚውሉ አልገባንም....

ወሬዎችን እንደገደል ማሚቶ ሲደግሙ የሚውሉ ሙያዊ እውቀት፤ ክህሎት፤መረጃ አጠገባቸው ድርሽ ብሎ የማያውቅ፤ በዚህ ሽግግር ግዜ እንደመገናኛ ብዙሀን ባለሙያና ተቋም ሚናቸውን ያልለዩ በኮክቴልና በአበል ያበዱ ሆነዋል፡፡

ምናለበት አሁን እንደ ደራሲ ብርሃኑ ዘርይሁን አይነት ንቃተ-ህሊናዉ የዳበረ፤ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴዎችን አስተሳስሮ ለሰፊው ህዝብ በሚጥቅም መልኩ በደርዝ በደርዝ ትርጉም ሰጥቶ ለታሪክም፤ ታሪክ ለመስራትም በሚያመች መልኩ ይሄን የሽግግር ወቅት ፈትፍቶ የሚያጎርሰን ባለሙያ ቢገኝ፡፡ ‹የአብዮት ዋዜማ፤የአብዮት መባቻና የአብዮት ማግስት› በሚል ርእስ ዛሬ ነበር መተንተን የነበረበት ፡፡

የለውጡ የተሃድሶ አመራር ያገኘው ህዝባዊ ቅቡልና ተሸርሽሮ ሳያልቅ በተሰጠው ውሳኔ ሰጪነት አቅም በመጠቀም፤ ህዝብ ህዝብ የሚሸቱ አካታች፤አቃፊ፤ አሳታፊ አሰራሮችን በፍጥነት ዘርግቶ የማህበረሰቡን ፍላጎት ማርካት አለበት ሚዲያ፡፡ ይሄ ጨዋና አስተዋይ ማህበረሰብ ከሰማይ መና ይውረድልኝ፤ወርቅ አንጥፉልኝ ብሎ አያውቅም፡፡ መጀመርያ መቀመጫዬን ነው ያለው፤ ለዘመናት በጋብቻ ፤በመዋለድ፤አብሮ በመኖር ያደበራቸውን እሴቶች ላይ የዘመቱትን ጽንፈኞችና፤ አክራሪዎች መንግስት አደብ ያስገዛልን ነው የሚለው፡፡ በዋነኝነት የመንግስትን አስተዳደራዊ መዋቅሮችን ተገን ተድረጎ የሚፈፀሙ፣ ማንነትን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች፤ማፈናቀሎች፤ ዘረፋ ይቁም ነው እያለ ያለው፡፡

ጠርቶ የማይጠራው የመንግስት መዋቅር በመደመር መፈክር ቀልባሾችን አግበስብሶ በራሱ ላይ ካራ እየመዘዘ ነውና በምንጥር ዘመቻ ታችኛውን መዋቅር ያጥራ ነው የሚለው፡ ፡ ዜጎች ሀገር አማን ነው በማለት የእለት ተእለት እንቅስቃሴያቸውን በሚያካሄዱበት ወቅት ደንገተኛ የሞት ድግስ አይጠብቀን ነው የሚሉት፡፡ እንደዚህ አይነት የታሪክ፤የባህል፤የተፈጥሮ ሃብታም፤ የነቃ ማህበረሰብ ተይዞ ወደፊት አለመሻገር ትዝብት ነው ፡፡ ወቅታዊ ተግዳሮታችንን ለመፍታት የሁሉም ተሳትፎ፤አበርክቶ፤ጽናት፤ቆራጥነት የሚያስፈልግበት ወቅት ላይ ደርሰናል፡፡

ቅድሚያ የሀገራችንን አንገብጋቢና በአፋጣኝ ምላሽ ሊሰጥባቸው የሚገቡ ቁስሎች፤ፈተናዎችን ፤መከራዎችን መለየት፤ አባባሽ ነገሮችን ማስወገድ ፤የስጋት ቀጠናዎችን ለይቶ የቅደመ-ጥንቃቄ ስልቶችን መቀየስ፤ ከአቅም በላይ የሆኑ ቸግሮች ሲከሰቱ በፍጥነት ለመቆጣጠር የሚስችል ብቁ የሰለጠነ የሰው ሃይል ከተደራጀ ቀላል አሰራር ጋር መዘጋጀት አለበት፡፡ በሰሜን ተራሮች ብሄራዊ ፓርክ የተነሳው ቃጠሎ ቢከፍቱት ተልባ የሆኑ ተቋሞቻችንን ገበና ነው ገልብጦ ያሳየን፡፡ ከህዝብ ግብር ተለቅሞ ያለንን ተፈጥሮአዊ ሀብቶች በመንከባከብ የገቢ ምንጭ ያደርጋሉ የተባሉት የባህልና ቱሪዝም ቢሮ የዱርና ደን ባለስልጣን መ/ቤት፤ የአደጋ መከላከልና ቅነሳ ዝግጁነት ቢሮ፣ በአካባቢ ጥበቃ ላይ የሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች..ወ.ዘ.ተ የማንን ጎፈሬ ሲያበጥሩ እንደሚውሉ አልገባንም፡፡ እንደዚህ አይነት አደጋዎችን የመከላከልና የመቆጣጠር ተግባራትን ካላከናወኑ የሚመደበው በጀት በስልጠና፤በወርክሾፕ፤ በአበል፤በኮክቴል ድግስ ሲባክን ነው የሚውለው ማለት ነው፡፡

በዚህ አጋጣሚ የኬንያ መንግስት የጉርብትና ሚናውን ስለተወጣ፤ የእስራኤል መንግስት ፈጣን ምላሽ ስጥቶ ስለታደገ፤ በሰፊው ህዝብ ስም ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡ በማህበራዊ ደረ-ገጽ ላይ በጎጥ አስተሳሰብ ተመርዛችሁ ብሄራዊ ፓርካችንን የአንድ ክልል ጉዳይ አድርጋችሁ መርዘኛ የጠለሹ ሀሳቦችን ስትሸጡ የከረማችሁ አካሎች፤ ምኞታችሁ መቼም እውን አይሆንም፡፡ አሁን ያስቸገሩን ህዝብ “የእኔ ወኪል ናችሁ” ብሎ እውቅና ሳይሰጣቸው የብሄር፤የቋንቋ፤የእምነት ለምድ ደርበው ወኪል ነኝ ብለው፤ በየአደባባዩ በህዝብ ጥቅሞች ላይ የሚደራደሩትና የግል እንጀራቸውን የሚያበስሉት ናቸው፡፡

ህዝብ ሆይ በብሄርህ፤በቋንቋ ፤በእምነትህ፤ በባህል ተንተርሰው የሚቀሰቅሱህን ጆሮ ዳባ ብለህ ውግንናህን በችግር-ፈቺ አመለካከት ፤አማራጭ ፖሊሲ ታግለው የሚያታግሉህን፣ ትከሻህን ያጎበጠውን ሸክም የሚያራግፉልህን፣ ልብህን ከፍተህ ስጥ፡፡ በቁስልህ እንጨት እየሰደዱ የራሳቸውን ድስት የሚያበስሉትን አንቅረህ ትፋቸው፡፡ አንገትህን ዞር አድርገህ አካባቢህን ቃኝ፡፡ አለም-አቀፉ ማህበረሰብ ምን እንደደገሰልህ ተረዳ፡፡ አሁን ግዜው በውሃ ቀጠነ የምንነታረክበት፤ጥቃቅን ክፈተቶችን እየሰነጠቅን የምንጨቃጨቅበት፤ “የእናቴ መቀነት አደናቀፈኝ፤ የለሁበትም፤አልነበርኩም”...ወ.ዘተ የምንልበት ወቅት ሳይሆን ሁላችንም የበኩላችንን ድርሻ እየተወጣን ሀገር እንደ ሀገር የምትቀጥልበት ሁኔታ ላይ በጋራ የምንሟሟትበት ፤የምንዋደቅበት ግዜ ላይ ደርሰናል፡፡ አበርክቶ ለማድረግ የፕሮፌሰርነት ካባ መደረብ፤ስመጥር ዝነኛ ፤የመንግስት ስልጣን መያዝ፤ በርካታ ቲፎዞ ያለው መሆን አይጠበቅብንም፡፡ እያንዳንዳችን ባለን ውስን አቅም ፤ክህሎት ፤እዉቀት ፤መረጃ አንድ ቀዳዳ መደፈን እንችላለን፡ ፡ እንደግለሰብ፤እንደተቋም፤እንደፓርቲ ሚናችንን ለይተን ድርሻችንን እንወጣ፡፡



ተስፉ (ኢትዮጵያ) አሊታሰብ

# ምክንያታዊነት ለኑሮአችንና ለፖለቲካችን

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል በ11993 ዓ.ም ባሳተመው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ላይ ምክንያት ለሚለው ቃል ትርጓሜውን ሲያስቀምጥ አንድ ነገር ሊሆን፤ሊፈፀም፤ሊደረግ የቻለበት ወይም የሚችልበት መሰረተ ነገር፤ሳቢያ፤ መነሻ ማለት ነው ይለዋል፡፡ እንግሊዝኛው ዲክሽነሪ ደግሞ ምክንያታዊነት እንዲህ ይተረጉመዋል፡ ፡ (Rational comes from the Latin word rationalis, meaning reasonable or logical. If you're rational, you do things based on logic, as opposed to impulse or whimsy.) በዚህ ትርጓሜ መሰረት ማንም ሰው አንድ ሁኔታ ሊፈፀም የቻለበትን ምክንያትና የመሰረተ ነገር መነሻ ምንነት በሚገባ አብጠርጥሮ ለማወቅ ጥረት ማድረግና ወደ አንድ መደምደምያ ሀሳብ መድረስ ሲሆን፤ እንዲህ አድርጎ ወደ መደምደሚያ የሚደርስን ግለሰብ ምክንያታዊ ብለን ለመጥራት አንቸገርም፡፡ አንድ ጉዳይ ወይም ሀሳብ በፌስ ቡክ ስለተለቀቀ ብቻ፤ብዙ ሰዎች ስለ ጉዳዩ ስለተናገሩ ብቻ፤ ዝም ብሎ የነገሩን ስረ መሰረት ሳያጠራ፤ሳያኝክና ሳያላምጥ እንዳለ የሚቀበልና የሚውጥ ከሆነ ይህን ግለሰብ ኢ-ምክንያታዊ እንለዋለን፡፡

ምክንያታውያን ግለሰቦች ባነበቡትና በሰሙት ነገር ብቻ አይነዱም፡፡ በሰሙትና ባነበቡት ብቻ ፈጥነው ሰው አይጠሉም፤ ፈጥነው አይፈርጁም፤ ፈጥነው አያደንቁም፤ አያንኳሱሱም፡፡ ምክንያታውያን ግለሰቦች ስለተነገረው ነገር፤ የነገሩን ጅማሬና የውሉን መጨረሻ አንገዋለው፤ አበጥረውና ለቅመው ከጨረሱ በኋላ ነገሩን ለማመንም ሆነ ለመቀበል፤ ለመቃወምም ሆነ ለመተቸት ይነሳሉ፡፡ ምክንያታውያን ሰዎች በዚህ ዘመን ለኑሮአችንና ለፖለቲካችን በጣም ጠቃሚዎች ናቸው፡፡ በሀገራችን ለረጅም ዘመናት የኑሮአችን እና የፖለቲካችን ቁስል አልሽር ያለን ምክንያታዊ (Rational) ሰዎች ስላነሱን ነው፡፡ በፍልስፍና መስክ ኢትዮጵያዊው ፈላስፉ ዘርዓያዕቆብ፣ የባህልና የወግ አስተሳሰቦችን ትችት በማዳበር በማህበረሰቡ ውስጥ ምክንያታዊነትና ማህበረሰባዊ ፍትህ እንዲሰፍን ሀተታ የተሰኘ ስራውን ለማቅረብ ሞክሯል፡፡ ነገር ግን የሚፈለገውን ያህል ባህል ሆኖ መቀጠል አለመቻሉ፤በሀገራችን ኢ-ምክንያታውያን በዝተው ሀገራችንን የመከራ ገደል አፋፍ ላይ አድርሰዋታል፡፡

ምክንያታዊ (Rational) በሆነ መንገድ የሌሎችን የንግግርና የሀሳብ ነፃነት ማክበር ተገቢ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ በምክንያታዊነት የተደገፈ የሰላ ትችት ሲቀርብ በፀጋ መቀበል የግድ መሆን አለበት፡፡

በምክንያታዊነት የሚያምን ማህበረሰብ በመፍጠር ለዜጎች ነፃነት የሚታገል፤ ማኅበረሰባዊ ትችትን የሚቀበልና ፈጥኖም የሚያርም ማህበረሰብ በቀላሉ መፍጠር ይቻላል፡፡ እርግጥ ነው ትችት በምክንያታዊነት ከተደገፈ ገንቢና አስተማሪ ነው፡፡ የሌሎችን መብት አይጥስም፡፡ ምክንያታዊ (Rational) በሆነ አካሄድ የተለያዩ ሐሳቦች ለንግግር ነፃነት ክብደት መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ ደስ የሚለንን የምንሰማውን ያህል የሚጎረብጠንንም ቢሆን በምክንያታዊ (Rational) መርህ መሰረት እንዲሰማ ጠበቃ መሆን እንችላለን፡፡ ዛሬ ለፖቲካችንና ለኑሮአችን እንዲሁም ለአገራችን የጋራ ጉዳይና ለብሄራዊ መግባባት፤ ለብሄራዊ እርቅ የሚያስፈልገውም ይህ አካሄድ ብቻ ነው፡፡ በጠላትነት እየተያዩ፣ አጥፊና ጠፊ ሆነን በኢ-ምክንያታዊነት ኑሮን መምራትና ፖለቲካን ማራመድ ለዚህ ዘመን አይመጥንም፤ አይጠቅምም፡፡

ምክንያታዊነት የህዝባችንን እሴትና ሞራላዊ ጉዳዮች ከመጠበቅ አንፃር ለእውነትና ለፍትሕ ወግኖ ከመቆምና ከመቆርቆር፣ ከመቻቻልና ከመከባበር፣ ሰውን በሰውነቱ ከመመዘንና ዋጋ ከመስጠት ጋር ይቆራኛል፡፡ በአንፃሩ በኢ-ምክንያታዊነት ዘርን፣ ቋንቋን፣ ሃይማኖትን፣ ፆታን፣ ወዘተ… መሠረት አድርጎ በሰዎች መካከል ልዩነት መፍጠር፣ ጉዳት ማድረስ፤ መፈራረጅና መጠቃቀም ወይም በእነዚህ ልዩነቶች ላይ በመመርኮዝ መጠቃቃት ይስተዋላል፡፡ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የምንመለከታቸው ጉዳዮች እንደ ሰው ባህሪይ፤ ሰው ከምክንያታዊነት እርቆ የእንስሳነትን ባህሪይ ተለብሶ ሲንቀሳቀስ በግልፅ እየተመለከትን ነው፡፡ ይህ አይነት አካሄድ ለሰው ልጆች በተፈጥሮ የተቸረውን የማሰብና የተፈጥሮ ግኝትም ይፃረራል፡፡

በሀገራችን አሁን እየተፈጠሩ ያሉ ችግሮች ሁሉ መነሻ ምንጫቸው በትውልዱ ውስጥ የምክንያታዊነት አስተሳሰብ መጓደል ነው፡፡ ትውልዱ የሚሰራውን ስራ ሁሉ በምክንያት ካደረገው፤ ለአንዳንድ የሀገራችን ችግር ፈጣሪ ሀይሎች ለሚፈልጉት ስውር ዓላማ ዝም ብሎ የሚታዘዝላቸውና በነሲብ የሚሰለፍላቸው፣ እንደ ጋሪ የሚነዳላቸው አይሆንም፡፡ ይልቁንም ብርቱ ትውልድ ሆኖ በሀሳብ ይሞግታቸዋል፡ ፡ ምክንያት ይጠይቃል፡፤ ይከራከራል፤ ለምን ብሎ ይጠይቃል፡፡ የሚወስዳቸው ማንኛውም ውሳኔዎቹ የሚመሠረቱት በዕውቀትና በብስለት ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ይሆናል፡፡

ከእውነት ውጪ በምክንያታዊነት አንድ ግለሰብ ዝም ብሎ በቃልም ይሁን በማህበራዊ ሚዲያ ስለነገራቸው ብቻ የተወሰዱ የተሳሳቱ እርምጃዎች በርካታ ችግሮች ተከስተዋል፡ ፡ ለምሳሌ ብንወስድ ምንም ጥፋት ባልሰሩ ሁለት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የዶክትሬት ተማሪዎች በመስክ ጥናት ላይ እያሉ በኢ-ምክንያታዊ ግለሰቦች ባልዋሉበት ድርጊት ተገድለዋል፡፡ ምንም አይነት ቦምብ በእጁ ያልተገኘበት የሻሸመኔው ልጅ በኢ-ምክንያታዊ ግለሰቦች ያለ ጥፋቱ በወገኖቹ መሀል ተዘቅዝቆ ተሰቅሏል፡፡ በኢ-ምክንያታዊ ግለሰቦች እና የፀጥታ ሀይሎች ተዘቅዝቆ የተሰቀለውን ወጣት ማዳን እንኳን ሳይቻል ቀረ፡፡ ያለ ጥፋታቸው በብሄራቸው ብቻ በኢ-ምክንያታዊ ግለሰቦች ህይወታቸው የጠፋ፣ ንብረታቸው የወደመና የተዘረፈውን ቤታቸው ይቁጠረው፡፡

በምክንያታዊነት ላይ ተደግፎ በማንም ላይ የትችትም ሆነ የድጋፍ ሀሳብ ማቅረብ ይቻላል፡፡ ነገር ግን ትችትም ሆነ ድጋፍ ከመሰንዘሩ በፊት የሌላውን ወገን ሀሳብ በደንብ ማብላላትና መመርመር፤ እውነታውን አስቀድሞ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ እንዲያ ሳይሆን ቀርቶ በግልብና በነሲብ የተነገረውን ዝም ብሎ ሳያኝኩና ሳያላምጡ ለመዋጥ መሞከር፤ እንዲሁም ሀሳብ ለመስጠት መፍጠን ምክንያታዊ (Rational) የመሆን ባህሪን ያሳጣናል፡፡ ለአላስፈላጊ ጉዳትም ይዳርገናል፡፡

እዚህ ላይ አንድ ምሳሌ ልጥቀስ፤ በቅርቡ በዚህ በግዮን መፅሄት ላይ የእኔ ያልሆነ ፅሁፍ በእኔ ስምና ፎቶ ታትሞ ለህዝብ ቀርቦ ነበር፡፡ አንድ እኔን የሚያውቅ ወዳጄ ፅሁፉን አንብቦ እኔን ለመተቸት ይሁን ለመደገፍ በጉዳዩ ላይ የራሱን ግላዊ እይታ ለመፃፍ ፈልጎ፤ወደ እኔ ደውሎ ግዮን ላይ የወጣውን ያንተን ፅሁፍ አነበብኩት እና በፃፍከው ፅሁፍ ላይ የግሌን አስተያየት ለማስቀመጥ ስለምፈልግ ካንተ በጉዳዩ ላይ ተጨማሪ ሀሳቦችን እፈልጋለሁ አለኝና ቀጠረኝ፡፡ ወዳጄ አስተያየት ሊሰጥበት የፈለገውን ፅሁፍ ሲያሳየኝ፤ በስህተት በኔ ስምና ፎቶ የታተመውን ፅሁፍ ነበርና፤ይቅርታ ወንድሜ ይህ ፅሁፍ የኔ አይደለም፡፡ በአጋጣሚ በህትመት በተፈጠረ ስህተት የወጣ ነው እና በሚቀጥለው ሳምንት በራሱ በግዮን መፅሄት ላይ እርማት ይሰራል አልኩት፡፡ ይህ ወዳጄ በሳልና ምክንያታዊ (Rational) ሰው መሆኑን ተረዳሁ፡፡ ምክንያቱም ዝም ብሎ ድጋፍም ይሁን ትችት ከመፃፉ በፊት የነገሩን ስረ መሰረትና እውነቱን ለመረዳት ተጨማሪ ▶

ሀሳብና እውነትን ለመፈለግ ብዙ መድከሙን አደነቅኩ፡፡ ግዮን መጽሄትም ሙያውና የጋዜጠኝነት መርህ በሚፈቅደው መሰረት በቀጣይ ህትመት ላይ ስህተት መፈጠሩን አምኖ እርማቱን ሰራ፡፡ ወዳጄም እርማቱን ካየ በኂላ ደውሎ ያንተ መስሎኝ ዝም ብዬ ብፅፍ እፀፀት ነበር አለኝ፡፡ ወደጄን አደነቅኩት፤ ምክንያታዊ (Rational) ያልሆነ ሰው ቢሆን ኖሮ የእኔ ባልሆነ ፅሁፍ ድጋፍም ይሁን ወቀሳ ሊፅፍ ነበር፡፡ እኔም ለወደፊቱ ለሌላ ሰው መልስ ከመስጠቴ በፊት ስረ መሰረቱን በደንብ መመልከት እንደሚኖርብኝም ከምክንያታዊው ወዳጄ ብዙ ተማርኩኝ፡፡

ስለዚህ ሁሉ ግዜ ለምናነሳቸው ጉዳዮች በድጋፍም ይሁን በተቃውሞ ሀሳብ ከማቅረባችን በፊት እና ወደ ውሳኔ ከመድረሳችን በፊት በምክንያታዊነት ነገሮችን ዘልቀን በጥልቀት መመርመር ይገባናል፡፡ ሁሌ ምክንያታዊ ስንሆን ከግጭት፣ ከንትርክ፣ በጭፍን ከመጠላላት፣ ጠመንጃ ከማንሳት፣ ከመገዳደልና ከመጎዳዳት እንድናለን፡፡ የሚያስፈልገን በምክንያታዊነት (Rational) የሐሳብ ልዕልናና የአስተሳሰብ የበላይነት ይዞ መገኘትን ባህል አድርገን መያዝ ይኖርብናል፡፡

ምክንያታዊ (Rational) ባልሆነ መንገድ ለዘመናት አብረው ክፉና ደግ እያዩ አብረው የኖሩ ኢትዮጵያውያንን በብሔር በመከፋፈል ለማፋጀት መሞከር የጭካኔ ድርጊት ነው፡፡ ሰብዓዊ ፍጡርን እንደ አውሬ አድኖ ከመግደል ጀምሮ በዘር ለይቶ ከመጨፍጨፍ የበለጠ ነውረኛና አረመኔያዊ ድርጊት የለም፡፡ ሕፃናትን፣ አረጋውያንን፣ ነፍሰ ጡሮችን፣ እመጫቶችን፣ አቅመ ደካሞችንና ለፍቶ አዳሪዎችን ያለ ጥፋታቸው በጭካኔ ደማቸውን እያፈሰሱ የሚገድሉትን ያለ ምንም ማመንታት ሕግ ፊት መገተር ይገባል፡፡ በኢ-ምክንያታዊ አካሄድ ዜጎች በገዛ አገራቸው እንደ ባዕድ እንዲሳደዱ የሚያደርጉም ሆነ፣ ድርጊቱን በዝምታ የሚያዩ ሹማምንትና የሕግ አስከባሪዎች ጭምር በሕግ መጠየቅ አለባቸው፡፡ ያኔ ነው ኢ-ምክንያታዊነት ለምክንያታውያን ቦታውን የሚያስረክበው፡፡ ዝም ብሎ ከታየና ከታለፈ በቁጥር ጥቂት ኢ-ምክንያታውያን በበርካታ ምክንያታውያን ላይ ድርብ በደል በቀጣይነት ሊፈፅሙ ይችላሉ፡፡

በሀገራችን አሁን እያየነው ያለነው የችግሮች ሁሉ መነሻውም፣ ምንጩም በምክንያታዊነት ላይ ያልተመሠረተ ጭፍን ጥላቻ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ስሜትን አግሎና አንሮ እዚህም እዚያም አሳፋሪ በሆነ መንገድ ሕይወት እንዲጠፉና ዘግናኛ ጥፋት እንዲደርስ አድርጓል፤ እያደረገም ይገኛል፡፡ ይህ ኢትዮጵያውያን ለዘመናት ካዳበሩት አብሮ የመኖር ባህልና የማኅበራዊ ሕይወት መስተጋብር በእጅጉ ተፃራሪ የሆነ ነገር ነው፡፡ ምክንያታዊ ሰዎች ምንጊዜም በስሜት አይመሩም፤ ሲወዱም ሆነ ሲጠሉ በምክንያት ነው፡፡

አንዳንዶች ምክንያታዊ (Rational) ባልሆነ መንገድ ለፍትሕ እንቆማለን እያሉ ለኢ-ፍትሐዊነት በአደባባይ ከበሮ ሲደልቁ ማየት ያማል፡፡ ትናንት የመንግሥትን ተገቢ ያልሆኑ ድርጊቶች የተቃወሙ፣ ተመሳሳይ ድርጊቶች ሲፈጸሙ መቃወም ካቃታቸው ምክንያታዊ የመሆን ችግር አለ ማለት ነው፡፡ የመርህ ሰዎች ሲቃወሙም ሆነ ሲደግፉ ምክንያታዊ ሆነው ነው፡፡ በምክንያታዊ (Rational) በሆነ በጨዋነት አካሄድ እየተነጋገሩ ስህተቶችን መተራረም የሚጠቅመው ሕዝብንና አገርን ነው፡፡ ምክንያታዊ ሆኖ መነጋገር ሲያቅት ነው በየሥፍራው ግጭት እየተቀሰቀሰ ንፁኃን ሰለባ እየሆኑ የሚገኙት፤ የአገር አንጡራ ሀብት የሚወድመው፡፡

ምክንያታውያን ለውይይትና ለድርድር፣ እውነትን ለመረዳት በጣም ቅርብ ናቸው፡፡ ለመተቸት አይቸኩሉም፡፡ የሚቸኩሉት እውነትን ለማወቅ፣ የተደበቀን ለመግለጥ ነው፡፡ አንድን ግለሰብ ወይም ፓርቲ ለምን ደገፍከው ተብሎ ጥያቄ ሲቀርብ በብዙዎች የሚሰጠው ምላሽ ምክንያትነቱ አሳማኝ አይደለም፡፡ እንዲያውም ብዙ ግለሰቦች ስለሚደግፉት ፓርቲ ዓላማና ፖሊሲ በቂ ግንዛቤ የላቸውም፡፡ ከጥቂቶች በስተቀር፤ ስለ ደገፉት ሆነ ስለተቃወሙት ግለሰብና ፓርቲ ጥልቅ ጉዳዮች አንብበውም ይሁን ጠይቀው የማያውቁም ናቸው፡፡ ምክንያታዊ (Rational) የሆነ ደጋፊ ግን አንድን ፓርቲ የሚደግፍበትን፣ የሚቃወምበትን የነገሩን ስረ መሰረት እና መነሻ ሀሳብ በደንብ አውቆ ነው ለውሳኔ የሚደርሰው፡፡ አንዳንዶች እገሌን ፓርቲ ወይም ግለሰብ የወደዱበት ወይም የደገፉበትን መንገድ የሚያስቀምጡት በምክንያት ሳይሆን በጥራዝ ነጠቅ ነው፡፡ እንደነዚህ አይነት ግለሰቦች በምክንያታዊ የሐሳብ የበላይነት እስካልተሸነፉና እንደ ሕዝብ ነገሮችን ሰከን ብለው፣ የነገሩን ስረ መሰረት የመመርመር ባህል እስካላዳበሩ ድረስ፤ በተሳሳቱ መንገዶች ተጉዘን ችግር ውስጥ ስላለመክረማችን ምንም ዋስትና የለንም፡፡

በዚህ በ21ኛው ክ/ዘመን እየኖርን የምንገኝ መሆናችንን ማመላከቻው ጥራት ያለው ምክንያታዊ ሐሳብ መያዛችን መሆኑን በሚገባ መረዳት ይኖርብናል፡፡ ጥራት ያለው ሐሳብ ለማግኘት ደግሞ የተለያዩ ምክንያታዊ (Rational) ሐሳቦች በነፃነት የሚወዳደሩበትን ዓውድ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ይህ ዓውድ ሊኖር የሚችለው ደግሞ በሰላማዊና በዴሞክራሲያዊ መንገድ፤ በምክንያታዊነት ፊት ለፊት መነጋገር ሲቻል ብቻ ነው፡፡ ለምሳሌ ከብሄርና ከዜግነት ፖለቲካ የትኛው ይሻላል ብሎ ለመነጋገርና ለመደማመጥ ሀሳቡን ወደ ህዝቡ ወስዶ በሎጂክ እና በምክንያት ለማሳመን ጥረት ማድረግ እንጂ፤በአንድ ክልል የሚገኝ የብሄር ፖለቲካ መሪ የዜግነት ፖለቲከኞች ወደ ክልላችን እንዳይገቡ የሚል ከሆነ፤ ይህ ግለሰብና የፖለቲካ መሪ ምክንያታዊነት የሚጎድለውና በዚህ በ21 ኛው ክ/ዘመን እየኖረ፤ እንደ 21ኛው ክ/ዘመን ማሰብና መኖር ያልቻለ የፖለቲካ መሪ ነው የሚሆነው፡፡ አዲሱን ትውልድ ምክንያታዊ እንዲሆን የመቅረፅ ኃላፊነት የተጣለበት የፖለቲካ መሪ ዝም ብለው የሚነዱትን «ደጋፊዎቹን» ሰብስቦ ግጭት የሚቀሰቅስ፤ከክልሌ አስወጣ ብሎ የሚለቅብህ ከሆነ፤ መታዘዝ ያለበት በኢ-ምክንያታዊ ተነጂ «ደጋፊዎቹ» ሳይሆን በኢ-ምክንያታዊው የፖለቲካ መሪ ተብየው ነው፡፡ አንድ የፖለቲካ መሪ ይህን ማድረግ አቅቶት አገር ችግር ውስጥ እንድትገባ ሲያደርገ ማየት በዚህ ክ/ዘመን አሳፋሪ ድርጊት ነው፡፡

ምክንያታዊ (Rational) ሰዎች ሲበዙ ሞጋች ሐሳብ ይዘው መቅረብ ይችላሉ፡፡ ትውልዱን በዕውቀት ማነፅ ኢ-ምክንያታዊ ሰዎችን ከአውዱ ለመቀነስና ሞጋቹን ለማበራከት ይረዳል፡፡ በመንግሥት፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም በተቋማት ላይ የሰላ ትችት ማቅረብ የሚቻለው የዳበረ ዕውቀት ሲኖር ብቻ ነው፡፡ በመንጋ ፖለቲካ አገር መምራት ውጤት አያመጣም፡፡ ከመንጋ ፖለቲካ የሚገኘው ውጤት ምናልባት ከተሳካ ጊዜያዊ ድል እንጂ፣ ለሀገርና ለህዝብ ዘለቄታዊና አስተማማኝ የሆነ ድል አያመጣም፡፡ ስህተትን በስህተት ለማረም መሞከር ከሕዝብ ጋር ደጋግሞ ያጣላል፡፡

ለአንድ አገር ምክንያታዊ ፖለቲከኛና የፖለቲካ መሪ የሚባለው የተለያዩ ሐሳቦች የሚቀርቡበት ገበያ ላይ ተገኝቶ የፖለቲካውን ፖሊሲና የፕሮግራም አቋሙን በማሳየት፣በግልጽነት፣ በነፃነትና በተፎካካሪነት ስሜት ከሚቀርቡ የፖለቲካ ኃይሎች ጋር ተገናኝቶ የርሱን አላማና አስተሳሰብ በኃላፊነት፣ በጥንቃቄና በሰላማዊ መንገድ ለማቅረብ ዝግጁ የሆነ ማለት ነው፡፡ ምክንያታዊ ፖለቲከኛ የማንንም ሀሳብ አይፈራም፡፡ የሌላውን ሀሳብ እንዳይደመጥ በሰፈሩ አጥር አያበጅም፡፡ ኢ-ምክንያታዊ የሆኑትን፣ ዝም ብለው የሚነዱትን «ደጋፊዎቹን» አነሳስቶ ግጭት አይፈጥርም፡፡ ምክንያታዊ (Rational) ወጣት ደግሞ በማህበራዊ ሚዲያ የሚቀርበውን ጉዳይ ማን እንደተናገረው ወይም እንደጻፈው ሳያውቅ፣ የነገሩን ስረ መሰረት ሳያጠና ለግጭትና ለሁከት ዝም ብሎ እንደ ከብት የሚነዳ አይሆንም፡፡

ምክንያታዊ (Rational) ወጣት ዝም ብሎ ማንም አድርግ ያለውን እሺ ብሎ የሚያደርግ አይደለም፡፡ ማን ነው ያለው? ለምን አለ? እንዴት አለ? ውጤቱ ምን ያመጣል? ብሎ በደንብ የስረ ነገሩን መነሻ ከምንጩ ይመረምራል፤ያጣራል፡፡ ሁሉን መመርመርና መርምሮ መቀበል የምክንያታዊ ሰዎች መለያ ባህሪ ነው፡፡ ምክንያታዊ አስተሳሰብ ያለው ሰው በሐሳብ ልዩነት ውስጥ መኖር ይችላል፡፡ በምክንያታውያን መንደር የተለያዩ ሐሳቦች ጠብና ግጭት ሳያስፈልጋቸው በነፃነት የሚፎካከሩበት አውድ ነው፡፡ የሚቀርቡት ማናቸውም ሐሳቦች በሙሉ ለሕዝብ የህሊና ዳኝነት የሚቀርቡ በመሆናቸው፣ በሰላማዊና ጨዋነት በተሞላበት መንገድ ከሕዝብ ብያኔ የሚጠብቁ ናቸው፡፡ ምክንያታዊነትና ፖለቲካችን ዘልቆ እንዲሄድ፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በሀገራችን እንዲገነባ የጨዋታ ሕጉን ጠንቅቀው በሚያውቁ የፖለቲካ ተፎካካሪዎችና ደጋፊዎች የተሞላን ሊሆን ይገባል፡፡ የፖለቲካ መጫወቻ ሜዳው ሁሉንም አሳታፊ እንዲሆን ደግሞ ሁሉም ለሕግ የበላይነትና ፖለቲካችን ደግሞ ለምክንያታዊነት ቦታውን አምኖ መልቀቅ አለበት፡፡ ይህ እንዲሆን ደግሞ ሁሉም ዜጋ እኔ ምክንያታዊ ነኝ (I'm Rational) የሚል ዘመቻ እንደ ሀገር በጋራ ማድረግ ስንችል ብቻ ነው፡፡

*ኢትዮጵያ በክብር ለዘላለም ትኑር!!*

# የሴትነት ተግዳሮቶች ጀግና

*ሲኤንኤን ቴሌቭዥን ጀግኖቼ ብሎ ሶስት ኢትዮጵያውያን ሴቶች ይዞ ወጥቷል፡፡ አንዷ የኬሚካል ኢንጂነሪንግ ምሩቋና የ54 ዓመቷ ፍሬወይኒ መብራቱ ነች፡፡ ሲኤንኤን ስራዎቿን እና የጀግንነት ሀሳቦቿን እንዲህ ዘግቦታል፡፡*



ፍሬወይኒ የወር አበባዋን ያየችው በ13 ዓመቷ ነበር፡፡ በጣም የሚረብሽ አጋጣሚ ነበር፤ በጣም አዝኜ ነበር ትላለች፡፡ ይሄ ነገር እርግማን ነው፤ ለትዳር ዝግጁ ነኝ ማለት ነው፤ በቃ መጥፎ ነኝ ማለት ነው? የሚሉ ሀሳቦች ሲነገር ከምሰማው ተነስተው መጡብኝ፡፡

በሰሜን ኢትዮጵያ እንደ አብዛኛው ሴቶች ሁሉ በዝምታ ተሰቃይታለች፡፡ ለእናት እና እህቷ እንኳን ልትናገር አልደፈረችም፡፡ ንፅህናዋን መጠበቂያ ምርቶችንም የማግኘት እድል አልነበራትምና ብጣሽ ጨርቆችን ነበር የምትጠቀመው፡፡

“አንድ ጊዜ ክፍል ውስጥ ሆኜ መጣብኝ በጣም ፈርቼ እና አፍሬ ነበርእስካሁን የተሰማኝን ስሜት አስታውሰዋለሁ” ትላለች የ54 ዓመቷ ፍሬወይኒ፡፡

ፍሬወይኒ የኬሚካል ኢንጂነሪንግ ትምህርቷን ልትማር ወደ አሜሪካ ካቀናች በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1977 ዓ.ም ወደ አንድ የአሜሪካ መድኃኒት ቤት ስትገባ የነበረውን ስታስታውስ “ከበቂ በላይ የሆኑ የንፅህና መጠበቂያዎችን ሳይ ጥያቸው የመጣሁትን እነዚያን ሴቶች አሰብኩ” ትላለች፡፡

በኢትዮጵያም ይሁን በሌሎች የአለም ክፍላት የወር አበባ እስካሁንም እንደ ነውር ይቆጠራል፡፡ እንደ ዩኒሴፍ መረጃ በጠቅላላው ርዕሰ ጉዳዩ በትምህርት ገበታ ላይ የሚሰጥ አይደለም፡፡ በዚህ ላይ ሴቶች ለውይይት የሚመርጡት ጉዳይም አይደለም፡፡ የአንድ ጊዜ አገልግሎት ያላቸው የንፅህና መጠበቂያ ምርቶች በጣም ውድ ናቸው፤ አንዳንዴም አይገኙም፡፡ ስለዚህ ወደ 85% የሚጠጉ ኢትዮጵያውያን ሴቶች በራሳቸው መንገድ ካልተወጡት በቀር እነዚህን ምርቶች የማግኘት እድል የላቸውም፡፡

በኢትዮጵያ በአማካይ ከ10 ሴቶች አንዷ ከወር አበባ ጋር በተያያዘ ከትምህርቷ ትቀራለች፡፡ በአንድ አንድ የገጠር አከባቢዎች በ50% ይጨምራል፡፡ ከትምህርት መቅረታቸው ወደ ኋላ እንዲቀሩ የሚያደርጋቸው ሲሆን፣ ይህ ደግሞ ትምህርቱን እንዲያቋሙትም በሂደት ተፅዕኖ ያሳድርባቸዋል፡፡

ፍሬወይኒ አንድም ሴት በወር አበባ ምክንያት ከትምህርት ገበታዋ መቅረት እንደሌለባት ታምናለች፡፡ በመሆኑም ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ 800,000 ሴቶችን በስራዋ ተደራሽ አድርጋለች፡፡

ለወትሮ በተለምዶ ሴቶች የወር አበባ ጊዜያቸውን ብጣሽ ጨርቅና ሳሮችን በመጠቀም ያሳልፋሉ፡፡ የፍሬወይኒ ምርቶች ባለገበርና ከጥጥ የተሰሩ ሲሆኑ፤ ውሃን የማያሳልፍ፣ የሚመጥ ሆኖ የተሰፋና ሙሉ በሙሉ የሚታጠቡ ናቸው፡፡ ለጥንቃቄ አያያዝ እንዲያመች ተደርጎም ተሰርቷል፡፡ ከሌሎቹ የአንድ ጊዜ አገልግሎት ከሚሰጡት ምርቶች ጋር ሲነፃፀር የ90% የዋጋ ቅናሽ ያለው ሲሆን፣ በአግባቡ እና በጥንቃቄ ከተያዘ ለሁለት አመታት ያገለግላል፡፡

ከ80% በላይ የሚሆነው ምርት መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የሚሰራጭ ሲሆን እነርሱም በነፃ ያከፋፍሉታል፡፡

ፍሬወይኒ በት/ቤቶች ውስጥ ለአመታት ለወር አበባ የተሰጠውን መጥፎ ስም ለመቀየር እያስተባበረች ቆይታለች፡፡ “አጠቃላይ አላማው የንፅህና መጠበቂያዎችን ማምረት ብቻ አይደለም፤ በጣም ገደብ ነበረብኝ ምክንያቱም ብቻዬን ነበር የምሰራው፡፡”

አሜሪካዊው pobsletnies እና gyneology ዶ/ር ስዊስ ዋሌን ከገኘች በኋላ ሁኔዎች ተለወጡ፡፡ በ2016 ምን ያህል እንደሰራች በተመለከቱ ጊዜ በመደነቃቸው ከባለቤታቸው ጋር በመሆን ስራዋን ለመደገፍ ዲግኒቲ ፔሬድ (Dignity period) ያለ ትርፍ የሚሰራ ተቋም መሰረቱ፡፡

በአሁኑ ወቅት ከመቀሌ ዩኒቨርስቲ ጋር በመሆን ድርጅቱ የፍሬወይኒን ጥረት በበለጠ አስፋፍቶታል፡፡ እስከ ዛሬ ድረስ ከ300.000 በላይ ለሆኑ ተማሪዎች የወር አበባ ተፈጥሮአዊና የማያሳፍር መሆኑን በተለያዩ ትምህርታዊ ወርክሾፖች ግንዛቤ አስጨብጧል፡፡

ትምህርቱን ለሴቶች ብቻ በመስጠት ሳይሆን ወንዶችንም በማካተት የማህበረሰቡን አስተሳሰብ እያሻሻልን ነው፤ ዲግኒቲ ፔሬድ 50 000 ነፃ የንፅህና መጠበቂያዎችን ከፍሬወይኒ በመግዛት አከፋፍሏል፡፡ በዚህ ቡድን በተሰበሰበ መረጃ ተደራሽ በተደረጉ ት/ቤቶች ውስጥ የሴቶች በትምህርት ገበታ ላይ የመገኘት አሃዝ በ14% መጨመሩን ያሳያል፡፡

*ፍሬወይኒን ጀግና አድርጎ የሰየማት ሲ.ኤን.ኤን ከጋዜጠኛዋ ካትሪን ቶነር ጋር ያደረገችው ቆይታ ከታች ቀርቧል፡፡*

**ሲኤንኤን፡- ከምርቶቹ ባለፈ ፋብሪካውስ የሴቶችን ህይወት ለማሻሻል ይረዳል?**

ፍሬወይኒ መብራቱ፡- ለእኔ ምርቶቹ በሴቶች ለሴቶች መሰራቱ አስፈላጊ ነው፡፡ ዛሬ ላይ 43 ሴቶችን ቀጥረናል፡፡ ምርጡን ምርት በመስራት ሂደት ውስጥ ክብሩን እነርሱ ይወስዳሉ፤ ሴትን በኢኮኖሚ ራሷን የቻለች እንድትሆን መርዳት አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ ነፃ ስልጠናዎችን፣ ተጨማሪ ክፍያዎችን፣ ነፃ የእረፍት እድል እና የእድገት እድሎችን እንሰጣለን፡፡

አራት የወሊድ የእረፍት ወር የምንሰጥ ሲሆን፣ ነፃ የህፃናት ማዋያ ማዕከልም በማቅረብ ስራቸውን እየሠሩ ልጆቻቸውን ያለ ስጋት ያሳድጋሉ፡፡ ለሰራተኞች ነፃ የህፃናት መዋያ ማቅረባችን ቀዳሚ ያደርገናል፤ ይኸው አሁን ሌሎችም የሚተገብሩት ፖሊሲ ሆነ፡፡ አላማዬ እነርሱን በህይወት መርዳት ብቻ አይደለም፡፡ ህይወትን የበለጠ ማሻሻል እና በማህበረሰቡ ውስጥ ልዩነትን መፍጠር እንዲማሩም ነው፡፡

**ሲኤንኤን፡- ፋብሪካው ንፅህና መጠበቂያ ዎቹን ብቻ ነው የሚያመርተው?**

ፍሬወይኒ መብራቱ፡ ፓንቶችንም ከንፅህና መጠበቂያዎቹ ጋር እናመርታለን፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ሴቶች ፓንት እንኳን የላቸውም፡፡ ይህ 21ኛ ክ/ዘመን ነው፡፡ አሁን ትልቁ ደንበኞችን ዲግኒቲ ፔሬድ ነው፡፡ በተጨማሪነት 4 የንፅህና መጠበቂያዎችን እና 2 ጥንድ ፓንቶችን እንሰራለን፡፡ ይሄ አንዲት ሴት በት/ቤት ውስጥ ያለ ስጋት እንድትቆይ ያደርጋታል፡፡ ለዲግኒቲ ፔሬድ በ144 ብር ገደማ እንሸጥላቸዋለን፡፡ በአንድ መቶ ብር የአንድን ሴት ህይወት ቀየርን ማለት ነው፡፡

**ሲኤንኤን፡- ይሄ “የወር አበባ ትክክለኛነት” መርህ በቅርብ አመታት ውስጥ ትኩረትን ያገኘ ሆኗል፤ አንቺ ስትጀምሪው ምን ይመስል ነበር?**

ፍሬወይኒ፡- በ2005 ዓ.ም ስጀምረው ማንም የሚያወራበት ጉዳይ አልነበረም፡፡ ትግል ነበር ገንዘብ ለማግኘት እንኳን አመታት ፈጅቶብኛል፤ ምክንያቱም ማንም ይገዛዋል ብለው ስላላሰቡ መሰረታዊ ፍላጎት መሆኑን ማሳመን ነበረብኝ ቀላል አልነበረም አንድ ሰው ይሄን ማድረግ አለበት እኔ ካላረኩ ማንም አያረግም ብዬ አሰብኩ፡፡”

ዶ/ር ዋልን ማግኘቴ ጨዋታውን ቀየረልኝ፡፡ እርሱ እርዳታ ለሚያቀርብላቸው ሴቶች ልዩ ፍቅር አለው፤ ወኔን የሚጨምርልኝ ነበር፡፡ የሌሎች ጉዳይ የእኔን ያህል ያገባኛል ከሚሉ ሰዎች ጋር አብሮ መስራት ያስደስታል፡፡ እንደዚህ ያለ በህይወቴ ላደርግ የምችለው ነገር በምንም መንገድ አይኖርም፡፡ የተቻለውን ያህል ሴቶች ጋር መድረስን እሻለሁ፡

## የጽንፈኝነት . . .

◀ ከገጽ 6 የዞረ

አመለካከት ተደማጭነቱ ከፍተኛ ነበር:: በመሆኑም ርዕዮተዓለሙ ካፒታሊዝምና ሊበራሊዝምን የሚያንቋሽሽ ብቻ ሳይሆን ከአብዮትና ከአብዮታዊነት ውጪ ክብርም ጀግንነትም የለም የሚል ሥነ-ምግባራዊ መርህ ፈጥሯል፤ በተለይም በወጣቱ ዘንድ:: ለምሳሌ የከበረ ሁሉ በዝባዥ ተባለ:: እንዲሁም ከላይ እንደተገለፀው ኮንሰርቫቲቭ መሆን በወግአጥባቂነት፣ ሪፎርሚስት መሆን በጥገኝነት ተተረጎሙ:: ይህ የሚያሳየው ርዕዮተዓለሙ የነበረው ከፍተኛ ግብረገባዊ እሴት ለተለዋጭ ማንኛውም አስተሳሰብ ውስጣዊ እንቅፋት እንደሆነ ነበር::

3) የኢትዮጵያ ተማሪዎችና ምሁራን ይህን ርዕዮተዓለም በቀላሉ እንዲቀበሉ ያደረጋቸው ሌላው ምክንያት ከሩሲያና ቻይና መሪ ሲሺያሊስት አገሮች ጋር የኃይለ ሥላሴ ሥርአት የነበረው የታሪክ ተመሳሳይነት ነው:: ሩሲያና ቻይና ፊውዳሊዝምን ያጠፉት በሶሺያሊስታዊ አብዮት እንደመሆኑ ሁሉ ኢትዮጵያም ተመሳሳይ ሥርአት ስላላት በተመሳሳይ መፍትሄ መጠቀም አለባት ወደሚለው ደምዳሜ በቀላሉ ተደርሷል::

እዚህ ላይ መሰመር ያለበት ለማርክሳዊ ሌኒናዊ ፍልስፍና አለማቀፋዊ ተቀባይነትና የሩሲያና ቻይና ለኢትዮጵያ ምሳሌ መሆን መንገዱን ያመቻቸው በዘመናዊነት ስም የመጣው የምዕራባዊያን ትምህርት መሆኑ ነው:: የዚህ ትምህርት አንዱ መሰረት የሥነ ታሪክ አቀራረብ እንደሆነ ይታወቃል:: የሚለውም የሰው ልጅ ታሪክ የሚሄደው በአንድ መስመር ነው፤ እሱም ከኃላቀርነት ወደ ከፍተኛ ሥልጣኔ ነው:: ከፍተኛ ሥልጣኔ ላይ የሚደረሰው በአንዴ ሳይሆን ደረጃ በደረጃ ነው:: በመሆኑም ከፍተኛ የሥልጣኔ ደረጃ ላይ የደረሱት ምዕራባዊ አገሮች በመሆናቸው በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ ሕዝቦች ሁሉ የእነሱን ፈለግ መከተል አለባቸው:: ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፣ ለእነዚህ ሕዝቦች ከኃላቀርነት መላቀቅ ዋናው ቁልፍ የምዕራባዊያኑን ሥልጣኔና የበላይነት መቀበልና መቅዳት ነው::

ዘመናዊነት የምዕራቡን ሥልጣኔ መቅዳት ነው የሚለው ግንዛቤ ጠልቆ በመግባቱ ነው የኢትዮጵያ የተማሪዎችና ምሁራን አመለካክት ሁሌም ወደ ውጪ የሚያየው፤ ክዚህም አልፎ መመሪያውን ሁሌም ከውጪ የሚፈልገውና የሚያገኘው:: ይህ ለአገሩ እንግዳ የሆነ አስተሳሰብ የተማረው ክፍል የማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተዓለም በጊዜው የነበረውን ዓለምአቀፋዊ የበላይነትና የሩሲያና ቻይና ታሪክ አርአያነት በቀላሉ ካለምንም ሂሳዊ ጥናት እንዲቀበል አድርጎታል:: የተማረው ክፍል የዓለም የተለያዩ ሥልጣኔዎች በአንድ ታሪክ አቅጣጫ፣ ማለትም በምዕራባዊ ታሪካዊ ፈለግ ውስጥ መጠቃለል የለባቸውም የሚል እምነት ላይ ደርሶ ቢሆን ኖሮ፤ ግራ ከተጋባ ቀጂነት ወደ ፈጣሪነት በመሸጋገር ኢትዮጵያዊ የሆነ ዘመናዊነትን ማመንጨት በተቻለ ነበር::

## የኢትዮጵያ ልሂቃን አሉታዊ ገጽታዎች


ከላይ የተዘረዘሩት የአክራሪነት ምንጮች የኢትዮጵያ ልሂቃንን ብልሹ ባህሪያት የሚያስረዱ ብቻ ሳይሆን አገሪቱ ከገባችበት መቀመቅ መላቀቅ ለምን እንዳልቻለችም ያብራራሉ:: የተማረው ክፍል በአግባቡ ሕዝቡን እየመራ ወደ ዘመናዊነት ማሸጋገር የተሳነው ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ በመብዛቱ ነው:: ከላይ የተገለጸው የአስተሳሰብ ውጫዊ ምልከታ ጠባይ ከአገሩ ተጨባጭ ሁኔታ ተነስቶ ለችግሮች ተመጣጣኝና ተስማሚ መፍትሄዎችን ከመፈለግና ከመፍጠር ይልቅ የውጪውን መቅዳት ይቀለዋል:: ለምሳሌ የኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ የተቀረጸው በምዕራባዊ የቅኝ አገዛዝ ታሪክ መነጽር ነው:: ከሰሜን የመጡ የሴም ሕዝቦች (ሐበሻ) የደቡብን ሕዝቦች የቅኝ ግዛት አደረጓቸው ይባላል:: ይህ ከውጪ የተወሰደ ታሪክ ነው ለዘውጋዊ ፖለቲካና የመገንጠል ፍላጎት መሰረት የሆነው:: ሌላው መመልከት ያለብን፤ ይህ ወደ ውጪ የዞረ አስተሳሰብ ሁሌም የውጪውን ያደንቃል፣ ሁሌም የውስጡን ያጥላላል:: ይህ ደግሞ የተወረሱትን እሴቶችና እምነቶች እንዲናቁ ስለሚያደርግ ሁሉን ነገር ደምስሰን አዲስ ሕብረተሰብ እናምጣ የሚለውን አጥፊ አስተሳሰብ ይጋብዛል:: በአገሩ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ መፍትሄ አጥፊ እንጂ አልሚ ሊሆን አይችልም:: በሌላ አባባል፣ የተመረተው የተማረ ክፍል ቀጂና የመፍጠር ችሎታ የሌለው ነው:: ካለው ሁኔታ (ማለትም ካለው ሥርዐት፣ ባሕልና እምነቶች) አለመነሳቱ አጥፊ እንጂ ገምቢ እንዳይሆን ያደርገዋል:: የሚያደንቀው የውጪውን ስለሆነ ነው ያለውን አጥፍተን አዲስ ማህበረሰብ እንገንባ የሚለውን አክራሪ አቋም የሚይዘው::

የምዕራባዊ ትምህርት አንዱ ውጤት የተማረውን ክፍል የገዛ አገሩን አሠልጣኝ፣ ቅኝ ገዢ ያደርገዋል ብለናል:: በመሆኑም ይህ ሕዝቦችን ከኃላቀርነት የማላቀቅ ትልዕኮው ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው ሁሉ ነገር ከላይ ወደ ታች ሲሄድ ነው:: የሚፈለገው የሕዝብ ተሳትፎ ሳይሆን ሙሉ ታዛዥነት ብቻ ነው፤ ምክንያቱም ሕዝብ አልተማረም፣ አያውቅም:: ይህ የዘመናዊነት ንደፈ ሐሳብ የሚጠይቀው የተማከለ የፖለቲካና የኤኮኖሚ ሥርአት ብቻ ሳይሆን የሥርአቱ አሰራር አምባገነናዊ መሆኑንም ነው:: ሥርአቱ ለሕዝብ የሚለው፣ የሚበጅህን የማውቅልህ እኔ እንጂ አንተ አይደለህም ነው:: በአጭሩ፣ የምዕራባዊ ትምህርት የተማረው ክፍል የገዛ አገሩን ቅኝ ገዢ ሆኖ እንዲያስብና እንዲሰራ አድርጎታል::

ይህ ሥልጣንን የመማከል አዝማሚያ ከማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተዓለም ጋር የጠበቀ ዝምድና አለው:: የሌኒናዊ እጅግ የተማከለ አሰራር የሚያሳየው ሁሉን ነገር ወደመንግሥት ሥር ማምጣት፣ መንግሥትን ደግሞ ፓርቲ ሥር ማድረግ፣ ፓርቲን በተራው ፖሊት ቢሮ ሥር ማምጣት እንደሆነ እውቅ ነው:: ይህ ጸረ ዲሞክራሲያዊ አሰራር ሕዝብን ነጻ ለማውጣትና ከኃላቀርነት ለማላቅቅ የሚበጀውን የምናውቀው እኛ ብቻ ነን የሚል ነው::

ወደ ውጭ የዞረ አመለካከት ከዘውጋዊነት ጋራ የማይጣጣም ሊመስል ይችላል:: ምክንያቱም ዘውጋዊ ፖለቲካ ለአንድ ዘውግ ጥቅም፣ ቋንቋና ባሕል ቆሚያለሁ ስለሚል:: ጠጋ ብለን ስንመለከት ግን፣ ዘውጋዊ ፖለቲካ ከአምባገነናዊነት ፍላጎት ጋር ተሳስሮ እናገኘዋለን:: ቀደም ብለን እንደገለጽነው፣ የማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተዓለም ያወረሰን ሁሉን ነገር ከተቃርኖ አንጻር ማየት እንደመሆኑ፤ መደቦች እንደሚቃረኑ ሁሉ የዘውጎችም ግንኙነቶች የተመሰረቱት በቅራኔ ላይ ነው:: ሁሉን ነገር ከቅራኔ አንጻር ማየት በስምምነትና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ሥርአት ማቋቋም እንዳይቻል ያደርጋል:: ፖለቲካ ማለት ተቃራኒ የተባለውን ዘውግ ማጥፋት ወይም በበላይነት መግዛት ነው:: ይህ ደግሞ ሕዝብን ከሕዝብ የሚያጋጭ ብቻ ሳይሆን ልሂቃን በወገን እንዲከፋፈሉና ለበላይነት እንዲታገሉ ያደርጋቸዋል:: ይህ አመለካከት ከዴሞክራሲያዊ አሰራር ጋር አብሮ እንደማይሄድ ጉልህ ነው::

የመደብ ትግል ጽንሰ ሐሳብ ላብአደሩን ከሌላው የሕብረተሰብ ክፍል፣ በተለይም ከከበርቴው ጋር ያቃርናል:: ዘውጋዊነትም የአንድ ዘውግ ተጠሪና ተቆርቋሪ እኔ ብቻ ነኝ፣ ሌላው ሁሉ ጠላት ነው ይላል:: ሁለቱም የተለያዩ ጥቅሞች ልሂቃን እንዲጻረሩ ያደርጋሉ፤ ሁለቱም ማስማማትን ሳይሆን የማጥፋት ወይም የበላይነት የማግኘት አሠራርን ስለሚያስከትሉ ከመሰረታቸው ጸረ ዴሞክራሲያዊ ናቸው:: በመሆኑም ኢትዮጵያን ወደ ሰላም፣ ዴሞክራሲና ብልጽግና መውሰድ የሚቻለው ከእንዲህ ዐይነት አስተሳሰብ በመላቀቅ ነው:: ይህ ደግሞ እውን ሊሆን የሚችለው መቃረን ትተን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ እንዳሉት መደመር ስንጀምር ነው:: ምክንያቱም ዘውግን መጻረር መልሶ ቅራኔያዊ አስተሳሰብ ውስጥ ይከተናልና:: ስለሆነም ውጤታማው አሠራር፤ ዘውግን የሚጻረረውን ሳይሆን የዘውግን ፖለቲካዊ መሳሪያነት የሚያዳክሙ ዴሞክራሲያዊና የአስተሳሰብ ለውጦችን በሂደት ማከማቸት የሚሻውን ፖለቲካዊ አማራጭ መከተል ነው::


ጥላሁን መሸሻ

# በሀገራችን የመጣው ለውጥ ግቡን ይመታ ዘንድ መደራጀት ግድ ይላል

ባለፉት ጥቂት መጣጥፎቼ ኢትዮጵያ ዊነትን፣ የዘር ፖለቲካ አጥፊነትን፣ የብሔር ጥያቄ ጊዜው ያለፈበትና የንዑስ ከበርቴ እንጂ የሕዝብ አለመሆኑን ወዘተ ለማስረዳት ሞክሬ ነበር። ሆኖም በዘር ላይ የተመሰረተው የፖለቲካ ስርዓት በብሔር ጥያቄ ስም፣ ላለፉት 27 ዓመታት ጭቁን ብሔር ብሔረሰቦች በሚል ሰበብ ሲሰራ የቆየው ሕዝብን የመለያየት የሴራ ፖለቲካ ምንም ዓይነት የሶሺዎ-ኢኮኖሚክ አናሊስስ ያልተሰራበትና በዕውር ድንብር ሲጓዝ የኖረ፤ ዓላማውም የአንድ ብሔር የበላይነትን ለማስፈን እንደነበር ይታወቃል። ይህ ሁኔታ ዓለም ያወቀው፣ ፀሐይ የሞቀው በመሆኑና በ27 ዓመቱ የፖለቲካውም ሆነ የኢኮኖሚው ተዋናይነት የመሰከረው፣ ብዙ የተፃፈበት፣ ብዙ የተደሰኮረበት ስለሆነ በዚህ ጉዳይ ዝርዝር መረጃ ማቅረብ አይጠበቅብኝም። በኢኮኖሚው ውስጥ የነበሩትን ተዋናዮች፣ በፖለቲካው ውስጥ የነበሩትን የስልጣን አደረጃጀቶችና ቅርምቶች በበቂ ሁኔታ ያየናቸው ስለሆነ በዚህ ፅሑፍ ያን ስርዓት ወደ መተንተንና ማብራራት ውስጥ መግባት አስፈላጊ አይሆንም።

በመሰረቱ ይህችን ትንሽ ጽሑፍ ለማቅረብ የፈለኩበት ምክንያት አሁን በአገራችን በመከናወን ላይ ያለው ወይም አለ ተብሎ የሚወራለት ለውጥ በውዥንብር ባህር ውስጥ እየዋኘ ያለ፣ አቅጣጫውም ሆነ ግቡ ምን እንደሆነ ያልታወቀ በመሆኑ፤ አንድም የለውጡ ባለቤትና መሪ (በርግጥ መሪ ነኝ የሚለው ኃይል) እየመራ ያለውን ለውጥ አቅጣጫና ግብ በመርሃ ግብር ደረጃ በግልፅ አስቀምጦ የለውጥ ሂደቱን በአግባቡ እንዲመራ፣ ሕግና ስርዓትን ባስከበረ መልኩ አቅጣጫ እንዲያሲይዝ፣ የሕዝብንና የሀገርን ደህንነት እንዲያስከብር አለበለዚያም የፖለቲካና ሶሺዎ- ኢኮኖሚክስ ምሁራን ባላቸው የማህበራዊ ሳይንስ ዕውቀት ላይ ተመርኩዘው ግልፅና ሳይንሳዊ ትንታኔ በመስጠት አሁን ካለንበት ውዥንብር እንዲያወጡን፤ (መቼም በማኅበራዊ ሳይንስ ጥናት ውስጥ አንዱን ከሌላው የሚለይና ለማኅበራዊና ፖለቲካዊ መፍትሄ የሚሰጥ ተሞክሮ ከታሪክ አይታጣምና) ለማሳሰብ ነው፡ ፡ ይህን ለማለት ያሳሰበኝን ምክንያት ደግሞ እንደሚከተለው እገልፃለሁ።

የፖለቲካ ለውጥ የሚመጣው በሁለት መንገድ ነው። አንዱ ከላይ ወደታች ሲሆን፣ ሁለተኛው ከታች ወደላይ ነው። ዓይነቱ ደግሞ እንደዚሁ ሁለት ነው። አንዱ ጥገናዊ ለውጥ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ስርነቀል ለውጥ ነው። እነዚህ የለውጥ ዓይነቶች በሀገራችን ከዘመነ ደርግ ጀምሮ የሚምታቱና ራሳቸውን በራሳቸው ጠልፈው እየጣሉ፣ የንደፈ ሃሳብና የአቅጣጫ ውዥንብር እየፈጠሩ ኢትዮጵያን ከአንዱ አብዮት ወደ ሌላው አብዮት ሲያላጉት ኖረዋል፤ አሁንም እያላጉት ይገኛሉ። በዚህ ምክንያት ኢትዮጵያ መሄድ የሚገባትን መንገድ ሳትለይ፣ መከተል የሚገባትን አቅጣጫ ሳታውቅና ሕዝቡ ደግሞ ማግኘት የሚገባውን ለውጥና ዕድገት ሳያገኝ ሀገርና ሕዝብ በማዕበል እየተናጠች እንደምትጓዝ መርከብ ለዘመናት ሲንገላቱ ይኖራሉ። እኔ ይህ ቋጠሮ ዛሬ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ሊፈታ ይገባል ብዬ አምናለሁ። ሀገርም እንደሀገር ከማይረባ ንትርክ ወጥታ ስልጣኔዋን፣ ዕድገቷንና ብልፅግናዋን መገንባት ይኖርባታል።

> የለውጡ መሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ ለውጡን የሚያዩት በጋራ ስምምነት የሚካሄድ፣ በለውጡ መግባባት ላይ ተደርሶ ስራው እንደተጀመረ፣ ነገር ግን በኋላ የተወሰኑ ሰዎች ፀረ ለውጥ ሆነው እንደቆሙና "ቅን ልቡና የራቃቸው ሰይጣናዊ መንገድ የሚከተሉ" መሆናቸውን ነው። የጥገናዊ ለውጥ ሀሳብና የተግባር ስርነቀልነት ተቀላቅሎ ለለውጥ መሪ ነኝ ባዩ ቅን መሳይ ቀለም፣ በለውጡ ለተነካው ጎራ ደግሞ የጥቃት ስሜትን አላብሷል

አሁን በኢትዮጵያ መጣ የምንለው ለውጥ ከላይ ተነስቶ ወደታች እየሄደ ያለ ለውጥ ነው። ከላይ ወደታች የሚመጣ ለውጥ ደግሞ በባህሪው ጥገናዊ ነው። ሂደቱም አዝጋሚ ከመሆኑ የተነሳ ከለውጡ ጥቅም ባሻገር ያለው ጉዳት ብዙ የሚሰማ አይደለም። እንዲህ ዓይነት የለውጥ ሂደት ጉዳቱም ሆነ ጥቅሙ ብዙ ሳይሰማን በረጂም የጊዜ ማዕቀፍ ፖለቲካንና ኢኮኖሚን ለውጦ የሕዝብንና የሀገርን ጥቅም ያስከብራል። በዚህ ምክንያት ለውጡን ከሚቃወሙት ይልቅ የሚደግፉት በእጅጉ የበዙ ናቸው። በታሪክ እንዲህ ዓይነቱ ለውጥ የተከናወነው በአሜሪካና በምዕራብ አውሮፓ ነው። አሁን በኛ ሀገር መጣ የምንለው ለውጥ ደግሞ እንዲሁ ጅምሩ ከላይ ቢሆንም መሰረቱ ግን ከታች በገነፈለ የህዝብ አመፅ ነው። አካሄዱ ደግሞ መሰረታዊ ወይም ደግሞ ስርነቀል ሆኖ ፈጣንና ስፋት ያለው፣ የሀገሪቱንም ፖሊሲና ሕዝቡን በጥልቀት ሊነካ የቻለ ሆኗል።

በዚህ ለውጥ የተቃውሞ ጎራ የቆመውም ኃይል ቀላል አይደለም። በዚህ ምክንያት ይህ ለውጥ ከጥገናዊ ይልቅ ወደአብዮታዊ ባህሪ ያዘነበለ ነው። አብዮታዊ ለውጥ ደግሞ ጠላትና ወዳጅ አለው። ነገር ግን የለውጡ መሪዎች የሰሩት ስራ ስርነቀል ሆኖ ሳለ እነርሱ ግን የሚያስቡት ጥገናዊ ለውጥ እያከናወኑ እንደሆነ ነው። ጥገናዊ ለውጥ ሳይሆን የቻለበት ምክንያት ደግሞ ትልቁና የአንዣዡ ቁንጮ የሆነውን አካል በአይዲዮሎጂም ሆነ በስልጣን የነካ ስለሆነ ነው። የኢሕአዴግ ስርዓት ፈጣሪና መስራች ዋና ኃይል የሆነው አካል ደግሞ ሳይወድ በግድ ስልጣኑም ሆነ ጥቅሙ ተነክቷል። በዚህም የተነሳ ይህ ኃይል አኩርፏል፣ ልክ መፈንቅለ መንግስት እንደተካሄደበት ያህል አድርጎ ወስዶታል፤ ክህደት ተፈፅሞብኛል ብሎም ያምናል፤ ፀረ ለውጥም ሆኖ በተቃራኒ ቆሟል፤ ለውጡንም ለማጨናገፍ እየሰራ ይገኛል።

የለውጡ መሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ ለውጡን የሚያዩት በጋራ ስምምነት የሚካሄድ፣ በለውጡ መግባባት ላይ ተደርሶ ስራው እንደተጀመረ፣ ነገር ግን በኋላ የተወሰኑ ሰዎች ፀረ ለውጥ ሆነው ▶

እንደቆሙና “ቅን ልቡና የራቃቸው ሰይጣናዊ መንገድ የሚከተሉ” መሆናቸውን ነው፡፡ የጥገናዊ ለውጥ ሀሳብና የተግባር ስርነቀልነት ተቀላቅሎ ለለውጥ መሪ ነኝ ባዩ ቅን መሳይ ቀለም፣ በለውጡ ለተነካው ጎራ ደግሞ የጥቃት ስሜትን አላብሷል፡፡ በአጠቃላይ ይህ ለውጥ በዛ ስርዓት ተጠቃሚ በሆኑ የሁሉም ብሔር ብሔረሰብ አባላት ላይ ቀላል የማይባል የፀረ ጥቅም ዱላ አሳርፏል፡፡ በጅብ ቆዳ የተጠረዘ ክራር ቅኝቱ እንብላው፣ እንብላው ነው ይባል የለ! ስለዚህ ምናልባት ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያልተረዱት በዚህ ለውጥ ፊት በመቆማቸው ቀላል የማይባል ጠላት እያፈሩ መሆናቸውንና በየትኛውም የሀገሪቱ ከፍልና ቀበሌ ለውጡ እንዳይሳካ የሚሰሩ ኃይሎች መፈልፈላቸውንም ጭምር ነው፡፡ ፀረ ለውጥ እንቅስቃሴውም እንዲሁ ተቋማዊ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ይህን ሁኔታ ያለመመርመር ወይም እያወቁ መናቅ ለእርሳቸው አደጋው ቀላል ካለመሆኑም በላይ በታሪክ ተጠያቂ ሊያደርጋቸው፣ የማይረሳም ፀፀት ሆኖባቸው ሊያልፍ ይችላል፡፡

ክቡር ጠ/ሚኒስትር! ለዚህ መፍትሄው ታዲያ ሕዝቡን የለውጡ ባለቤትና ተሳታፊ ማድረግ፣ ማደራጀት፣ ሕገ መንግስቱ የሚሰጥዎትን ስልጣን መጠቀምና ስራ ላይ ማዋል፣ ፀረ ለውጥ ሥራ የሚሰሩ ኃይሎችን ያለማመንታትና ያለመዘግየት በሕግ ተጠያቂ ማድረግ፣ ሕዝቡ የለውጡን ግንዛቤ እንዲያገኝ ማድረግና ማደራጀት፣ ለውጡንም የተደራጀና ተቋማዊ ማድረግ ነው፡፡ ለዚህ ሥራ አስፈላጊ የሆኑት የመንግስት ተቋማት በእጅዎ ስር ነው ያሉት፤ ፓርላማው ሕግ ያወጣል፣ ሕግ ያፀድቃል፤ ፍርድ ቤቱ በሕጉ መሰረት ይፈርዳል፣ ወደ አስፈፃሚው ያስተላልፋል፣ ሰራዊቱ (ፖሊስና መከላከያ) ሕጉን ይጠብቃል፣ ያስፈፅማል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሕዝቡ ለውጡን እንዲጠብቅ ማድረግና መብቱን እንዲያስከብር ማደራጀት በከፍተኛ ደረጃ ይጠቅማል፡፡

ሰሞኑን በአዲስ አበባ ጉዳይ ላይ የተነሳውን እንደምሳሌ መውሰድ ይቻላል፡፡ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቹ አቶ እስክንድር ነጋ በአዲስ አበባ ጉዳይ ላይ ሕዝባዊ ስብሰባ መጥራቱና ማወያየቱ፣ ሕዝባዊ ኮሚቴም ማቋቋሙ የእርስዎን ዓላማ ከመተግበሩም በላይ በእርስዎ ከእስር የተፈታበትን የዴሞክራሲ ሥራ አስጀምሯል፡፡ ስለዚህ እርስዎንም ረዳ፣ የእርስዎንም ዓላማ በሥራ ተረጎመ ማለት ነው፡፡ አቶ እስክንድር ይህን በማድረጉ እኛም እንቅልፍ ተኝተን ማደር ጀምረናል፡፡ በምላሹ እኛም ለአቶ እስክንድር ነጋ ልክ በመስቀል አደባባይ ለእርስዎ ደህንነት እንደቆምነውና የእርስዎን ሞት ለኛ ብለን እንደተሰለፍነው ነው ከጎኑ የምንቆመው፡፡ ምክንያቱም በኢትዮጵያዊነት ጥያቄ ላይ ከእርስዎ ቀጥሎ ከኛ ጎን እንደቆመ እናስባለንና ነው፡፡ በዚህ መልክ ሕዝብ እየተደራጀ ራሱንና

*አቶ እስክንድር ይህን በማድረጉ እኛም እንቅልፍ ተኝተን ማደር ጀምረናል፥፥ በምላሹ እኛም ለአቶ እስክንድር ነጋ ልክ በመስቀል አደባባይ ለእርስዎ ደህንነት እንደቆምነውና የእርስዎን ሞት ለኛ ብለን እንደተሰለፍነው ነው ከጎኑ የምንቆመው*

አካባቢውን ከነውጠኞችና ለውጥ አደናቃፊዎች ቢጠብቅ ለውጡን ያራምዳል፣ የእርስዎንም ሥራ ያቃልላል፡፡ ሕዝቡ ራሱ ተደራጅቶ ራሱንና ከተማውን ከዘሎ ገብ ጉልበተኞችና ሽፍቶች ጥቃት ይጠብቃል፡፡

በአዲስ አበባ ጉዳይ ይኸን ያህል ጭቅጭቅ ሲነሳ የክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዝምታ አስገራሚም፣ አስደንጋጭም እንደነበረ እርስዎም ሊገነዘቡት ይገባል ብዬ አምናለሁ፡፡ ሲጀመር ይህ የአዲስ አበባ ጉዳይ እንዲህ መታሰቡ፣ ከመታሰቡ ደግሞ መነገሩ አሳዛኝ ነው፡፡ ለመሆኑ ይሁን ቢባል ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ግብር ተሰብስቦ ለአዲሰ አበባ ከተማ መንገዶች ማሳመሪያ፣ ለአዲስ አበባ ቤተመንግስቶች መስሪያና ማስዋቢያ፣ በአዲስ አበባ ውስጥ ለከተሙ የሚኒስትር መ/ቤቶችና ታላላቅ ህንፃዎች፣ በአዲስ አበባ ለታነፁ ሆስፒታሎችና ት/ቤቶች የፈሰሰው ገንዘብ ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በግብር መልክ ተሰብስቦ አይደለምን? ታዲያ ለዚህ ሕዝብ፣ ለዚች ከተማ ግንባታ ያፈሰሰውን ሀብት ማን ሊከፍለው ይችላል? የአዲስ አበባ ኗሪ ሕዝብስ አዲስ አበባ ውስጥ ተወልዶ አያት፣ ቅም አያት ያሳለፈው አዲሳቤስ ምን ያውራ? ዛሬ ታላቋ ብሪታኒያ እንኳን በተባባሪ አባልነት ቆይታ ከአውሮፓ ኮሚኒቲ መውጣት ምን ያህል እንደከበዳት ማየት ማን ይሳነዋል? ይልቁንስ የአዲስ አበባ ዙሪያ ሕዝብ ከአዲስ አበባ ራቅ ብሎ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ የማያገኘውን ትልቅ ጥቅም ያገኛል፡፡

በአዲስ አበባ ዙሪያ ያለ ሕዝብ ስልጣኔ በደጁ ነው፣ ዘመናዊ መንገድና ትራንስፖርት አጠገቡ ነው፣ ሆስፒታሉ፣ ትምህርት ቤቱ፣ የአየር በረራው፣ ባቡሩ፣ ኢኮኖሚው ወዘተ በደጁ ነው፡፡ ይሄ ሁሉ የተሰራው ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ በአራቱም ማዕዘን ባለው የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ሀብት ነው፡፡ ይህ ጥያቄ የአንድ አካል ጥያቄ ሆኖ መነሳቱ ግን በጣም የሚገርም ነው፡፡ እንደ እኔ አዲስ አበባ የማን ናት ብሎ መጠየቅ ኢትዮጵያ የማን ናት? ብሎ እንደመጠየቅ ይመስለኛል፡፡ መልሱም ቀላል ነው፡፡ ኢትዮጵያም ሆነች አዲስ አበባ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ሁሉ ናት፡፡ ማንኛው ሰው በማንኛው መሬት ላይ ነው ባለቤት የሚሆነው ወይ ደግሞ ባለቤት የማይሆነው? ለመሆኑ ሀገር ነው ወይስ ብሔር የሚለው ቃል ቀድሞ የተፈጠረው? ለኛም ለአባቶቻችንም መጀመሪያ የቆምንበት መሬት ነው፤ እኛም እዚያ መሬት ላይ ቆመን ነው ሁሉንም መሆን የቻልነውና አዲስ አበባን አዲስ አበባ ያደረግነው፡፡ ከገቢያችን ግብር ከፍለን፣ ከአፋችን ነጥቀንና ቆጥበን ቤት ሰርተን ይህችን ከተማ የገነባናት እኛ አዲስ አበቤዎች ነን ለሁሉም ኢትጵያዊ ሁሉ እንድትሆን ብለን የሰራናት፡፡ ሀገር ደግሞ በአያት ቅደመ አያቶቻችን የተሰራች ምድር ናት፡፡

በመጨረሻ ግን ክቡር ጠ/ሚኒስትሩን ሳላሳስብ ማለፍ የማልፈልገው ጉዳይ የሚከተለውን ነው፡፡ እንደዚህ የመሳሰሉት ጥያቄዎች “ማለትም ይኸ የኛ ነው፣ የነሱ ወዲያ ነው፣ እነሱ ያንሳሉ፣ እኛ ከእነሱ እንበልጣለን ወዘተ.” የሚሉ ጥያቄዎች የሚነሱት በፀረ-ለውጥ ኃይሎች ነው፡፡ እነዚህ ፀረ ለውጥ ኃይሎች ለውጡን ለመቀልበስ በትጋት እየሰሩ ነው፡፡ ሕዝብን እየገደሉና እያስገደሉ ሀገሪቱን በብጥብጥ በማዳረስ ላይ ናቸው፡፡ የእርስዎም ዝምታ እንደቀጠለ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ በወቅቱና በሕግ ካልተፈታ ግን ወዴት እንደሚሄድና መቋጫውስ ምን ሊሆን እንደሚችል ለእርስዎ መንገር አስፈላጊ ባይሆንም በመጨረሻ በሰብዓዊ መብት ጥሰትና በጦር ወንጀል የሚያስጠይቅና ለወንጀሉም ተጠያቂ የሚሆን ኃይል ሊኖር እንደሚችል መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡ ስለዚህ እንዳነሳስዎ ከሕዝብ ጎን ቢቆሙ፣ ኢትጵያዊነትን እንደሰበኩት ሁሉ የሚሉትንም በቆራጥነት ወደ ተግባር ቢቀይሩት፣ በሕዝብና በሕዝብ ላይ ብቻ ቢተማመኑ፣ ሕዝቡንም ተደራጅቶ ራሱንና ጥቅሙን እንዲጠብቅ ቢያደርጉ፣ የለውጡ ተቃዋሚዎች ደግሞ በፍጥነት ወደ ሕግ ተጠያቂነት እንዲቀርቡ ቢያደርጉ፤ ሕዝብ ከጎንዎ ይቆማል፤ የተነሱለት ዓላማም ግቡን ይመታል፤ ታሪክም ሲያወድስዎ ይኖራል፡፡ ሀገርም ሆነ ታሪክ የሚለወጠው በሕዝብ፣ ሀገር የሚገነባውም በሕዝብ ነውና፡፡ እንዴት ሊሆን እንደሚችል መንገዱን ማሳየት ግን የመሪው ነው፡፡ ስለዚህ እንደአነሳስዎና ለመሪ እንደሚገባ ይምሩን፤ ካልተገባ የዘረኝነት ደንቃራ ውስጥም እንድንወጣ መንገድ መርጠው በቆራጥነት አቅጣጫ ያሳዩን፤ የመለያየት መንገድ አቀንቃኞችንም ያስታግሱልን፡፡

*ኢትዮጵያ በልጆችዋ ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!*

# ግንቦት 8 . . .

◀ ከገጽ 28 የዞረ

መንጌን ወደ ‘መንግሥተ ሰማይ’ ልኮ መሬት ላይ አዲስ መንግሥት የማቆም ብርቱ ሥራ አለባቸው፡፡

ጄኔራሎቹ ጦርነት ታክቷቸዋል፡፡ በመንጌ “ቆራጥ” አብዮታዊ አመራር ሺህ የድሀ ልጆችን መማገድ አንገሽግሿቸዋል፤ በአፋቤቴ፣ በቀይ ኮከብ፣ በባሕረነጋሽ ዘመቻ…አሥር ሺህዎች እንደቅጠል ረግፈዋል፡፡ ‘ጦርነትን እንደ ሥራ የያዘ መንግሥት ሕዝብ ሊመራ እንዴት ይቻለዋል?’ ሲሉ ነበር ድምጻቸውን ዝግ አድርገው የሚያጉረመርሙት፡፡

መንግሥቱ ይሄን ማጉረምረም ከሰሙ ጄኔራሎቹን አይምሯቸውም፡፡ ማዕረጋቸውን በመቀስ፤ ግንባራቸውን በሽጉጥ ሊነድሉት ይችላሉ፤ አድርገውታልም፡፡ የናደው ዕዝ ዋና አዛዥ ብርጋዲየር ጄኔራል ታሪኩ ዓይኔን፣ አሳዛኝ ፍጻሜን የሰማ ከመንጌ ጋር አይቀልድም፡፡፡

የአገሪቱ ምጣኔ ሐብት ደቋል፣ ሕዝብ ተርቧል፤ ወታደሩ ኮቾሮ እየበላ ነው የሚዋጋው፡፡ የገዛ ልጁንና ሚስቱን እንኳ ማየት አይፈቀድለትም፡፡ ጄኔራሎቹ ‘የገዛ ወገናችንን ትርጉም በሌለው ጦርነት ለምን እናስጨርሳለን?’፣ ‘ደግሞስ የሰሜኑ ችግር በፖለቲካ እንጂ በአፈሙዝ ይፈታል እንዴ?’… እያሉ ያጉረመርሙ ነበር፤…መንጌ ሳይሰሙ፡፡

ኮ/ል መንግሥቱ ግን ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር እያሉ ጦርነቱን ገፉበት፡፡ በዚያ ላይ ከጦር አዛገሮቻቸው ይልቅ ካድሬዎቻቸውን ማመን አበዙ፡፡

“ይሄ ሰውዬ እኛን የማይሰማ ከሆነ ለምን አናስወግደውም?” አሉ…ጄኔራሎቹ፤ ማንም ሳይሰማቸው፡፡

መፈንቅለ መንግሥት ለማካሄድ ዝግጅት ተጧጧፈ፡፡ ለዚያ ነው ያን ቀን፣ ግንቦት 8 መንጌን ቶሎ መሸኘት የነበረባቸው…፤

ከሻዕቢያ ጋር ቶሎ ለድርድር መቀመጥ ያሻል፡፡ ይሄን የውጭውን ሽርጉድ፣ ገና ድሮ መንጌን የከዱት ሻለቃ ዳዊት ወ/ጊዮርጊስ አሰናድተውታል፡፡ ጄኔራሎቹ የመንጌን ወደ ምሥራቅ ጀርመን መሸኘት…ይቅርታ የመንጌን እስከወዲያኛው መሸኘት በጉጉት እየጠበቁ ያሉት ለዚሁ ነው፡፡

### የዛሬ 30 ዓመት፤ ግንቦት 8፤ ረፋድ ላይ

ሰዓቱ አልገፋ አለ…

ወግ ነውና…መሪን መሸኘት… “ጓድ ሊቀመንበር በሰላም (አ)ይመልስዎ” እያሉ ቀኝ-ወ-ግራ ተሰይመው ተሰናበቷቸው፤ የገዛ ጄኔራሎቻቸው፡፡

መንጌ ያቺን ተወርዋሪ ኮከብ የመሰለች ፈገግታቸውን ቦግ እልም እያደረጉ አጸፋውን መለሱ፡፡ ለምን ይሆን ግን ፈጣሪ ለአምባገነኖች ችምችም ያለ፣ የተፈለፈለ በቆሎ የሚመስል ጥርስና ረዥም ዕድሜን የሚቸረው?

የሚደንቀው ታዲያ…በዚያች ዕለት የቦሌ ሽኝት ጄኔራል መርዕድ ንጉሤ አልተገኙም፡፡ ይሄ ቀላል ፕሮቶኮሏዊ ህጸጽ ተብሎ ሊታለፍ ይችላል፡፡ ጊዜ አጥተው ነው ሊባልላቸውም ይችላል…፡፡ ምክንያቱም ዘመኑ የጥድፊያ ነዋ… የጦርነት፡፡ በየግንባሩ ‹‹ገንጣይ-አስገንጣይን›› ለመፋለም የወገን ጦር ከሺህ “የወንበዴው ጦር” ጋር ተናንቆ እየተዋደቀ ነው፡፡ ፈንጂ እየረገጠ ነው…በእንዲህ ያለ ቀውጢ ጊዜ ለሽኝት መኳኳል ቅንጦት ሊሆን ይችላል፡፡ ቢኾንም…ጄኔራሉ ደግ አልሠሩም፡፡

“መርዕድ ምነው ቀረ? ምንስ ብርቱ ጉዳይ ቢገጥመው፣ ቆራጡን መሪያችንን መሸኘት አልነበረበትም?” የምትል የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል ጥርጣሬ ሳይገባቸው አልቀረም፤ የደኅንነቱን ሹሙን፤ ኮ/ል ተስፋዬ ወልደሥላሴን…፡፡

ኢታማዦር ሹሙ ደግ አልሠሩም፤ እንደምንም ብለው አለቃቸውን መሸኘት ነበረባቸው፡፡ እርሳቸው በተቃራኒው መከላከያ ሚኒስትር ውስጥ፣ ከኢትዮጵያ ሆቴል ፊት ለፊት፣ ከአምባሳደር ሲኒማ ጎን፣ ከቢሯቸው ቁጭ ብለው የክፍለ ዘመኑን አስገራሚ የስዒረ መንግሥት ‘ተውኔት’ እየጻፉ ነበር፡፡

### የመንጌ አውሮፕላን ለምን አልጋየም?

ጓድ መንግሥቱ ለምሳ ያሰቧቸውን ለቁርስ ማድረግን ተክነውበት ሊሆን ይችላል፡፡ በዚያች ዕለት ግን ቁርስም ምሳም እራትም ሊደረጉ የነበሩት እርሳቸው ናቸው፡፡ ይህን ፈጽሞ አያውቁም፡፡ አውሮፕላኑን የተሳፈሩትም የእሳትራት ኾነው ነው፡፡

የተሳፈሩባትን አውሮፕላናቸው ሰማይ ላይ እንዳለ የማጋየቱ ነገር ያበቃለት፣ ተቦክቶ ያለቀ፣ የደቀቀ ጉዳይ ነው፡፡ ይህን ያጸደቁት ደግሞ ከሞላ ጎደል ሁሉም የጦር አዛዦች ነበሩ፡፡ ድንገት መንጌን ሸኝተው ሲመለሱ ቆፍጣና ወታደራዊ መንፈሳቸው በ’ኖና ተ’ኖ የባህታዊ ሐሳብ በልባቸው አደረ፡፡

“…ጓዶች! ለምን እናጋየዋለን ግን?”

“እንዴት ማለት…”

“…እሱን ለመግደል ብለን የ70 ንጹሐን ነፍስን ከምናጠፋ….”

“ኖኖኖኖ…ወደ ኋላ ባንመለስ ነው የሚሻለው በዚህ ጉዳይ…ተስማምተን የጨረስነውን? ‘’

“አደለም!ተስማምተን ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ወ/ሮ ውባንቺስ፣ ልጃቸውስ? አብራሪዎቹስ? ወገኖቻችን አይደሉም? ምን አጠፉና ነው በዚህ ሰውዬ ጦስ የሚጠፉት…” ይሄ ሐሳብ ምናልባትም ከአየር ኃይል አዛዡ ጄኔራል አመሃ የመጣ ሳይሆን አይቀርም፡፡

“…እና ምን በጀ ጓዶች?” ምናልባት እርጋታ የማይለያቸው ሰብሳቢው ጄኔራል መርእድ እንዲያ ጠይቀው ይሆናል፡፡

“…ባይሆን በጦር አውሮፕላን አስገድደን አሥመራ ብናሳርፈው አይሻልም?” ይሄ ከጄኔራል አመሃ የመጣ መፍትሄ ሊሆን ይችላል፡፡

### “ አሥመራ የማይሆን ነው፤ በሙሉ መንጌ መንጌ የሚል አየር ወለድ ነው ያለው”

በዚህ ጊዜ ምናልባትም የዘመቻ አዛዡ ጄኔራል አበራ እምር ብለው እንዲህ ተናግረው ይሆናል፤ “ምንድነው ይሄ ውልውል? ተስማምተን? ተግባብተን በአንድ ያጸደቅነውን? የምን መንሸራተት ነው? ይሄኮ ፌዝ አይደለም! መፈንቅለ መንግሥት ነው እያካሄድን ያለነው፡፡ የሊቀመንበሩን አውሮፕላን ካላጋየን ኋላ የምንጋየው እኛው ነን…ውርድ ከራሴ…”

ጄኔራሎቹ መግባባት ተሳናቸው፡፡ ይህ ጉዳይ የመጨረሻቸው መጀመርያ ኾነ፡፡

ጄኔራሎቹ በመከላከያ ሚኒስትር ግቢ፣ አንደኛ ፎቅ ላይ፣ ፊቷን ወደ ክቡ የብሔራዊ ባንክ ሕንጻ ባዞረች አንዲት የስብሰባ አዳራሽ ታድመው በኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታ ላይ እንዲህ ጉንጭ አልፋ ክርክር እያደረጉ ሳለ ጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱን የያዘው አውሮፕላን በሰማይ ላይ ሳይጋይ፣ አሥመራም ተገዶ ሳያርፍ የኢትዮጵያን የአየር ክልል እየቀዘፈ ራቀ፡፡

ደብረዘይት አየር ኃይል ግቢ አውሮፕላኑን ለመምታት በተጠንቀቅ የነበሩት ጄቶችም ሞተር አጠፉ፡፡

### በአሥመራ ግን ‘መንጌ ተገድለዋል’

በአሥመራ የግዙፉ 2ኛው አብዮታዊ ሠራዊት አድራጊ ፈጣሪ፣ ሥመ ጥሩው ጄኔራል ደምሴ ቡልቶ ናቸው፡፡ እንዲያውም የስዒረ መንግሥቱ ሁነኛው ጠንሳሽ ሳይሆኑ አይቀሩም፡፡

ምክትላቸውን ጠርተው ነገሩ ሁሉ መልክ መልክ መያዙን አረጋገጡ፡፡ ጄኔራል ቁምላቸው በአራት አንቶኖቭ የታጨቁ 433 ልዩ ኮማንዶዎችን አሳፍረው ወደ አዲስ አበባ ጉዞ እንዲጀምሩ አዘዟቸው፡፡

ጄኔራል ቁምላቸው አገሪቱ አለኝ የምትላቸውን የአየር ወለድ አባላት “ዳይ! ተንቀሳቀስ” አሏቸው፡፡ በወታደር ቤት አለቃ ሲያዝ “አቤት ጌታዬ!” እንጂ “ለምን ጌታዬ?” አይባልም፡፡

ሶቭየት ሠራሽ አንቶኖቭ ውስጥ እንዳሉ ድንገት ጄ/ል ቁምላቸው እመር ብለው ተነሱ፡፡ የሃሎ ሃሎ መነጋገሪያውን ረዳታቸው አቀበሏቸው፡፡ አንድ በራሪ ወረቀት ከኪሳቸው አውጥተው ማንበብ ጀመሩ፡፡

### መንጌ ተገድሏል፡፡ ጦርነት አብቅቷል፡፡ እንኳን ደስ ያላችሁ!

ጄ/ል ቁምላቸው

እዚያ አንቶኖቭ ውስጥ ያለው ወታደር በሙሉ በታላቅ ፌሽታ አጨበጨበ፡፡ በዚያ አንቶኖቭ ውስጥ የነበሩትና ዛሬም በሕይወት የሚገኙት ሌ/ኮ/ል ካሳዬ ታደሰ ለቢቢሲ አማርኛ እንደተናገሩት… “መንግስቱ ተገድሏል ሲባል መጀመርያ ደነገጥኩ፤ ከዚያ ሁሉም ሲያጨበጭብ እኔም ማጨብጨብ ጀመርኩ” ሲሉ የወቅቱን ድራማ ገልጸዋል፡፡

ሰማይ ላይ አንቶኖቩ ውስጥ ይህ ሲሆን የአሥመራ ሬዲዮ በበኩሉ መንግሥቱ መገደሉን አወጀ፡፡

ከአንድ ሰዓት ተኩል በረራ በኋላ ጄኔራል ቁምላቸው ኮማንዷቸውን ይዘው አዲስ አበባ ጦር ኃይሎች ልደታ አርሚ አቪየሽን ገብተዋል፡፡ ግማሾቹን ኮማንዶዎች ደግሞ እዚያው ቦሌ አየር መንገድን እንዲቆጣጠሩ አድርገዋል፡፡ የዚህ ልዩ ኮማንዶ ተግባር ሬዲዮ ጣቢያውን መቆጣጠር፣ መከላከያ ሚኒስትር ለሚገኙት መፈንቅለ መንግሥት አድራጊዎች ደግሞ ከለላ መስጠት፤ ድንገት ‹‹ለመንጌ አንገቴን እሰጣለሁ›› የሚል ኃይል ካለ አንገቱን እንደ ዶሮ መቀንጠስ ነው፡፡

የሚገርመው የአሥመራ ሬዲዮ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም እስከወዲያኛው እንደተሰናበቱ ያወጀው ገና ረፋድ ላይ ነበር፡፡ በመሆኑም ጄኔራል ቁምላቸውም እስከመጨረሻው የሚያውቁት መንግሥቱ መገደሉን ነው፡፡ ሌ/ኮ/ል ካሳዬም ይህንኑ ለቢቢሲ አረጋግጠዋል፡፡

### ከጣላይ የመጣው ሠራዊት

መፈንቅለ መንግሥቱን ለማቅናት ከአሥመራ በጄ/ል ቁምላቸው እየተመራ አዲስ አበባ ከገባው ኃይል ሌላ ከጦላይም አንድ ሻለቃ ተንቀሳቅሷል፡፡

ጄኔራል ውበቱ ፀጋዬ ከሴረኞቹ ጋር በስሱም ቢሆን ሳይመሳጠሩ አልቀሩም፡፡ አሁንም ድረስ በሕይወት አሉ፤ አሜሪካን አገር፡፡ ወደ አዲስ አበባ የሚላከውን ጦር አዘጋጅተው እሳቸው ከሰሜን ኮሪያ የመጣ ልኡካን ቡድንን ተቀብለው እያነጋገሩ ነበር፡፡

ጦላይ ያለው ልዩ ኮማንዶ የቁልምጫ ስሙ “ስፖርታ” ይባላል፡፡ ሰሜን ኮሪያዎች ለከተማ ውጊያ፣ ለጨበጣ ፍልሚያ በልዩ ጥንቃቄ ያሰለጠኑት ጦር ነው፡፡

ጄ/ል ውበቱ ጥርት ያለ መመርያ▶

ባይደርሳቸውም 150 የሚሆኑትን ምርጥ ምልምሎች በወታደራዊ ሄሊኮፕተር ወደ አዲስ አበባ ላኳቸው። ፖስታ ቤት መገናኛ ሚኒስትር አካባቢ በሚገኝ ሜዳ ላይ ሆነው ትዕዛዝ እንዲጠባበቁ ተደረገ። ኋላ ላይ 4ኛ ክፍለ ጦር…

አምባሳደር ጋ፣ ኢትዮጵያ ሆቴል ጎን፣ መከላከያ ሚኒስትር ውስጥ …

ከኢትዮጵያ ሆቴል ትይዩ በዋናው የመከላከያ ሕንፃ 1ኛ ፎቅ የጠቅላይ ኢታማዦር ሹሙ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ይገኛል። ይህ አዳራሽ ፊቱን ወደ ወርቃማው የብሔራዊ ባንክ የሰጠ ነው።

በዚህ አዳራሽ 18 መፈንቅለ መንግሥት አድራጊዎች ሴራ እየጎነጎኑ ነው። ቁጥራቸው ይጨምራል ይቀንሳል። ሆኖም በአገሪቱ አንድም የቀረ ቱባ ጄኔራል የለም።

በኢትዮጵያ የመጀመርያው አብዮታዊ ጄኔራል፣ ተወዳጁ፥ ደርባባው፣ አንደበታቸው የረጋው ጄ/ል መርዕድን ጨምሮ የባሕር ኃይል አዛዥ ሪር አድሚራል ተስፋዬ ብርሃኑ፣ የአየር ኃይል አዛዡ ጄኔራል አምሐ፣ የምድር ጦር አዛዡ ጄኔራል ኃይሉ፣ የፖሊስ ሠራዊት አዛዡ ጄኔራል ወርቁ ይገኙበታል።

ስለ ጀግንነታቸው ሳር ቅጠሉ የመሰከረላቸው እነ ጄኔራል ፋንታ በላይ፣ እነ ጄኔራል አበራ አበበ፣ እነ ጄ/ል ደምሴ ቡልቶም አሉበት። ስለነዚህ ጄኔራሎች የጦር ጀብድ እንኳን ወታደሮቻቸው አንዳንድ የሰሜን ተራሮችም አፍ አውጥተው ባይናገሩ…ማን ቀረ ታዲያ?

እርግጥ ነው ጄኔራል ደምሴ ቡልቶ በአካል አምባሳደር-ብሔራዊ አካባቢ አይሁኑ እንጂ በመንፈስ አብረዋቸው ናቸው። እርሳቸው አሥመራ ትልቁን የቤት ሥራ ሠርተው ጨርሰዋል። የአገሪቱ ሁለት ሦስተኛ ጦር በርሳቸው ሥር ነው ያለው።

አሁንም ድረስ አስገራሚው ነገር ታዲያ የአሥመራ ጦር መጀመሪያ በታቀደው መሠረት የመንጌ አውሮፕላን መመታቷን ነው የሚያውቀው። ይህንኑም በሬዲዮ አስነግሯል።

እነዚህ 18 የጦር አበጋዞች ግማሽ ሚሊዮን የሚጠጋውን የአገሪቱን ሠራዊት ያዛሉ። ሁሉም በመፈንቅለ መንግሥቱ ጉዳይ ላይ መግባባት ደርሰዋል። ሆኖም እዚያው መከላከያ ሚኒስትር ስብሰባ ላይ ናቸው። ይህ ይሆን መዘናጋትን የፈጠረባቸው? ምን ዓይነት ምድራዊ ኃይል መጥቶ ይህን 'ኩዴታ' ሊያከሽፍ ይችላል?

ስክነት የራቃቸው ጄኔራል አበራ ብቻ ናቸው። እስራኤል ነው የተማሩት። የዘመቻ አዛዡ ጄኔራል አበራ ወትሮም ችኩል ናቸው ይባላል። ቀልባቸው የሆነ ነገር ሳይነግራቸው አልቀረም። በስብሰባው መካከል ወጣ እያሉ ግቢውን ይቃኛሉ። በዚህ መሀል የታንክ ቃቃታ የሰሙ መሰላቸው።

የመከላከያ አስተዳደር መምሪያ አዛዡን ጄኔራል ዑመርን አስከትለው የመከላከያ ግቢ የባንዲራ መስቀያው ጋ ቆመው መከላከያ ቢሮ ውስጥ ያለውን ሰው በሙሉ ወደ ግቢው እንዲሰለፍ አዘው ንግግር ማድረግ ጀመሩ፤ የመንጌን ፍጻሜም አበሰሩ። ተጨበጨበ…ቪቫ ኩዴታ ተባለ. የመከላከያ ሚኒስትሩ መገደል

የደኅንነት ሚኒስትሩ ተስፋዬ ወ/ሥላሴ ሴራ ሸትቷቸዋል፤ ባምቢስ ከሚገኘው የደኅንነት ቢሯቸው እየበረሩ ወደ ምኒሊክ ቤተ መንግሥት ነዱ። የመንጌን ልዩ ረዳት መንግሥቱ ገመቹን ጠርተው አስቸኳይ ስብሰባ ጀመሩ። እነ ፍቅረሥላሴ ወግደረስም አሉበት። እንዲያውም ሰብሳቢው እርሳቸው ናቸው።

ምንድነው እየሆነ ያለው? እነ መርእድ ምንድነው እየዶለቱ ያሉት?

**የደኅንነት ሚኒስትሩ ተስፋዬ ወ/ሥላሴ**

መከላከያ ሚንስትሩን ጄኔራል ኃብተጊዮርጊስን ጠርተው፣ ለመሆኑ በቢሮህ ምን እየተካሄደ እንደሆነ ታውቃለህ? ብለው ጠየቁ።

‹‹አረ በፍጹም›› አሉ ሚኒስትሩ። ሄደው እንዲያጣሩ ሐሳብ ቀረበ። በሄዱበት ይቀራሉ ያለ አልነበረም።

ሚኒስትሩ ቁልቁል ወደ አምባሳደር በረሩ። ወደ ቢሯቸው ገብተው ወጡ።

ጄ/ል ኃብተጊዮርጊስ ወትሮም ከጄ/ል አበራ ጋር እስተዚህም ናቸው። እረ እንዲያውም ዐይንና ናጫ…። ጄ/ል አበራ የሆነ የቀፈፋቸው ነገር ያለ ይመስላል። ጄ/ል መርዕድ ከሚመሩት ስብሰባ በየመሀሉ እየወጡ ኮሪደሩን፣ አካባቢውን ይቃኙና ይመለሳሉ።

ድንገት ለቅኝት ደረጃውን ሲወርዱ፣ መከላከያ ሚኒስትሩ ደግሞ ደረጃውን ሲወጡ ተገጣጠሙ።

"አበራ! ምንድነው እኔ የማላውቀው ስብሰባ?" ሳይሉ አልቀሩም። አንዱ ሁለት ተባብለውም ሊሆን ይችላል። ብቻ ጄኔራል አበራ በቅልጥፍና ሽጉጣቸውን አውጥተው መከላከያ ሚኒስትሩ ላይ አከታትለው ተኮሱ።

ጦር ኃይሎች ቢወሰዱም አልተረፉም።

**ጄኔራል አበራ እንዴት አመለጡ? ለምን አመለጡ ?**

ይህ ሁሉ ሲሆን ከአሥመራ የመጣው የጄኔራል ቁምላቸው ሠራዊት ጦር ኃይሎች ግቢ ሆኖ በተጠንቀቅ ትእዛዝ ይጠባበቃል። እንዲያውም ስልክ ወደ ጄ/ል አበራ ደውሎ አልተነሳለትም። ከጦላይ የመጣውና በሰሜን ኮሪያዎች የሰለጠነው የስፓርታ ጦርም ፖስታ ቤት አካባቢ ሥራ ፈትቶ ሜዳ ላይ ተቀምጧል። ።

ሁሉም ታዲያ ሪፖርት የሚያደርጉትም ትእዛዝ የሚቀበሉትም ከጄኔራል አበራ ብቻ ነው። የዘመቻ መምሪያ ኃላፊ እሳቸው ናቸዋ።

ጄ/ል አበራ ግን ያልተጠበቀ ነገር ፈጽመው ችግር ውስጥ ገብተዋል። መከላከያ ሚኒስትሩን ከገደሉ በኋላ ወደ ቢሮ አልተመለሱም። ልዩ ኮማንዶነት የሰለጠኑት ጄ/ሉ በአጥር ዘለው አምልጠዋል።

አንዳንዶች ከጎን የሚገኘው ቡና ገበያ ግቢ ገብተው ዘበኛ ማርከው የወታደር ልብሳቸውን አውልቀው የዘበኛ ልብስ ለብሰው ተሰወሩ ሲሉ፣ ሌሎች ደግሞ የለም ከመከላከያ የወጡት በአጥር ሳይሆን በበር ነው፤ የአንድ ሠራተኛ ልብስ ቀይረው ነው ይላሉ።

የጄ/ል አበራ ከመከላከያ መሰወር ነገሮችን አመሰቃቀለ።

ከጦላይና ከአሥመራ የመጣው ኃይል ምን ማድረግ እንዳለበት ግራ ገብቶት እርሳቸውን ይፈልጋል። እርሳቸው ግን ስልክ አያነሱም። ቢሮም የሉም። በዚያ ዘመን ሞባይል የሚባል ነገር አይታወቅ ነገር…

**ጄኔራሎቹ ራሳቸውን ለምን አጠፉ?**

ግንቦት ስምንት ቀትር ስምንት ሰዓት ግድም የጀመረው መፈንቅለ መንግሥት ራሱን በራሱ እየተበተበ አንድም ፋይዳ ያለው ነገር ሳያከናውን መሸበት። ደኅንነቱ ተስፋዬ ወ/ሥላሴ ሻምበል መንግሥቱ ገመቹን ይዘው መከላከያን አስከበቡ፤ ለዚያውም በታንክና በብረት ለበስ።

ከዚያ በፊት ግን ነገሩን በሰላም እንጨርሰው በሚል ሽማግሌ ተልኳል፤ ሌ/ኮ አዲስ ተድላና ኮ/ል ደበላ ዲንሳ ነበሩ አደራዳሪዎቹ።

‹‹መፈንቅለ መንግሥቱ ያበቃለት ጉዳይ ነው፤ ምንም ድርድር ብሎ ነገር የለም። ባይሆን አግዙን›› ሳይሏቸው አይቀርም፣ እነ ጄ/ል መርዕድ።

ዞሮ ዞሮ ሰዓቱ ነጎደ። ማስታወቂያ ሚኒስትር አልተያዘ፣ ሬዲዮ ጣቢያ አልተያዘ፣ ቴሌ አልተያዘ…ሰዓቱ ነጎደ። የሳር ቅጠሉ አዛዦች በሙሉ እዚያ መሆናቸው ሳያዘናጋቸው አልቀረም። የጄ/ል አበራ ድንገት ሰው ገድሎ መሰወር ግን ነገሮችን አወሳሰበ።

የመንጌ ቀኝ እጅ ሞክሼያቸው መንግሥቱ ገመቹ የልዩ ብርጌድ ኃይላቸውን ከ4ኪሎ አንቀሳቀሱ። በሂልተን አድርገው አምባሳደር ጋ ሲደርሱ 'መከላከያ ሚኒስትሩን ክበብ' አሉ።

ውስጥ እነ ጄ/ል ፋንታ በላይ፣ እነ ጄ/ል አመሃ፣ እነ ጄ/ል መርዕድ…ምን እያደረጉ እንዳሉ የሚያውቅ ምድራዊ ኃይል የለም። ሆኖም በዚያ ሰዓት መከበባቸውን እንደተረዱ ከአሥመራ ይመጣል የተባለው ኃይል ባለመድረሱ ተስፋ ቆርጠው ሊሆን ይችላል። ብቻ ጄ/ር መርዕድና ጄ/ል አመሐ ዛሬም ድረስ ግልጽ ባልሆነ ሁኔታ እዚያው ራሳቸውን አጠፉ።

**ድኅረ ታሪክ**

ግንቦት 9 ማታ ኮ/ል መንግሥቱ ከምሥራቅ ጀርመን ጉብኝታቸውን አቋርጠው ኮሽታ ሳያሰሙ ተመለሱ።

ግንቦት 10፣ ጄኔራል ደምሴ ቡልቶ በገዛ ወታደሮቻቸው ተገደሉ፤ ከእርሳቸው ጋር በድምሩ 18 ከፍተኛ መኮንኖች ተመሳሳይ ክፉ እጣ ገጠማቸው። በሚኞቹ ሬሳ ላይ እጅግ የሚቀፍ፣ ታሪክ የሚጸየፈው የሰይጣን ድርጊት ተፈጸመ።

ከሦስት ቀን በኋላ ጄኔራል ፋንታ በላይ ከተደበቁበት ኮንቴይነር ወጡ። ለጥቂት ወራት ማዕከላዊ ለብቻቸው ተነጥለው ታስረው ሳሉ እስከዛሬም ይፋ ባልሆነ ሁኔታ "ጠባቂያቸውን ገድለው ሊያመልጡ ሲሉ ተገደሉ" ተባለ።

በሦስተኛው ሳምንት መከላከያ ሚኒስትሩን ገድለው ያመለጡት ጄ/ል አበራ ጉለሌ አካባቢ ከተደበቁበት ዘመድ ቤት ተከበቡ። በመስኮት ዘለው ጣሪያ ላይ ወጥተው ሊያመልጡ ሲሉ በአንድ ወጣት ፖሊስ ግንባራቸውን ተመትተው ወደቁ። አንዳንድ የሰው መረጃዎች ጄ/ል አበራን አሳልፎ የሰጣቸው ዘመድ ዛሬም ድረስ በጸጸት ይኖራል ይላሉ።

ከሆኑ ወራት በኋላ የአሥመራውን አየር ወለድ ጦር አዲስ አበባ ይዘው የመጡት ጄኔራል ቁምላቸው በአንዳች ተአምር አምልጠው አሜሪካ ገቡ ተባለ። ሲአይኤ እንዳሾለካቸው ተጠረጠረ።

ከዓመት በኋላ ግንቦት 13፣ 1981 መፈንቅለ መንግሥቱ ላይ ተሳትፈዋል የተባሉ 12 ጄኔራሎች ድንገት ለውሳኔ ተጠሩ። የወታደራዊ ፍርድ ቤት የመሀል ዳኛው ጄ/ል አሥራት ብሩ በብጣሽ ወረቀት የተጻፈችና ከኮ/ል መንግሥቱ እንደተላከች የምትገመት አንዲት ወረቀት እንባ እየተናነቃቸው አነበቧት ተባለ። በ12ቱ ላይ ሞት ተፈረደ። ፍርደኞቹም እንዲህ እያሉ ይጮኹ ነበር፤ ‹‹ቤተሰባችንን ሳንሰናበት አትግደሉን…››፣ ‹‹ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ዕድሜ የለውም››፣ ‹‹ልጆቻችንን አደራ››። ያንኑ ምሽት ተረሸኑ።

ከስዒረ መንግሥት ሙከራው ከ2 ዓመት በኋላ ግንቦት 13 ቀን ኮ/ል መንግሥቱ ከአገር ሸሹ።

የኮ/ሉን ሽሽት ተከትሎ ለአንድ ሳምንት ርዕሰ ብሔር የሆኑት ጄ/ል ተስፋዬ ገብረኪዳን ሞታቸውን እየተጠባበቁ ለነበሩ ጥቂት የመፈንቅለ መንግሥቱ ተከሳሾች ምሕረትን አወጁ።

**ምንጭ ቢቢሲ**

# “ትፈልጉ እንደኾነ፣ አስከሬኑን ውሰዱና ቅበሩት”



ጉድ ሼፐርድ አካባቢ አቶ አሰፋ ዳገቱን ወጥቶ ሲጨርስ አካባቢ አንዲት ፒክአፕ መኪና መጥታ ከፊቱ መንገዱን ዘግታበት ቆመች፡፡ የመገናኛ ሬድዮን የያዘውን ሰውዬ እና ሹፌሩን ሳይጨምር መኪናዋ ክላሽንኮቭ ጠብመንጃዎችንና የእጅ ቦምቦችን ወገባቸው ላይ የታጠቁ ስድስት ፖሊሶችን ይዛ ነበር፡፡ አቶ አሰፋ ወደ ግንቡ ተጠግቶ መኪናዋን ለማለፍ ሞከረ፡፡ በዚኽ ጊዜ አቶ አሰፋን ከቅርብ ርቀት ስትከተለው የነበረች ሌላ ኦፔል የፖሊስ መኪና የአደጋ ጥሪ እያሰማች ወደ እርሱ ቀረበች፡፡ ከኋላ ወንበር ላይ ተቀምጦ የነበረ ፖሊስም አውቶማቲክ መሣሪያ አውጥቶ አሰፋ ላይ አከታትሎ ተኮሰበት፡፡ አቶ አሰፋም ወዲያው ነፍሱ ከሥጋው ተለየች፡፡

ጥቂት ቆይቶም አስከሬን ለመጫን የሚያገለግል የፖሊስ መኪና መጥቶ የሟቹን አስከሬን አነሣ፤ በእንጦጦ አጠቃላይ ኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (እንጦጦ ቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ኮሌጅ) በስተጀርባ አድርጎ ወደ ስድስት ኪሎ በረረ፡፡ አስሩ ፖሊሶችም በቶዮታ ፒክ አፕ መኪናዋ ላይ ተጭነው የአስከሬን መኪናውን ተከተሉት፡፡ አቶ አሰፋ ከተገደለ ከ25 ደቂቃዎች በኋላ (8:45) የመገናኛ ሬድዮዎችን የያዙ፣ አውቶማቲክ መሣሪያዎችንና የእጅ ቦምቦችን የታጠቁ ፖሊሶች አቶ አሰፋ ቤት በመኼድ የፍርድ ቤት የብርበራ ማዘዣ በማቅረብ የሟቹን ቤት በረበሩ፡፡ ከረፋዱ 4:00 ሰዓት ገደማ የማይታወቅ ሰው ወደ ኢሰመጉ ቢሮ ስልክ በመደወል “አሰፋ ማሩ የሚባል ሰው ታውቁታላችኹ? የእናንተ አባል ነው?” በማለት ጠየቀ፡፡ አዎንታዊ ምላሽ ሲያገኝም “አቶ አሰፋ በመኪና አደጋ ስላረፈ አስከሬኑን ከምኒልክ ሆስፒታል መጥታችኹ ውሰዱ፡፡” የትና መቼ እንደሞተ እንዲናገር ሲጠየቅ ለመናገር ፈቃደኛ አልነበረም፤ ይልቁንም “ትፈልጉ እንደኾነ፣ አስከሬኑን ውሰዱና ቅበሩት፡፡” በሚል ዐረፍተነገር ንግግሩን ቋጨው፡፡ የኢሰመጉ አባላት ወዲያው ወደ ምኒልክ ሆስፒታል በፍጥነት ኼዱ፡፡ ያገኙት ግን በመኪና የተገጨ ሰው ሳይኾን ጭንቅላቱና ደረቱ በጥይት የተበሳሱ ፊቱ በደም አበላ የተሸፈነ፣ የሸሚዙ ደረት በደም የተነከረ የአሰፋ ማሩን አስከሬን ነበር፡፡

አሰፋ እንዴት እንደተገደለ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (EXTRA-JUDICIAL KILLING. Special Report No. 14 May 13, 1997) የዓይን እማኞችን ጠቅሶ የተረከው

የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን : (የቅዳሜ እና እሁድ ኦፕሬሽን) በልደታ፣ ንፋስ ስልክ ላፍቶ እና ቦሌ ክፍለ ከተማዎች ባካሄደው ጥናት ላይ በተመሰረተ ዘመቻ እና ድንገተኛ ፍተሻ፤

* ሰነድ ሳይኖራቸው እና ህጋዊነታቸው ያልተረጋገጡ 260 ተሽከርካሪዎች፣

* የተለያዩ ወንጀሎችን በተደራጀ መልኩ ሲፈፅሙ የነበሩ ተጠርጣ ሪዎችን እና ለወንጀል ተግባር ሲውሉ የነበሩ ተሽከርካሪዎች፣

* በህገ ወጥ ተግባር ላይም ማለትም በቅሚያ፣ በዝርፊያ፣ በህገ ወጥ የጦር መሳሪያ እና መድሃኒት ዝወውር ላይ ሲሳተፉ የነበሩ ግለሰቦች፣

* ከአደገኛ እፅ ዝውውር ጋር በተያያዘ ትልልቅ ሆቴሎች የሚያርፉ የውጭ ሀገራት ዜጎችን በደላላ እና በሆቴል ሰራተኞች በኩል በማግባባት ሺሻ እና ባእድ ነገር ተቀላቅሎ ወደ ሚጨስባቸው ስፍራዎች በመውሰድ የወንጀል ድርጊት እንዲፈፀምባቸው ያደረጉ ተጠርጣሪዎች፣

* በቅንጅት የሚንቀሳቀሱ ከ250 ሺህ ብር በላይ ትላልቅ ህንፃዎችን በመከራየት የወንጀል ድርጊት ሲፈፅሙ የነበሩ ከ2500 በላይ የሺሻ ማጨሻና እና መገልገያዎች ከዋና ዋና የድርጊቱ ፈፃሚዎች ጋር፣

* ግማሽ ኪሎ የሚደርስ አደገኛ እፅ፣ በቁጥጥር ሥር አድርጌያለሁ ብሏል፡፡

(ጌጡ ተመስገን)

# ወደ መቀሌ በረራ ያለባችሁ

ዲሲ ያለው የደለስ ኤርፖርት አንድ አንጀት የሚበላ የአበሻ ሕይወት ትዕይንት አለ፡፡ አሜሪካ የሚኖር አበሻ ወደ ኢትዮጵያ በአስቸኳይ እንዲደርስለት የሚፈልገው እንደ መድሃኒት ወይንም የሆነ አስቸኳይ ዶክመንት አይነት ነገር ይኖረዋል፡፡ እሱ በሚፈልገው ሰዓት ወደ ኢትዮጵያ የሚሄድ ዘመድ ወዳጅ የለውም፡፡ እሱ ትኬት ቆርጦ እራሱ እቃውን ይዞ ወደ ኢትዮጵያ አይሄድ ነገር የራሱ ኬዝ አላለቀለት፣ የገንዘብ አቅም የለው ብቻ የአሜሪካ ኑሮ አይፈቅድለት ይሆናል፡፡

ስለዚህ በቃ “መቼም አበሻ በአበሻ አይጨቅንም” ብሎ አይኑን አጥቦ ደለስ ኤርፖርት አስቸኳይ እቃውን ይዞ ከች ይላል፡፡ ወደ ኢትዮጵያ የሚመለሱ አበሾች ጋር ጠጋ ብሎ “ እባካችሁን ተባበሩኝ ይሄ መድሃኒት/ ዶክመንት በቶሎ ካልደረሰ እናቴ አደጋ ላይ ነች ወንድሜ ቪዛ አይመታለትም” ብሎ አይኑን ሰብሮ ወደጆቹን ይማፀናል፡፡ በጣም ብዙ ጊዜ በተለይ ደግሞ የሚላከው እቃ መድሃኒት ከሆነ ተባባሪ አበሻ አይጠፋም፡፡ መልዕክት አድራሽም “ለማን ላድርስልህ? በምን ስልክ ቁጥር አገኛቸዋለሁ? ሰፈራቸው የት ነው? “ ብሎ በቁም ነገር ጠይቆ አይዞህ ብሎ አፅናንቶ ይለያያል፡፡ እና ምን ለማለት ነው እንግዲህ የጠ/ሚ ዓብይም መንግስት የዲሲ ስደተኛ አይነት ችግር እያሳየ ስለሆነ ወደ መቀሌ በረራ ያለባችሁ እስቲ ይህቺን መጥሪያ ይዛችሁ መቀሌ በመሄድ ተቸገሩለት፡፡ ወገን በወገን አይጨክንም አይደል?

ታምራት ነገራ

# በአሜሪካ ግማሽ ሚሊዮን ዶላር አግኝቶ ለደንበኛ የመለሰው አስተናጋጅ መነጋገሪያ ሆኗል

በአሜሪካ አንዲት ጡረተኛ ሴት ልጇን ይዛ ምሳ ለመብላት ወደ አንድ ሬስቶራንት ታቀናለች፡፡ ሴትየዋ ታዲያ የፈለገችውን አዛ ከልጇ ጋር ከጣጣመች በኋላ ከነበረችበት የምግብ ጠረጴዛ ላይ በፖስታ የታሸገ ዕቃ ረስታ ትነሳለች፡፡ ከምግብ ቤቱ አስናጋጆች አንዱ አርማንዶ ማርካጅ ወዲያው የፅዳት ስራውን ለመስራት ወደ መመገቢያ ጠረጴዛው ሲያመራ ፖስታውን ይመለከታል፡፡

አስተናጋጁ ፖስታውን ከፍቶ ሲያይ በውስጡ የ424 ሺህ የአሜሪካ ዶላር ቼክ ያገኛል፡፡ አስተናጋጁ ከተገልጋይዋ ምንም ዓይት ጉርሻ (ቲፕ) ያልተቀበለ ቢሆንም ቼኩን ለምግብ ቤቱ ባለቤት አሳልፎ ሰጥቷል፡፡ ቼኩን የተቀበለው የምግብ ቤቱ ባለቤትም ከጥቂት ቀናት በኋላ ቼኩን ለባለንብረቷ አስረክቧል፡፡ በጥድፊያ ሰበብ ረስቼው የወጣሁት ገንዘብ ለኮንዶሚኒም መግዣ የያዝኩት ቅድመ-ክፍያ ነበር ብላለች ጡረተኛዋ ሴት፡፡

ጉርሻ(ቲፕ)ባለመስጠት አስተናጋጁን አስቀይመነው የነበረ ቢሆንም ይህ ግን እርሱን ትክክለኛውን ነገር ከማድረግ አላገደውም፤ በዚህ በጣም ላመሰግነው እወዳለሁ ብላለች ሴትየዋ ገንዘቧን ከተቀበለች በኋላ፡፡

ዘገባው የዩ.ፒ.አይ. ነው ምንጭ ኢቢሲ

# ግንቦት 8 የዛሬ 30 ዓመት



ኮ/ል መንግሥቱ ኃይለማርያም



ጄኔራል ፋንታ በላይ



ጄኔራል ደምሴ ቡልቶ

የዛሬ 30 ዓመት፣ ማክሰኞ'ለታ የወጣችው ጨረቃ "ጤፍ ታስለቅም ነበር"። ሌ/ኮ ካሳዬ ታደሰ ናቸው እንዲያ የሚሉት። እንደ ትናንት ያስታውሷታል፤ የነፍስ ውጭ-ነፍስ ግቢ ሌሊት። እርሳቸው ያኔ የ102ኛው አየር ወለድ ኢታማዦር ሹም ነበሩ።

30 ዓመት ብዙ ነው። ግንቦት 8 የኾነው ግን ዛሬም ድረስ እንቆቅልሽ ነው። እንደው በደፈናው "ተምኔታዊም ተውኔታዊም" ነበር ማለቱ ይቀል ይሆን?

የጦር ኃይሎች ኢታማዦር ሹሙ ጄኔራል መርዕድ ንጉሤ 'የኢትዮጵያን ባንዲራ ራሳቸው ላይ ጠምጥመው' ምናልባትም እንደ 'መይሳው ካሣ' ሽጉጣቸውን የጠጡባት ምሽት።

እርግጥ ነው በጄኔራል መርዕድ ዙርያ ብዙ የሚጣረስ ታሪክ አለ። ባንዲራ ለብሰው ነበር ከሚለው ሰነድ አልባ ተረክ ጀምሮ እስከ አሟሟታቸው ድረስ ይኸው 30 ዓመት እንኳ ያልፈታው ምሥጢር...።

ሻምበል እዮብ አባተን እዚህ ጋ እናምጣቸው። ያኔ የወታደራዊ ደኅንነት ባልደረባ ነበሩ። ከዚያ በኋላም ስለ መፈንቅለ መንግሥቱ ጥናት አድርገዋል። ስለ ጄኔራል መርዕድ አሟሟት በስፋት ከሚታመነው በመጠኑም ቢኾን ያፈነገጠ ታሪክ ጽፈው አስነብበዋል።

ጄኔራል መርዕድ ራሳቸውን ባጠፉ አፍታ እዚያ ደረስኩ ያለ አንድ የልዩ ብርጌድ ወታደር ነገረኝ ብለው ለቢቢሲ እደተናገሩት ከሆነ ጄ/ል መርዕድ ያን ምሽት ራሳቸው ላይ ቢተኩሱም ነፍሳቸው ወዲያውኑ አልወጣችም። ሺህ ወታደር ሲያዝዙ ኖረው ሞት አልታዘዝ አላቸው።

አምቡላንስ ተጠርቶ ቢመጣም አምቡላንሷ ወደ ሆስፒታል አልወሰደቻቸውም፤ ወደ ቤተመንግሥት እንጂ። አምቡላንሷ ውስጥ እስከ ንጋት ድረስ እያጣጣሩ ነበር። ቢያንስ ለ6 ሰዓታት፤ በሁለት ወታደሮች እየተጠበቁ ጣር...።

ነገሩ ሆን ተብሎ የተፈጸመ የጭካኔ ተግባር ይመስላል፤ አልያም ደግሞ ዘመኑ የወለደው የበዛ ፍርሃት። በዚያች የነፍስ ውጪ ነፍስ ግቢ ቅጽበት ማን ደፍሮ የመፈንቅለ መንግሥትን አውራ አቀናባሪና ጎንጓኝ "ሕክምና ያግኙ!" ብሎ ይጮኻል?

'አንተን የነዚህ ከሐዲዎች ጠበቃ ማን አደረገህ? ብባልስ' ይላል የዐይን እማኙ ዝምታን ለምን እንደመረጠ ሲተርክ። ...በሥራ ስንዋከብ ቆይተን ወደ አምቡላንሷ ከሌሊቱ 10 ሰዓት ስንመለስ 'የጄኔራሉ ህሊና የሚረብሸውና አንጀት የሚያላውሰው የጣርና የሲቃ ድምጻቸው ከበፊቱ ቀንሶ ይሰማ ነበር።'

በዚህ ረገድ የአየር ኃይሉ አዛዥ ጄኔራል አምሐ ዕድለኛ ነበሩ ማለት ይቻላል። የሚችና የአaሟሟት ዕድለኛ ካለው...። ጄ/ል አምሐ ሽጉጣቸውን መኪናቸው ውስጥ ረስተውት ነበር ወደ ስብሰባ የገቡት። ሽጉጥ ፍለጋ ተሯሯጡ። መከላከያ አንድ ቢሮ ዘው ብለው ሲገቡ ግድግዳ ተደግፎ የቆመ ክላሽ አገኙ። እስከ ወዲያኛው አሸለቡ። ጄ/ል መርዕድ እያጣጣሩ ከሚገኙበት አምቡላንስ ውስጥ፣ በሁለት የልዩ ብርጌድ ወታደሮች እየተጠበቀ ከነበረው አምቡላንስ ውስጥ የእርሳቸውም ሬሳ ተጠቅልሎ እንደነገሩ ተጋድሞ ነበር፤ እንደ ሻምበል እዮብ 'የማያወላዳ' የዐይን እማኝ ከሆነ።

ቢቢሲ፦ ሻምበል! ግን እኮ ይሄ ጄ/ል መርዕድን አሟሟት በተመለከተ የሚሉን ነገር እስከ ዛሬ ያልተሰማ ታሪክ ነው። ነገረኝ የሚሉትን ወታደር ያምኑታል?

ሻምበል እዮብ፦ የልዩ ብርጌድ ጥበቃ ጠባቂ ባልደረባ የነበረ ነው፤ ያን ምሽት ያየው ነገር እስከ ዛሬም ይረብሸዋል። ታሪክ ተዛብቶ ሲነገር ተበሳጭቶ ነው እኔን ያገኘኝ። "እውነታውን አስተካክለህ ጻፍ፤ እኔ እዚያው የነበርኩ ወታደር ነኝ" ነው ያለኝ። በዚያ ምሽት እሱ እዚያ ስለመኖሩ ከሌሎች አረጋግጫለሁ።

### ግንቦት 8፣ የነፍስ ውጭ፣ ነፍስ ግቢ ዕለት

አየር ወለዱ ጄኔራል አበራ አበበ የገዛ አለቃቸውን የመከላከያ ሚኒስትሩን ጄኔራል ኃይለጊዮርጊስን በሽጉጥ ገድለው፣ የዘበኛ ልብስ አስወልቀው፣ የወታደር ዩኒፎርማቸውን ቀይረው፣ ሲኒማዊ ኩነት በሚመስል አኳኋን አጥር ዘለው ከመከላከያ ግቢ ያመለጡበት ቀትር!

ይህም ታሪክ አሻሚ ነው። ለምን አመለጡ? ለምን ሚኒስትሩን ገደሉ? እንዴት መፈንቅለ መንግሥት የሚያህልን ነገር እየመሩ አንድ ሚኒስትር ስለገደሉ ብቻ እንደ ተራ ነፍሰ ገዳይ ሊያመልጡ ይችላሉ? 30 ዓመት ያልመለሳቸው ጥያቄዎች።

### ግንቦት 8፤ የነፍስ ውጭ፣ ነፍስ ግቢ ዕለት

ጄኔራል ፋንታ በላይ ለሦስት ቀን-ሦስት ሌሊት ኮንቴይነር ውስጥ የሚላስ የሚቀመስ በሌለበት የተደበቁበት ምሽት...።

ጄኔራል ፋንታ የትምህርት ዝግጅታቸውና የአመራር ብቃታቸው ለርዕሰ ብሔርነት አሳጭቷቸዋል። ምናልባትም ስዒረ መንግሥቱ ተሳክቶ ቢኾን ኖሮ ኢትዮጵያን የሚመሯት "ፕሬዝዳንት" ፋንታ በላይ ነበሩ።

ይህን የጄኔራል ፋንታ በላይን ድርጊት ተከትሎ 'ማሽሟጠጥ የሚቀናው' ሰፊው ሕዝብ ተቀኘ ተባለ...

_"ፔፕሲ ኮካ ኮላው ከከተማ ጠፍቶ_

_ፋንታ ተገኘ አሉ በኮንቴይነር ሞልቶ"_

### ግንቦት 8፤ የነፍስ ውጭ፣ ነፍስ ግቢ ምሽት...

ከሁሉም በላይ ኢትዮጵያ በብዙ ጽናት፣ በብዙ ትጋት አምጣ ያዋለደቻቸው፣ ለወግ ማዕረግ ያበቃቻቸውን እጅግ ውድና ምትክ የለሽ የሚባሉ ጄኔራሎቿን በአንድ ጀንበር ያጣችበት... ምሽት።

አይደለም አገረ ኢትዮጵያ፣ አህጉር-አፍሪካ ሳትቀር ከተቀረው ዓለም ወራሪ ጦር ቢገጥማት ከፊት ልታሰልፋቸው የምትችላቸው ምርጥ ጄኔራሎቿ ነበሩ...።

### ግንቦት 8 የኾነው በትክክል ምንድነው?

ጓድ ሊቀመንበር ምሥራቅ ጀርመንን ለመጎብኘት ክብርት ወ/ሮ ውባንቺንና ልጃቸውን ትዕግስትን (ወይም ትምህርትን) አስከትለው፣ በትረ መኮንናቸውን እየወዘወዙ ቦሌ ተገኙ። ረፋድ ላይ።

መንጌ ቆቅ ናቸው። ሆን ብለው ሰዓት ያዛባሉ። ጠላትን ለማወናበድ ወይ ረፈድ ወይ ቀደም ይላሉ። እርሳቸው ላይ የሚዶልተው ብዙ ነዋ።

ያን ለታም እንዲሁ አደረጉ። ማልጄ ነው 'ምሳፈረው ብለው ለደኅንነት ሚኒስትራቸው ተናገሩ። ሚኒስትሮቻቸው እውነት መስሏቸው ቦሌ ማልደው ደረሱ። እርሳቸው ግን ረፋድ ላይ ግንባራቸውን ቅጭም አድርገው ከቸች...።

ብዙዎቹ ጄኔራሎች እስከዚያች ሰዓት ድረስ ይቁነጠነጡ ነበር። ቶሎ ወደ ቢሮ መመለስ አለባቸዋ። አጣዳፊ ሥራ ነው የሚጠብቃቸው።

ቀሪውን በ ገጽ 26 ይመልከቱ